

## ያስፈራል፤ ግን ኢትዮጵያ አትፈርስም!

ፕ/ር መስፍን ወልደማርያም

■ ገፅ 3 »

# ተስፋዬ ገብረአብ ከሚበጀው የሚፈጀው

ዓለማየሁ ገላጋይ /ደራሲና ሃያሲ/

■ ገፅ 3 »

www.fetehe.com Addis Ababa-Ethiopia ቅፅ 5 ቁጥር 195 አርብ ሰኔ 29 2004 ዓ.ም ዋጋ 7.00 ብር

# "ይቅርታ" የኢህአዴግ ወይስ




■ ገፅ 5 »



# በካንጋሮ ፍርድ ቤት የመጨረሻው ፍርድ ሰጪ ማን ነው?

■ ገፅ 8 »



## በአዲስ አበባ መዲና የአፍሪካ ሕብረት መንግስታት የመንገድና የመሬት ስሪት ታሪክ

ከፕ/ር ላጵሶ ጌ.ድሌቦ
የታሪክ ተመራማሪና ደራሲ.

■ ገፅ 12 »

## በግንቦት 7 ጉዳይ በሽብርተኝነት ወንጀል የተከሰሱት ግለሰቦች የተከሳሽነት ቃላቸውን ሰጡ

‹‹በዚህ አይነት በሃገሪቷ ውስጥ ያሉት 300,000 መምህራን አ`ባሪዎች ናቸው ማለት ነው?!››

‹‹በሀሰት ሰዎች ላይ መመስከር ስላልቻልኩኝ በእኔ ላይ በሀሰት ተመስክሮብኛል››

‹‹አማራ በመሆኔ ነው የታሰርኩት››
/ተከሳሾች/

■ ገፅ 15 »

ፊቸር

# ከከሰረው የትምህርት ፖሊሲ ጀርባ



ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

ዘመናዊ የትምህርት ስርዓት በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ ቢገባም ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለመሸጋገር አራት አስርታት ወስዶበታል:: በ1940ዎቹ መጀመሪያ ለያኔው ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ መከፈት አፄ ኃይለሥላሴ በስደት በነበሩበት ወቅት የገጠማቸው የምዕራባዊው ስልጣኔ ተጋልጦት እና አፄው ምዕራባዊውን የአዘማመን ዘዬ ለመከተል መጣራቸው እንደሆነ ብዙ ፀሐፊዎች ይናገራሉ:: ፕ/ር ተከስተ ነጋሽ "Education in Ethiopia: From crisis to the brink of collapse" በሚለው ስራቸው የቅድመ አብዮቱ የሀገሪቱ የትምህርት ስርዓት በሁለት አመለካከቶች ስር ወድቆ እንደነበረ ይናገራሉ:: እንደ ፕ/ሩ ሙግት፣ ዘመናዊው ትምህርት በተለይም በሉተራን ሚሽነሪዎች ከተመራ ንጉሱንና ሀገሩን የሚያከብር ዜጋ ማስለጠን ይቻላል የሚለው የአፄው ምልከታና እንደ አለምባንክና ዩኔስኮ ባሉ ተቋማት የተገፋው ኢትዮጵያን መሰል ደሀ አገራት ለማደግ የሰለጠነ የሰው ኃይል ያስፈልጋቸዋል የሚለው አካሄድ ለከፍተኛ ትምህርት መስፋፋት አስተዋፅኦ የነበራቸው ገዢ አመለካከቶች ነበሩ:: በእነ ፕ/ር መሳይ ከበደና ጳውሎስ ምልኪያስ ‹‹ቅኝ ገዢዎች ለተገዢዎቹ የአፍሪካ ሀገራት ካዘጋጁት ያልተናነሰ›› ተብሎ የሚወቀሰው የአፄው የትምህርት ስርዓት፣ እንደፖለቲካው ስርዓት ሁሉ አብዮቱ አፈራርሶታል:: የኃ/ሥላሴን የትምህርት ፖሊሲ ‹‹ልሂቅነትንና ፊውዳሊዝምን›› የሚያስፋፋ ሲል የወቀሰው ደርግ፣ ሶሻሊስታዊውን ‹‹አዲሱን ሰው›› ለመቅረፅ ያስችለኛል በሚል የመጀመሪያና ሁለተኛ የትምህርት ደረጃን በተከታታይ በ12 እና 15 በመቶ ለማሳደግ ሞክሯል:: መሃይምነትን ወደ 37 በመቶ ዝቅ በማድረጉ፣ እ.ኤ.አ. በ1980 ዓ.ም. በዩኔስኮ የተሸለመው የጓድ መንግሥቱ ስርዓት፣ የትምህርት ፖሊሲውን በአንድ ወጥ ርዕዮተ-ዓለም ስር ለማበጀት በመሞከሩና ይህን ተከትሎ ለመጣው የትምህርት ዝቅጠት ቁጥራቸው በበዛ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ይወቀሳል::

ትምህርት ለሁሉም?

ባለፉት ዓስርት ዓመታት ኢህአዴግ እየሄደበት ላለው ትምህርትን በእጅጉ የማስፋፋት ፖሊሲ የጉዳዩ አጥኚዎች ሶስት ምክንያቶችን ያቀርባሉ:: የመጀመሪያው የኢኮኖሚው ዕድገት ከፍተኛ ቁጥር ያለው የተማረ የሰው ኃይል መፈለጉና በመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚያልፉ ተማሪዎች መብዛት ሲሆን፤ ዶ/ር ሙሉ ነጋ እንደሚጠቅሱት እነዚህ ሁለት ጉዳዮች ቁጥራቸው የበዛ መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎችን የግድ ማለቱ ለትምህርት ተቋማቱ መስፋፋት አስተዋፅኦ አድርጓል:: ከዚሁ ጋር የሚያያዘው ሁለተኛው ምክንያት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መስፋፋት በራሱ የግድ የሚላቸው የመምህራን መኖር ሲሆን ይህን ዕጥረት ለመሻገር ተቋማቱን ማስፋፋት አስገዳጅ መሆኑ ይጠቀሳል:: ዶ/ር አማረ አስገዶም "Academic freedom and development of higher education in Ethiopia" በሚለው ጥናታዊ ስራቸው በመጨረሻ የሚያነሱት ውጪያዊ ግፊቶችን ነው:: እንደ ዶ/ር አማረ፣ የአለም ባንክ፣ የተለያዩ ዓለም አቀፍ የትምህርት አማካሪ ድርጅቶችና ከሀገሪቱ የትምህርት ሚኒስቴር ውጪ ያሉ የፖለቲካ ተቋማት እየታየ ላለው የትምህርት መስፋፋት ከፍተኛ ድርሻ ይይዛሉ::

በ1980ዎቹ መጀመሪያ የነበሩት ሁለት ዩኒቨርስቲዎች አሁን ቁጥራቸው ወደ ሰላሳሶስት ተጠግቷል:: ከነዚህ የመንግሥት ዩኒቨርስቲዎች በተጨማሪ በትምህርት ሚኒስቴር ቅድመ-ዕውቅና እና ዕውቅና መደብ ውስጥ የሚሰሩ የግል ኮሌጆች መኖር ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚገቡ ተማሪዎችን ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እንዲንር አድርጎታል:: በቀደመው ዓመት የወጣው የትምህርት ሚኒስቴር መረጃ እንደሚያሳየው ወደ ዩኒቨርስቲዎች የሚገቡ ተማሪዎች ቁጥር በ1980ዎቹ ከነበረው 9,327 ወደ 76,995 ከፍ ብሏል:: በተቋማቱ የሚሰጡትን የተለያዩ ፕሮግራሞች /የቀን፣ የማታና የክረምት/ ለማካተት ከተሞከረ በዓመት በአማካይ በ22.3 በመቶ በማደግ ቁጥሩ ወደ ሦስት መቶ ሺህ ይጠጋል:: በተለይም በሁለተኛ ዲግሪ የሚመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር በ1991 ዓ.ም. ከነበረው 864 የተማሪ ቁጥር ወደ 11,125 ንሯል:: እንደ ተቋሙ ዘገባም ወደ ድህረ-ምረቃ ፕሮግራም የሚገቡ ዜጎች ቁጥር ከዓመት ዓመት በ30 ከመቶ ይጨምራል:: ይህን መሰሉን የተቋሙን ቁጥራዊ ገለፃዎች ያጠናቀሩት ዶ/ር ሙሉ እንደሚያወሱት፣ የከፍተኛ ተቋማቱ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎች ቁጥር በዚህ መልኩ በመጨመሩ የመምህራኑ መጠን ከፍ ቢልም፣ የመምህር ተማሪ ጥምረታው በነበረበት ቆሟል::

ኢህአዴግ ትምህርትን እየሄደበት ባለው መልኩ ሲያስፋፋ ዘንግቷቸዋል ከሚባሉት ተደጋጋሚና ተጠቃሽ ጉዳዮች አንደኛው የፍትሃዊነት ጥያቄ ነው:: የነገሩ ተከታታዮች እንደሚሉት በፆታና በከተማ-ገጠር ተጣምሮሻዊ ዕድገት ላይ የት/ት ፖሊሲው አካሄድ ክስረታዊ ሆኗል:: ‹‹የከፍተኛ ትምህርትን ፍትሃዊነት ለማየት የምንችልበት አንዱ መንገድ የወንዶችና የሴቶችን ተሳትፎ በማገናዘብ ነው›› የሚሉት ዶ/ር ዋና ሌቃ፤ ‹‹የከፍተኛ ትምህርትን የማስፋፋት ፍላጎትና የቅበላ አቅም›› በሚል ርዕስ በአንድ መድረክ ላይ ባቀረቡት ጥናታዊ ፅሁፍ፣ ሴቶች በከፍተኛ ትምህርት ያላቸው ተሳትፎ ከ25 በመቶ ከፍ ማለት እንዳቃተው ይናራሉ:: የፍትሃዊነቱ ሌላ መመዘኛ፣ የትምህርት እድሉን የሚያገኙት መነሻቸው ከተማ ወይስ ገጠር ነው? የሚለው ሲሆን፣ እንደ ዶ/ር ዋና ድምዳሜ፤ ከ9-10 ባለው የትምህርት ደረጃ የከተማው ድርሻ 91.1 በመቶ መሆን እና ከ11-12 ባለው መሰናዶ ትምህርትም ከከተማ የሚመጡ ተማሪዎች መጠን ወደ 96.3% መጠጋቱ የትምህርት ስርዓቱ ኢ-ፍትሐዊነት ማረጋገጫ ይመስላል::

በዚሁ የፍትሐዊነት ጉዳይ ላይ ጥናት የሰራው ‹‹ዘያንግ ላይቭስ ፕሮጀክት›› የተባለው ተቋም በበኩሉ አዲስ አበባና ሐረሪ ክልሎች ከሌሎቹ የተሻሉ እንደሆነ ያስነብባል:: ተቋሙ "Education choices in Ethiopia: what determines whether poor children go to school?" በሚል ርዕስ ባወጣው ጥናት፤ ሁለቱ ከተሞች 94 በመቶ የሚሆኑትን ህፃናቶቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ሲልኩ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል በ30 በመቶ ተገድቧል:: ከዚሁ ተቋም ጋር በተዛመደ ስለጭብጡ የፃፉት ዶ/ር ብርሃኑ ቦጋለ፣ የሱማሌ ክልልን 15.1 በመቶና የአፋርን 14.8 በመቶ ቁጥሮችን በማንሳት በክልሎች መሀከል ያለውን ልዩነት ‹‹አስደንጋጭ›› ሲሉ ጠርተውታል:: እንደ ዶ/ሩ ትንታኔ፣ በተማሪዎች ክፍልን የመድገም /የመውደቅ/ የመቶኛ ልኬት፣ የአዲስ አበባ ከ3 በመቶ ሳይበልጥ፣ በአፋርና በጋምቤላ ክልሎች ያለው መጠን ወደ 35 በመቶ ቢጠጋም፣ የትግራይ ክልል ከዚህ ነፃ ሆኗል:: እኒህን ቁጥራዊ ትርክቶች የዘገበው ‹‹ዘ ያንግ ላይቭስ›› በተጠቀሰው ጥናቱ፣ ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ2015 ዓ.ም. ከሚጠናቀቀው የሚሊንየሙ የልማት ግቦች አንዱ የሆነውን ትምህርትን ሙሉ ለሙሉ የማድረስ ግብ አስቸጋሪ ያደርግባታል:: በገጠሩ የሀገሪቱ ክፍል ከሚታየው የመጀመሪያ ትምህርት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ አለመዳረስ በተጨማሪ፣ የትምህርቱ ስርዓት በከፍተኛ ሁኔታ በውጪ እርዳታ ላይ የቆመ መሆኑና ይህ ዕርዳታም ቀስ በቀስ ዝቅ እያለ መሄዱ የግቡን መሳካት ለመጠራጠር በተቋሙ የተጠቀሱ ምክንያቶች ናቸው::

ኢህአዴግ ራሱን ከቀደሙት ስርዓቶች ጋር በማነፃፀር በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት እንዲሰጥ ማድረጉን እንደስኬት ለማየት ቢሞክርም፣ ሁነቱን ያጠኑ ፀሐፊዎች የገዢውን ፓርቲ ስኬት ይጠራጠራሉ:: ከነዚህ አንዱ የሆኑት ዶ/ር ብርሃኑ ቦጋለ፣ የጋምቤላንና የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ክልልን በማሳያነት ያነሳሉ:: ዶ/ር ብርሃኑ እንደሚሉት በጋምቤላ ክልል የመጀመሪያ ደረጃ መጀመሪያ ሳይክል ትምህርት በኑዌር፣ አኝዋክና መዥንገር ቋንቋዎች ቢሰጥም፣ በቋንቋው የሚሰለጥኑ መምህራን በክልሉ ወደሚገኙ ሌሎች ተቋማት በመፍለሳቸው ብዙው ትምህርት በአማርኛ እንዲሰጥ አስገድዷል:: ከዚህ ባለፈ፣ በክልሉ የሚኖሩ የሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ዜጎች፣ ልጆቻቸውን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ለማስተማር እንደተቸገሩ ዶ/ር ብርሃኑ "Language determination in Ethiopia: what medium of instruction?" በሚለው ፅሁፋቸው ይናገራሉ:: የሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ የሁለተኛ ሳይክል ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ መሰጠት እንዳለበት ቢያዝም፣ በደቡብ ክልል ይህ አለመተግበሩን የሚናገሩት ፀሐፊው፤ የፖሊሲው አተገባበር ከፍተኛ ጉድለት እንዳለበት ያወሳሉ::

## ‹‹ሁላችሁም ወደ ዩኒቨርስቲ››

ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ቆይታቸው የተሻለ የዕውቀት ክሂል እንዲያዳብሩ ያለፉባቸው የትምህርት ደረጃዎች ወሳኝ እንደሆኑ ይታመናል:: ተማሪዎቹ በታችኛው የትምህርት እርከኖች የሚያስመዘግቡት የትምህርት ውጤት ተከትለው በሚመጡት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚኖራቸውን ተሞክሮ ይወስናል:: ዶ/ር ሙሉ ነጋ ‹‹ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገቡ ተማሪዎች የቅድመ-ዝግጅት ብቃት›› በሚለው ጥናታዊ ፅሁፋቸው እንደሚናገሩት፣ በታችኞቹ የትምህርት እርከኖች የሚታየው የጥራት መጓደል በከፍተኛ ትምህርት ጥራት ላይ እጅጉን የበዛ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳርፏል:: በሀገሪቱ በተካሄዱት ተከታታይ አገር አቀፍ የትምህርት ምዘናዎች ውጤት ላይ ተመስርተው ጥናታቸውን የሰሩት ዶ/ር ሙሉ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎቹ አማካይ ውጤት፣ ፖሊሲው ካስቀመጠው 50 በመቶ ማለፊያ ነጥብ ያነሰ መሆኑን በመጥቀስ፣ ፈተናዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ በተዘጋጁበትና የፈተና ጥያቄዎቹ በአብዛኛው የምርጫ ጥያቄዎች ሆነው ይህ ሀገራዊ ውጤት መመዝገቡ የፖሊሲውን የከፋ መደምደሚያ እንደሚጠቁም ያነሳሉ:: እንዲህ ዓይነቱን የከፋ ውጤት የሚያስመዘግቡ ተማሪዎች፣ ስርዓቱ ከሚከተለው ትምህርትን በተቻለ ልክ የማስፋፋት አካሄድ የተነሳ ለዩኒቨርስቲ ቅድመ ዝግጅት ወደሚያደርጉበት የትምህርት እርከን ይሻገራሉ:: ግሪጎሪ ኩሽ የተባሉ ፀሐፊ "What students engagement data tell us about college readiness?" በሚለው ፅሁፋቸው እንደሚጠቅሱት፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት ጥራት በቀዳሚነት የሚንተራሰው ዩኒቨርስቲዎቹ በሚቀበሏቸው ተማሪዎች አካዳሚያዊ አቅም ላይ ነው:: ይህንን ሁኔታ የመረመሩት ዶ/ር ሙሉ "Quality and Quality Assurance in Ethiopian Higher Education" በሚል ርዕስ ለህትመት ባበቁት የሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ስራ፣ የሁኔታውን አደገኛ አዝማሚያ ይተነትናሉ:: የሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ እንደሚለው የመጨረሻዎቹ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ዕርከኖች ተማሪዎቹን ለዩኒቨርስቲ ትምህርት ለማብቃት ያለመ ቢሆንም፣ ሀገራዊው የተማሪዎቹ ውጤት የሚናገረው የነገሩን ግልባጭ ነው:: ዶ/ር ሙሉ ባለፉት ዓመታት በብሄራዊ ደረጃ የተመዘገበውን ውጤት ተንተርሰው እንደሚናገሩት፤ የአብዛኞቹ የቅድመ-ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ውጤት ከ50 በመቶ ዝቅ ያለ ነው:: ምፀታዊ በሆነ መንገድ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማቱ የገቡ ተማሪዎች ቁጥር ከ50 በመቶ ያነሰ ካገኙት ተማሪዎች እጅግ የላቀ ሆኗል:: ‹‹ትምህርትን የማስፋፋት ፖሊሲው›› ይላሉ ዶ/ር ሙሉ ከወራት በፊት ባሳተሙት መፅሀፍ ‹‹የብዙዎቹ ተማሪዎች ውጤት ከአነስተኛው የማለፊያ ነጥብ በታች ቢሆንም ወደ ዩኒቨርስቲ እንዲገቡ አስችሏቸዋል::››

እጅግ ዝቅተኛ ውጤት የሚያመጡ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርስቲ እንዲገቡ ከመደረጉ በዘለለ ገዢው ፓርቲ ያወጣው የ70:30 የሙያ አከፋፈል ከኋላ የመጡትን ችግሮች እያባባሳቸው መምጣቱን አጥኚዎቹ ይናገራሉ:: በከፍተኞቹ ተቋማት መኖር ስላለበት ጥናት የሚካሄድባቸው የሙያ ዘርፎችን በተመለከተ (የተፈጥሮ ወይስ የማህበራዊ ሳይንስ መቅደም አለበት) በነገሩ ተከታታዮች ሁለት የክርክር ጫፎች አሉ:: የትምህርት ስብጥሮሹን አስመልክቶ ‹‹በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው የተማረ የሰው ኃይል ገበያ የትምህርት ተቋማቱን የሙያ ዘርፎች መወሰን አለበት›› የሚሉት በአንድ ጫፍ፤ ‹‹ፖለቲካዊው ስርዓት ይህን ማድረግ ይችላል›› የሚሉት በሌላው ጠርዝ ያሉ ሙግቶች ቢሆኑም፣ ኢትዮጵያ የመረጠችው ሁለተኛውን መከራከሪያ ነው:: ፓርቲው ለሀገሪቱ ዕድገት የተሻለ ነው ከሚል መነሻ 70 በመቶ የሚሆኑ የከፍተኛ ደረጃ ተማሪዎች የተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርቶችን ማጥናት አለባቸው የሚለውን የፖሊሲውን ውሳኔ ‹‹ተጨባጭ ስለመሆኑ የሚያጠያይቅ›› የሚሉ አጥኚዎች አሉ:: ዶ/ር ያለው እንዳወቅ፣ ዶ/ር ተስፋዬ ስሜላ፣ ዶ/ር ዳዊት መኮንንና አያሌው ሺበሺ የተባሉ ምሁራን "Assessment of science education quality indicators" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ፣ በባህር ዳርና ሐዋሳ ዩኒቨርስቲዎች ላይ በሰሩት ጥናት ለተጠቀሰው ድምዳሜ ማሳያዎቻቸውን በስፋት አቅርበዋል:: የየዩኒቨርስቲዎቹ የሳይንስ ክፍል ትምህርት ካሪኩለም በፅንሰ ሀሳብም ሆነ በተግባር የላቀ ክሂል ያላቸውን ‹‹ሳይንቲስቶች›› ማውጣት ግቡ እንደሆነ ቢናገርም፣ እነዶ/ር ያለው ጥናታቸውን የሰሩባቸው ዩኒቨርስቲዎች አቅም ሊጠቀስ የሚችል አይደለም:: በአጥኚዎቹ በፊዚክስና ሂሳብ ክፍለ ትምህርቶች ያሉ ክዋኔዎች ለዚህ ማስረገጫ ሆነው ቀርበዋል:: በአፕላይድ ፊዚክስ ትምህርት፤ ካሪኩለሙ የሜትሮሎጂ፣ ኒውክሊየር ሜዲስንና ጂኦ-ፊዚክስ ኮርሶች መኖር እንዳለባቸው ቢናገርም በዩኒቨርስቲዎቹ እነዚህ ኮርሶች አይሰጡም:: ከዚህ ጉድለት በተጨማሪም የክፍለ ትምህርቱ ተማሪዎች ገቢራዊ እንቅስቃሴዎች የሚያደርጉባቸው ተቋማት የሉም:: እንደነ ዶ/ር ዳዊት ጥናት፤ የሂሳብ ትምህርት ክፍሉም ኮምፒውተር ነክ ኮርሶች እንዲሰጡ በካሪኩለሙ ቢጠቅስም፣ በቁሳቁስና ክሂሉ ባላቸው መምህራን እጥረት የተነሳ ዩኒቨርስቲዎቹ ይህን ማድረግ አልተቻላቸውም:: ሌላው ተያያዥ የሆነው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ የሚታየው ዋነኛ ችግር በሙያው የላቀ አቅም ያላቸውና ራሱ የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ካስቀመጠው በዩኒቨርስቲዎች ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራን ስብጥር መስፈርት አንፃር መሟላት አለመቻሉ ነው:: እንደ ተቋሙ መስፈርት፤ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከሚያስተምሩ መምህራን መሀከል የመጀመሪያ ዲግሪያላቸው 20 በመቶ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ ዲግሪ ያላቸው ደግሞ በተከታታይ 50 እና 30 በመቶ መሆን እንዳለባቸው ይናገራል:: ፖሊሲው ይህን ቢልም፣ የተለያዩ አጥኚዎች ከዚህ ተፃራሪ የሆኑ ቁጥሮችን ያስነብባሉ:: ዶ/ር ሙሉ እንደሚጠቅሱት፣ በጅጅጋ ዩኒቨርስቲ ሁለተኛ ዲግሪ ያለው መምህር የለም የሚያስብል ሲሆን፣ በመቀሌ ዩኒቨርስቲም ሦስተኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን የአንድ እጅ ጣት አይሞሉም:: ዶ/ር ዋና ሌቃ በበኩላቸው፤ በሀሮማያ፣ ሀዋሳ፣ ጅማ፣ አዳማና ጎንደር ዩኒቨርስቲዎች ያሉት የመጀመሪያ ዲግሪ ብቻ ያላቸው መምህራን ቁጥር በአማካይ እስከ 50 በመቶ ይደርሳል:: ከዶ/ር ዋና ሀተታ በሰፋ መልኩ ፕ/ር ኬት አሽክሮፎት "Ethiopia: Dilemmas of higher education massification" በሚለው ፅሁፋቸው በአዳዲሶቹ ዩኒቨርስቲዎች ካሉት መምህራን 70 በመቶ የሚሆኑት የመጀመሪያ ዲግሪ ብቻ ያላቸው መሆናቸውን በማስታወስ ሀገሪቱ ትምህርትን ለማስፋፋት ስትል ጥራቱን እየደፈጠጠች እንደሆነ ይናገራሉ::

በዚህ ጭብጥ ላይ የሚፅፉ አጥኚዎች ለዚህ መሰሉ ጥልቅ ችግር ሦስት ምክንያቶችን ያቀርባሉ:: በፖለቲካዊ አፈና፣ በአካዳሚያዊ ነፃነት ዕጦትና የተሻለ ኑሮ ፍለጋ በሚሉ ገፊ ምክንያቶች የሚታየው የተቋማቱ መምህራን ስደት አንዱ ሲሆን፤ ሌላኛው መነሻ፣ ህዝባዊዎቹ የትምህርት ተቋማት የሚፈልጉትን ሳይሆን ትምህርት ሚኒስቴር በፈቀደው ልክ መምህራኑ ወደ ዩኒቨርስቲዎቹ መመደባቸው ነው:: ተቋማቱ መምህራን የመቅጠር ነፃነታቸው ቢከበርላቸው መምህራኑ ትልልቆቹን ተቋማት ይመርጣሉ በዚህም አዳዲሶቹ ዩኒቨርስቲዎች ይጎዳሉ ሲል ትምህርት ሚኒስቴር ቢከራከርም፣ የተሻለ የትምህርት ደረጃ ያላቸው መምህራን በግዳጅ ከሚሄዱባቸው ተቋማት ይልቅ ወደ ግል የኢኮኖሚው ሴክተር ለመዛወር ተገደዋል:: በሦስተኛነት መንግሥት ለዩኒቨርስቲዎች በመነሻ መስፈርቱ መሰረት የሚያስፈልጉትን መምህራን ሳያሰለጥን፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማቱን ለማስፋፋት መወሰኑ መሆኑ ይጠቀሳል:: ዊልያም ሴንት የተባሉ ፀሐፊ በበኩላቸው፣ በከፍተኛው የኢትዮጵያ ትምህርት ተቋማት የበጀት አመዳደብ ጉዳይ አግባብነት እንደሚጎድለው ይናገራሉ:: ፀሐፊው "Higher education in Ethiopia: The vision and its challenges" በሚለው ፅሁፋቸው ለዩኒቨርስቲዎቹ የሚሰጠው ባጀት በቀዳሚነት ከሚቀበሏቸው ተማሪዎች መጠን ጋር ከመዛመድ እንደሚነሳ በመጥቀስ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከሚቀበለው የተማሪ መጠን ዕጥፍ የሚሆን ባጀት ሲመደብለት፣ በተፃራሪው እንደ ደቡብ ዩኒቨርስቲ ያሉት አዳዲስ ተቋማት ከተማሪዎቻቸው ቁጥር ያነሰ ባጀት ብቻ ይዘጋጅላቸዋል::

## ጥራት ካለ አካዳሚያዊ ነፃነት?

ትምህርት ማንኛውም የኅብረተሰብ አካል የራሱን ተፈጥሮአዊ የማወቅ አቅም ፍላጎት ከግብ ለማድረስ፣ የግል ፈጣሪነቱን ክህሎት ለማውጣትና ለማጎልበት፣ ለማኅበረሰባዊ እንከኖች መፍትሄ ለማበጀት ሲል የሚተገብረው የመብቱ አንዱ መታያ እንደሆነ በተባበሩት መንግሥታት ዓለማቀፍ የሰብዓዊ መብቶች አዋጅ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ ተደንግጓል:: ይህ ኢትዮጵያ ከፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ህጎች መሀከል አንዱ ቢሆንም፣በተግባር ለማዋል አካዳሚያዊ ነፃነት እጅግ ወሳኝ ሁነት ነው:: በሀገሪቱ ባሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ይህ ነፃነት መጣሱን የሚናገሩት ፀሐፊዎች የበዙ ናቸው::

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋዎች ጥናት ፕሮፌሰር የሆኑት ባዬ ይማም "Academic freedom at Addis Ababa University: An overview of its past and current experience" በሚል ርዕስ ባሳተሙት ጽሁፋቸው ላይ በመማር መብትና ትምህርት በሚሰጥበት አውድ መካከል ቀጥተኛ ምክንያታዊ ትስስሮሽ እንዳለ ያብራራሉ:: ይሄ ምሁራዊ አውድ እውቀትን በማስተላለፍ ሂደት ውስጥ የመንግሥት ፖለቲካዊ ጣልቃገብነትን ጨምሮ ፍርሃትን ሊፈጥሩ የሚችሉ ማንኛውም አይነት ክልከላዎች የማይስተዋሉበት ከባቢ መሆን እንዳለበት ፕሮፌሰሩ ይሟገታሉ:: እነዚህ የነፃነት መስመሮች በሁለት ማዕቀፍ ውስጥ የሚካተቱ ሲሆን፤ የመጀመሪያው ማዕቀፍ በግለሰብ ደረጃ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ለሚገኝ ማንም የማኅበረሰብ አካል ሊያገኘው የሚችለው መብት ሲሆን በዚህም ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ፣ ከሌሎች ጋር ህብረት መፍጠርና ለተፈጠረው ኅብረት ሀሳብን ያለገደብ መግለፅ ከመጀመሪያው የነፃነት ሀሳብ ጋር የሚጠቃለል ነው:: የአካዳሚው ማኅበረሰብ እንደ ተቋም ራሱን ችሎ የሚሰራበትን መብት ደግሞ በሁለተኛው ማዕቀፍ ውስጥ የሚስተናገዱ መብቶች ይሏቸዋል:: እውቀት የማምረትና የማስተላለፍ ተልዕኮአቸውን በራሳቸው እንዲወጡ እና የአስተዳደር አካላቶችንም ራሳቸው መምረጥ እንዲችሉ ማለትም መንግሥት የሚፈልገውን እንዲሾም የሚያስመቹ ሁኔታዎች አለመኖር እና በአጠቃላይ ማኅበረሰቡን ለመምራትና መንግሥታዊ ፖሊሲዎችን ለመቅረፅ እንዲሁም ለመተግበር በሚደረገው የማኅበረሰባዊ ሀላፊነቶች መሪ የመሆን ሚና ከመብቶች ውስጥ የሚካተቱ እንደሆነ በተባበሩት መንግሥታትና በልዩ ኮሚቴው ተቀባይነትን ያገኙ የነፃነት የመብት ማዕቀፎች መሆናቸውን ፕ/ር ባዩ ይናገራሉ::


ከአካዳሚያዊ ማኅበረሰብ ዋናው አካል የሆኑት ተማሪዎች ማጥናት የሚፈልጉትን የትምህርት ክፍል የመምረጥ፣ የሚማሩበት ተቋም ለትምህርታቸው የሚያስፈልገውን በሙሉ የማሟላት ግዴታ፣ ተወካዮቻቸውን በነፃነት የመምረጥ፣ በግልም ሆነ በቡድን ስለ ሀገራዊም ይሁን አለማቀፋዊ ጉዳዮች የመወያየት እንዲሁም ምክንያታዊነት ላይ በመንተራስ ያለፍርሃት አስተማሪዎቻቸውን የመቃወም መብቶች እንዳሏቸው ዓለማቀፍ ማኅበረሰብ የተስማማበት ቃልኪዳን መሆኑ ይጠቀሳል::

በአ.አ.ዩ በሳይንስ ፋኩልቲ ተባባሪ ፕሮፌሰር የሆኑት ደምሱ ገመዳ "Academic freedom in Ethiopia: The case study of Addis Ababa university" ብለው በሰየሙት ጥናት፣ በዩኒቨርስቲው ተቋማዊ እና አካዳሚያዊ ነፃነት ዙሪያ ለጥናታቸው ይረዳቸው ዘንድ ባሰባሰቡት መጠየቅ ከዘጠኝ መሠረታዊ ተቋማዊ መብቶች መካከል ስምንቱ በጣም ዝቅተኛ በሚባል ደረጃ ላይ እንደሚገኙ አረጋግጠዋል:: ከጣልቃገብነት ነፃ መሆን፣ የአካዳሚያዊ ማህበረሰብ መሪዎቹን ለመምረጥ ያለው ስልጣን፣ ተቋማዊ ነፃነቱን ለመከላከል ያለው አቅም እንዲሁም ሕይወትና ንብረት አደጋ ላይ እስካልወደቁ ድረስ የታጠቀ ሀይል እንዳይገባ መቋቋምን የመሰሉ መብቶች እየተጣሱ እንደሚገኙ በዶ/ር ደምሱ ዩንቨርስቲውን የአካዳሚክ የነፃነት ዕጦት ደረጃ ለማሳየት የተጠቀሱ ዋነኛ ጭብጦች ናቸው:: በዚሁ ጥናት ላይ ከተማሪዎች የተሰበሰበው መጠየቅ እንደሚያመለክተው በግለሰብና በቡድን ደረጃ መሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶች ይጣሳሉ:: የመንግሥት ፖሊሲዎችን እና ተቋማዊ ትግበራዎች ለመተቸት፣ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚሳተፉ ተወካዮቻቸውን ለመምረጥና በካሪኩለም ክለሳዎች ላይ ያላቸውን ምልከታ ለማንፀባረቅ የዩንቨርስቲው አባላት ከፍታኛ ተግዳሮቶች እንዳሉባቸውም ተጠቅሷል:: አካዳሚያዊ ነፃነትን ተንተርሰው የጎንደር ዩኒቨርስቲን እንደማሳያ በመጠቀም ምርምር ያደረጉት ፕሮፌሰር ሀብታሙ ወንድሙ በበኩላቸው፤ ቃለ ምልልስ ካደረጉላቸው (በከፍተኛ የስልጣን እርከን የሚገኙ የዩኒቨርስቲው መምህራንን ጨምሮ) መካከል አብዛኞቹ ስለ አካዳሚያዊ መብትና ነፃነት የሚያውቁ እንዳልሆኑ በመግለፅ ጥናቱ ከተካሄደባቸው መምህራን መሀከል 68 በመቶ የሚሆኑት በከፍተኛ ትምህርትና በአጠቃላይ ሀገራዊ ፖሊሲዎች ላይ ሊያቀርቡ የሚያስቧቸው ትችቶች አስመልክቶ ነፃነት እንደሌላቸው መስክረዋል:: ፕሮፌሰሩ "Academic freedom in Ethiopia: The case of university of Gonder" በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጥናት ‹‹ስልጣን ላይ ባለ የአንድ ግለሰብ ውሳኔ ምክንያት መምህራኖች ይባረራሉ:: …አቤት የሚባልበት ቦታ የለም::›› በማለት የአንድ መምህርን ማስታወሻ አያይዘው አቅርበዋል:: የተቋማትን ፖሊሲዎችና ተግባራቶች በግልፅ ለመተቸት፣ የመምህራን ማህበርን ለማቋቋምና በማህባራቱ ለመሳተፍ፣ መሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶችን ለመጠቀም፣ መብቶች ሲጣሱ አቤት ለማለት፣ የውስጣዊ ፖሊሲ ዝግጅቶች ሂደት ላይ መሳተፍን ጨምሮ በተለያዩ ተቋማዊ ነፃነቶች ላይ ከባድ ሊባል የሚችሉ መሰናክሎች መኖራቸውን ፕ/ር ሀብታሙ ይናገራሉ::

### ድንጋይ አንጣፊ ምሁራን

ትምህርትን ለሁሉም ዜጎች በስፋት የማድረስ ተልዕኮን እንደያዘ የሚያስበው

ወደ ገፅ 10 ዞሯል



ፕ/ር መስፍን ወልደማርያም

ኢትዮጵ ትወድቅ ይሆናል፤ ግን ያለጥርጥር ትነሣለች፤ በፊትም ወድቃ ተነሥታለችና፤ ኢትዮጵ ትሰነጠቅ ይሆናል፤ ግን ያለጥርጥር ትገጥማለች፤ በፊትም ተሰንጥቃ ገጥማለችና፤ ለኢትዮጵያ በጎ የማይመኙላት የአየሉ ቢመስሉም የንስሐ ጊዜ ስትሰጣቸው ነው፤

# ያስፈራል፤ ግን ኢትዮጵያ አትፈርስም!

ይቺ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ስንት የመከራ ወንዞችን ተሻግራለች! ገና ስንት ትሻገራለች! ስንት የግፍ ተራራዎችን አቋርጣለች! ገና ስንት ታቋርጣለች! ስንት የበደል ሰይፎችንና ጦሮችን አምክናለች! ገና ስንት ታመክናለች! ስንት የውጭ ኃይሎችን አሳፍራለች! ገና ስንቱን ታሳፍራለች! ስንት አምባገነኖችን እያለቀሰች ቀብራለች! ገና ስንቱን ትቀብራለች! ጭቆና ከኢትዮጵያውያን ደም ሙልጭ ብሎ ወጥቶ በነፃነት፣ በእኩልነት፣ በዳኝነት በጠራ ደም እስቲተካ ድረስ ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታ ትጸልያለች! እግዚአብሔርም ቃል ኪዳን አለበት ይሰማታል! የኃያላን ኃያል ኢትዮጵያ እንድትፈርስ አይፈቅድም!

የኢትዮጵያን መፈራረስ የሚመኙ ግለሰቦችም መንግሥቶችም ሞልተዋል፤ ኢትዮጵያ እንድትፈራርስ የሚመኙ ጭንጋፍ ልጆችም አሏት፤ ማኅጸንዋ እየደማ እየረገማቸው ሰላምና እንቅልፍ አጥተው አብጠው ይፈነዳሉ፤ የኢትዮጵያን መፈራረስ የሚመኙ መንግሥቶች ሁሉ ከዚህ በፊት ቀድመው ፈራርሰዋል፤ ወደፊትም ይፈራርሳሉ።

የአገራቸው ፍቅር፣ የእርስበርሳቸው ዝምድና፣ የተራራውና የሸለቆው፣ የሜዳውና የገደሉ፣ የበረሀውና የለምለሙ፣ የዝናቡና የወንዙ፣ የዓየሩና የነፋሱ፣ የበዓላቱና የድግሱ፣ ያለውን አብሮ መቋደሱ፣ ተዝካሩ፣ ሙታዓመቱ ለሞቱ፣ መላእክቱ፣ ቅዱሳቱ፣ ሰማዕታቱ፣ እየተሸከሙ ያደረሱት ጸሎቱ፣ ለምዕተ-ዓመታት የተከማቸው እምነቱ፣ ሃይማኖቱ፣ በዚህ ሁሉ የተገነባው ኅብረቱ እንዴት ይፈርሳል! ማን ችሎ ያፈርሰዋል! አፍራሾች ቀድመው ይፈርሳሉ!

አንዳንዶች ቢጨነግፉም፣ አንዳንዶች ቢክዱም፣ አንዳንዶች ሆዳም ቢሆኑም፣ አንዳንዶች ቢወላውሉም፣ ኢትዮጵያ ልጆች አሏት፣ አሁንም የሚሞቱላት፣ ያልበሏት፣ የሚሳሱላት፤ ያልሸሿት፤ አፈሯን የሙጢኝ ብለው አፈርሽ እንሁን የሚሏት፣ ደሀነትም ሆነ ጭቆና ካንቺ አይለዩንም የሚሏት፣ ኢትዮጵያ ዛሬም ልጆች አሏት ስትፈርስ ቆመው የማያዩ፣ ሲያማት ነፍሳቸውን ዘልቆ የሚያማቸው፣ ሳልፈርስ አትፈርስም ነው ቃል ኪዳናቸው።

ቱርክና ግብጽ መጥተው ሄደዋል፤ ፖርቱጋል መጥቶ ሄዷል፤ እንግሊዝ መጥቶ ሄዷል፤ ኢጣልያ መጥቶ ሄዷል፤ ጠላቶች እየመጡ በመጡበት ተሸኝተዋል፤ ወዳጆች በጨዋነት ተስተናግደው ተዋኅደዋል፤ ቤተ ሙሴ፣ ቤተ ክርስቲያን፣ ቤተ እስልምና ኢትዮጵያዊ ሆነዋል፤ ዛሬ እንግዳ አይደሉም፤ ዛሬ ባዕድ አይደሉም፤ ኢትዮጵያ በፍቅር ለመጣ ፍቅር ነች፤ ምቹ ነች፤ በጠብ ለመጣ እሾህ ነች፤ ትዋጋለች።

ኢትዮጵያ፣ ነቢዩ ኢሳይያስ ለአንቺ የተናገረው ይመስለኛል፤ ‹‹ብርሃንሽ መጥቶአልና፣ የእግዚአብሔርም ክብር ወጥቶልሻልና ተነሺ፤ አብሪ፤ እነሆ ጨለማ ምድርን ድቅድቅ ጨለማም አሕዛብን ይሸፍናል፤ ነገር ግን በአንቺ ላይ እግዚአብሔር ይወጣል፤ ክብሩም በአንቺ ላይ ይታያል፤ አሕዛብም ወደብርሃንሽ፣ ነገሥታትም ወደመውጫሽ ጸዳል ይመጣሉ።

ዓይኖችሽን አንስተሽ በዙሪያሽ ተመልከቺ፤ እነዚህ ሁሉ ተሰብስበው ወደአንቺ ይመጣሉ፤ ወንዶች ልጆችሽ ከሩቅ ይመጣሉ፤ ሴቶች ልጆችሽንም በጫንቃ ላይ ይሸከሙአቸዋል፤ በዚያን ጊዜ የባሕሩ በረከት ወደአንቺ ስለሚመለስ፣ የአሕዛብም ብልጥግና ወደአንቺ ስለሚመጣ አይተሽ ደስ ይልሻል፤ ልብሽም ይደነቃል፤ ይሰፋማል፤ የግመሎች ብዛት የምድያምና የጌፌር ግመሎች ይሸፍኑሻል፤ ሁሉ ከሳባ ይመጣሉ፤ ወርቅንና ዕጣንን ያመጣሉ፤ የእግዚአብሔርንም ምስጋና ያወራሉ፤ የቄዳር መንጎች ሁሉ ወደአንቺ ይሰበሰባሉ፣ የነባዮትም አውራ በጎች ያገለግሉሻል፤ እኔን ደስ ሊያሰኙ በመሠዊያዬ ላይ ይወጣሉ፤ የክብሬንም ቤት አከብራለሁ።›› (60/1-7)

ኢትዮጵ ትወድቅ ይሆናል፤ ግን ያለጥርጥር ትነሣለች፤ በፊትም ወድቃ ተነሥታለችና፤ ኢትዮጵ ትሰነጠቅ ይሆናል፤ ግን ያለጥርጥር ትገጥማለች፤ በፊትም ተሰንጥቃ ገጥማለችና፤ ለኢትዮጵያ በጎ የማይመኙላት የአየሉ ቢመስሉም የንስሐ ጊዜ ስትሰጣቸው ነው፤ ኢትዮጵያ ዕብሪተኞችንም ትሕትና ታስተምራቸዋለች፤ ዕብሪተኞች ከነዕብሪታቸው በራሳቸው እሳት ቀልጠው እስቲያልቁ ኢትዮጵያ ትእግስትዋ አያልቅም፤ ኢትዮጵያ ትእግስት ነችና።

በበጎ መንፈስ እስከተመራን ድረስ፣ ፍርሃትንና አለመተማመንን፣ ጥላቻን፣ ጠብንና ድብድብን፣ ሊዘሩብን ከሚፈልጉ ርኩሳን መናፍስት ከራቅን ኢትዮጵያችን አትፈርስም፣ የደፈረሰውም ቶሎ ይጠራል።

---

# ተስፋዬ ገብረአብ ከሚበጀው የሚፈጀው

ዓለማየሁ ገላጋይ

ተስፋዬ ገብረአብ በመጽሐፎቹና በብሎጉ ሥማቸውን ካነሳቸው አራት ግለሰቦች ጋር በጉዳዩ ላይ አውርቼአለሁ። የእናቱን እሮሮ ነው ሁሉም የደገሙልኝ። በተለይ አንደኛው < <ለምን እኔን ማጥቂያ ያደርገኛል? ስለምን ከሚጎዱኝ ሰዎች ጋር ያያይዘኛል?> > ነበር ያለኝ። ቀላል የሚመስሉ ግን ከባድ የሆኑ የእናቱ ሮሮዎች ተስፋዬ እስካለ ድረስ ለመቀጠላቸው ምንም የሚያጠራጥር ነገር የለበትም።

ጋዜጠኛና ደራሲ ተስፋዬ ገብረአብ ሰሞኑን የኖህን ልጅ ካምን ሆኖ ከረመ ማለት ይቻላል። አባቱ ኖህ በወይን ጠጅ ሰክሮ እራሱን በማይቆጣጠርበት ጊዜ እራቁትነቱን (ነውሩን) ያየውን ካምን… አይቶ ያልበቃውን፣ ወንድሞቹም የአባታቸውን እራቁትነት አይተው እንዲሳለቁ የጋበዘውን ካምን… ይህን በማድረጉም ዘር ማንዘሩ በአባቱ የተረገመውን ካምን… ተስፋዬ ሆኖ ከረመ። ካምን ለመሆን ህሊና ቢስነት እንጂ ሌላ ችሎታ አለመጠየቁን ተስፋዬ የተረዳው አይመስልም። ድፍረት እንጂ ብልሃት ግድ እንደማይል የገባው አይመስልም። ይህም በሚያቀርባቸው ቁንፅል ታሪኮች ላይ በጉልህ ይነበባል።

ተስፋዬ ገብረአብ ሰሞኑን ካምን የሆነው እንዲህ ነው። ባትወልደውም ያሳደገችውን አገር የታሪክ ጉንፍ እየገላለጠ እራቁትነት ለማየት እጅግ በመጣር ላይ ይገኛል። ለማየት መጣሩ ሳይበቃው ሌሎችም እንዲሳለቁ ‹‹የቅዳሜ ማስታወሻ›› ብሎ በሰየመው ብሎጉ በመጋበዝ ላይ ነው። በተለይ አፄ ምኒልክን፣ አፄ ኃይለሥላሴን፣ እቴጌ ጣይቱ እና እቴጌ መነን የቀጥታ ተጠቂ ለማድረግ ፍላጎት እንዳለው በጉልህ ይታያል። ከእነሱ በሰተጀርባ ደግሞ እኛን ኢላማ አድርጓል። ‹‹የንጉሠ-ነገሥቱ እናት››፣ ‹‹የጎጃም ልዕልት›› እና ‹‹የመነን አራተኛ ባል›› በተሰኙ ፅሁፉ እነዚህ አጤዎችና ንግሥቶች ላይ ቦጫቂ የንሥር ጥፍር የመሰለ ብዕሩ ሲያንዣብብ በገሃድ ይስተዋላል። እንዴት? ለምን? ምን ፍለጋ? ምን ለማትረፍ? ይሄን ከመፈተሻችን በፊት ተስፋዬ ገብረአብን በጥቂቱ ለማየት እንሞክር።

የማይታበለው ነገር ተስፋዬ ገብረአብ ለአማርኛ ሥነ-ፅሁፍ ባለውለታ ነው። ‹‹ያልተመለሰው ባቡር››፣ ‹‹የቢሾፍቱ ቆሪጦች›› እና ‹‹የቡርቃ ዝምታ›› የተሰኙ ልቦለዶቹ እንደውርዴ ከወላጆቻቸው የወረሱት የዘር ጠባይ ቢኖርባቸውም የትረካ ጥበባቸው ቅርሳችን መሆኑን መካድ አይቻልም። እንዲሁም ሁለት ‹‹ባለቅፅ›› መጽሐፎችንም አበርክቶልናል። ‹‹ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ›› እና ‹‹እፍታ›› የተሰኙት እነዚህ ‹‹ባለቅፅ›› መጽሐፎች ተስፋዬ የጡት አባት ሆኗቸው በጉዲፈቻነት ባያሳድጋቸው ኖሮ ምናልባትም የሥነ-ፅሁፍ አፀድ ውስጥ የማይቀበሩ በጨቅላነት የተቀጠፉ በሆኑ ነበር። ከእነዚህ ሁሉ በኋላ ደግሞ ሁለቱ ‹‹የጋዜጠኛው›› እና ‹‹የደራሲው›› ማስታወሻዎች ተከትለዋል። የዘር በሽታው ካንዱ ሥራ አንዱ የማይሻል ቢሆንም በሁለቱ ‹‹ማስታወሻዎች›› ላይ ተስፋዬ ለጋነቱን አጥቶ፣ እንደዛፍ ተንጋዶ መብቀሉ በጉልህ የሚስተዋልባቸው ሆነዋል።

የተስፋዬ ገብረአብ አብዛኞቹ ሥራዎች (ብሎጉን ጨምሮ) እንደ ገጠር ሴትወይዘሮ መኳኳያቸው ‹‹ጥላሸት›› ነው። ‹‹ጥላሸቱ›› ደግሞ ከስም ማጥፋት ጥቀርሻ የሚገኝ ነው። ይሁንና ሥራዎቹ ገና በፈገግታ ሲቀርቡን ጉራማይሌአቸው የጥላሸት እንዳልሆነ ሁሉ በውበት ይጠልፉናል። ተስፋዬ ‹‹የሚነቅስበት›› የራሱ የሆነ የቋንቋ እሾህም አለው። እየጠቀጠቀ ከሚያደማው ‹‹ድድ›› ሆነ ‹‹አንገት›› ውስጥ ከማዝጐርጐር የሚመነጭ ውበት ያፈልቃል። ይሄንን ደግሞ ተስፋዬ ያውቃልና የስም ማጥፋት ጥቀርሻውን ሆነ መጠቅጠቂያ እሾሁን አይጥልም። ‹‹የጋዜጠኛው ማስታወሻ›› ላይ ስለመኳኳያ ‹‹ጥላሸቱ›› እንዲህ ይላል።

‹‹በዚህ መጽሐፍ ባልተለመደ ሁኔታ እውነተኛ ስማችሁን ለተጠቀምኩ ሁሉ ባለማስፈቀዴ ይቅርታ እየጠየቅሁ፤ አትቀየሙኝም ብዬ በመገመቴ ደግሞ አመሰግናለሁ።››

ከእጅ ያፈተለከ የጫካ እርግብ ይመስል መጽሐፍን ያህል የረጅም ዘመን ነዋሪ በዘፈቀደ መልቀቅ ከባድ ጥፋት ነው። ተስፋዬ ገብረአብ ሆን ብሎ ለሰራው ጥፋት ይቅርታውን የጥፋቱ አባሪ አድርጐ መልቀቁ ደግሞ ትልቅ ሹፈት ይሆንብናል። ተስፋዬ የጥፋቱን ጥፋትነት ቀድሞ ቢረዳውም እራሱን ገስፆ መተው የሚችል አይመስልም። ምክንያቱ ደግሞ ግልፅ ነው። የተጋባበትን ሳይሆን የለማበትን አንጡራ ባህርይ ስለሚያስተናግድ ብቻ ነው። ልጅ ሆኖ በእናቱ ላይ ያደረገውን ‹‹የደራሲው ማስታወሻ›› ላይ እንዲህ ይተርክልናል። ንዑስ ርዕሱ ‹‹የልጅነት ተራሮች›› ነው።

የጓደኛው የነብዩ አባት ኢሬቻን ለማክበር ወደሆራ እየወሰዱአቸው ነው። መንገድ ላይ ስለክብረ በዓሉ መልካም መልካም ነገር ይነግሯቸዋል። ተስፋዬ በጨዋታው መካከል ገብቶ ‹‹እናቴ ግን እንዲህ አልነገረችኝም›› በማለት ክብረ-በዓሉን የሚያጥላላ ነገር ይዘበዝባል። የነብዩ አባት ይሄን በሆዳቸው ይዘው ወደ ተስፋዬ እናት ይሄዳሉ። በነገሩም ላይ ይነጋገራሉ። ሰውዬው ገና እግራቸው ከቤት እንደወጣ እናት ከጉማሬ ቆዳ የተሰራውን አለንጋ አንስተው ተስፋዬ ላይ ይወርዱበታል። ‹‹ስትገርፈኝ እንዲህ እያለች ነበር›› ይላል፡-

‹‹የቤትህን ምስጢር ደጅ እያወጣህ ትዘረግፋለህ? ጅላጅል የሆንክ ፍጡር። ለሰው የሚነገርና የማይነገረው መቼ ይሆን የሚገባህ? በችግር ጊዜ ከሚደርሱልኝ፣ ተከባብረን ከኖርነው ጐረቤቶቼ ልታጣላኝ! ጅል!፣ ልጅ የሆንክ ፍጥረት…›› (ከገፅ 38-39)

ተስፋዬ ገብረአብ በመጽሐፎቹና በብሎጉ ሥማቸውን ካነሳቸው አራት ግለሰቦች ጋር በጉዳዩ ላይ አውርቼአለሁ። የእናቱን እሮሮ ነው ሁሉም የደገሙልኝ። በተለይ አንደኛው ‹‹ለምን እኔን ማጥቂያ ያደርገኛል? ስለምን ከሚጐዱኝ ሰዎች ጋር ያያይዘኛል?›› ነበር ያለኝ። ቀላል የሚመስሉ ግን ከባድ የሆኑ የእናቱ ሮሮዎች ተስፋዬ እስካለ ድረስ ለመቀጠላቸው ምንም የሚያጠራጥር ነገር የለበትም። እናቱ ካሉት ውስጥ ‹‹ጅል›› የምትለው ቃል ብቻ የምትታመን አይሆንም። እናት በመሆናቸው የልጃቸውን ጥፋት ከጅልነት ቆጥረውታል፣ ካልሆነም ተስፋዬ ለማደናገሪያነት እናቱ አፍ ላይ ቃሏን አኑሯታል እንጂ ተስፋዬ ጅል አይደለም። ውጤቱን እየገመተ ብቻ ሳይሆን ቀድሞ እያወቀ የሚያደርግ ለመሰሪነት የቀረበ ሰው ነው።

ተስፋዬ ገብረአብ የአካባቢ ተቆርቋሪ ይመስል ከውድቅዳቂ የታሪክ ፌስታል ቆሻሻ ኢትዮጵያዊ ዘንቢል የመስራቱ የሰሞኑ ሙከራ በጅልነት የተፈፀመ አይደለም። ያስወነጨፈብን ጫፉ የክፋት መርዝ የተቀባ የጠላትነት ቀስት ነው። በሚያመረቅዝ የሐፍረት ቁስል ሊመታን ሆን ብሎ የታሪክ ምሁራንን ከለላ አድርጐ ሰንዝሮብናል። ቁንፅል እውነታዎችን በመቅመል መላው ታሪካችንን የውቤ-በረሃ ገድል ሊያስመስለው ሞክሯል። ነገሥታቱን፣ መኳንንቱንና ሴትወይዘሮዎቹን ለድሪያ ብቻ የተፈጠሩ አሻንጉሊቶች በማድረግ ከኢትዮጵያ ውስጥ በታሪክ መኩራትን ጠራርጐ ለማጥፋት አልሞ አንዲት የዶሎዶመች ሙሬ አዘጋጅቷል።

ኢትዮጵያዊ የስብዕና ነውጥ በመሻት ከታሪክ ነቁጥ ተነስቶ የፃፈው አንዱ ሥራው ‹‹የንጉሠ ነገሥቱ እናት›› የሚል ርዕስ ተሰጥቶታል። የሚተርከው አጤ ምኒልክ ‹‹ከሥራየ ቤት›› (ገረድ) ስለወለዷት ሸዋረጋ ነው። ገና በእናቷ ሆድ ሳለች ከአጤ ምኒልክ እንደተረገዘች ያወቁት እቴጌ ጣይቱ ከቤተመንግሥት እንዳባረሯት ይተርካል። የሰባት አመት ልጅ ሳለች እናቷ ስለሞተችባት እንዴት የመከራ ጊዜ እንደገፋች ያጫውተናል። በመጨረሻ ወታደር አግብታ ሐረር ስትኖር የአባቷ ስም ማተቧ ላይ ተፅፎ በመገኘቱ ባሏ ወደቤተመንግሥት ያመጣታል። አጤ ምኒልክ ከልጃገረዶች መካከል ይለይዋታል፣ ለራስ አሊም ይድሯታል። በ1888 ዓ.ም. ልጅ እያሱ የተወለደው ከሸዋረጋ እንደሆነ ይነግረናል።

እዚህ የተስፋዬ ትርክት ውስጥ ፅሁፉን ወደ ውሸትነት ሊለውጥ የሚችል ከፍተኛ የዘመን ዝንፈት ይታያል። ሸዋረጋ ስትረገዝ እናቷን ከቤተመንግሥት ያባረሯት እቴጌ ጣይቱ እንደሆኑ በገደምዳሜ ተነግሮናል። እንዲያ ከሆነ ጉዳዩ የተፈፀመው ከ1876 ዓ.ም. ወዲህ ነው ማለት ነው። ምክንያቱም እቴጌ ጣይቱና አጤ ምኒልክ ተገናኝተው የተጋቡት በዚህ ዘመን በመሆኑ ነው። ሸዋረጋ እንደው ከአመት በኋላ ተወለደች ቢባል እንኳን ከ1877 ልጅ ኢያሱን እስከወለደች ጊዜ (1888 ዓ.ም) ያለው ዕድሜ ገና አስራ አንድ ዓመት ብቻ ይሆናል። ተስፋዬ፣ ሸዋረጋ ወታደሩን ያገባችው ለአቅመ ሔዋን ደርሳ መሆኑን ደግሞ ነግሮናል። ታዲያ እንዴት በአስራ አንድ አመት ዕድሜዋ ልትወልድ ቻለች? ድሎት በዝቶ የሴት ወጓን ቀድማ አየች እንዳይባል ሸዋረጋ በችግር ተቆራምዳ ያደገች ናት። ታዲያስ? እንዴት? በምን?…

ሙግት እንጂ ስድብ በመረጃ አይደገፍም። ተስፋዬ ገብረአብ ከዘመኑ አፋትቶና አፍኖ እዚህ ዘመን ያመጣው ታሪክ ለዚህ ትውልድ ነውር የሚመስል ጥቃቅን ነገር ስላለበት ብቻ ሙሉ ትኩረቱን የሰጠው ታሪኩን አቅርቦ አንጡራ ኢትዮጵያውያኑን ማሸማቀቁ ላይ ነው። ከዚያም ኢትዮጵያዊ ኩራትን ሰብሮ ሀገር ተከላካይነትን ማዳከም። ከዚያስ?

ተስፋዬ ገብረአብ ታሪካችንን ከክብሩ አውርዶ የሴትና የወንድ ‹‹ሎሚ ውርወራ›› ብቻ ለማስመሰል የጣረው ተደጋጋሚና አንድ አይነት ቁመና ያላቸውን ታሪክ ነክ ፅሁፎች በማቅረብ ነው። ‹‹የጎጃም ልዕልት›› የተሰኘው ፅሁፉ በንጉሥ ተክለኃይማኖት ልጅ የተነሳው መኳንንታዊ የጋብቻ ውርክብ እንዴት ለአጠቃላይ ጦርነት አስግቶ እንደነበር ይተርክልናል። በመጨረሻ አጤ ምኒልክ እንዴት እንደቋጩት ይነግረናል። ከቁመታቸውም፣ ከወርዳቸውም ቀናንሶ

ወደ ገፅ 13 ዞሯል

ርእሰ አንቀፅ

# የኢቲቪ ዘጋቢ ፊልሞች አቀራረብ አንድምታ

የአገራችን ትልቁ እና ብቸኛ የሆነው የቴሌቪዥን ጣቢያ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በገዥው ፓርቲ ፖለቲካ የተጠለፉ ርዕሰ ጉዳዮች ያላቸው ዘጋቢ ፊልሞችን በማቅረብ ይታወቃል፡፡ ይህ ሁኔታም ከዜጎች እለታዊ እና ወርሃዊ ገቢ ላይ በሚሰበሰብ ገንዘብ መተዳደሪያውን ያደረገው ይህ ግዙፍ የቴሌቪዥን ጣቢያ፣ ስሙ የህዝብ ቢሆንም ተጠሪነቱና አገልግሎቱ አገሪቷን ለሚያስተዳድረው አውራ ፓርቲ ብቻ ለመሆኑ ከብዙ ማሳያዎች አንዱ ይህ ነው፡፡

እንዲሁም በተደጋጋሚ በዚሁ የቴሌቪዥን ጣቢያ ላይ የሚተላለፉ ዘጋቢ ፊልሞች ሚዛናዊነት የሚጎላቸው ከመሆናቸው በተጨማሪ፣ ተሰርተው ለእይታ ከቀረቡም በኋላ በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚኖራቸው ተቀባይነት እምብዛ ነው፡፡ ፍትህ ዘጋቢ ፊልሞች ለዕይታ ሲቀርቡ የኢ.ሬ.ቲ.ቪ. ድርጅት ልብ የማይላቸው ነገር ግን ከአገራዊ ፋይዳቸው እና ማህበረሰባዊ ተጽዕኗቸው አንጻር ልብ ሊባሉ ይገባል የምትላቸውን ሁለት ነጥቦች በጥቅሉ ማንሳት ትፈልጋለች፡፡ የመጀመሪያው ትኩረት ሊሰጥበት ይገባል የምትለው ነጥብ፣ ዘጋቢ ፊልሞቹ ሲሰሩ ለዚህ ኃላፊነት የሚዘጋጁ ግለሰቦች ለወቅታዊው መወያያነት የመረጡትን ርዕስ ወደ ፊልም ከመቀየራቸው በፊት በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ተገቢውን መረጃ መሰብሰብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህ መረጃዎች በእውነታ ላይ የተመሰረቱ ሆነው ለየትኛውም ቡድን ያላደላና የመጨረሻውን ፍርድ ለሕዝብ የሚተው መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ሁለተኛው ትኩረት ሊሰጥው የሚገባው ነጥብ፣ ለዘጋቢ ፊልሙ ርዕስ መርጦ የሚሰራው ግለሰብ ባነሳው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ልምድና ችሎታ ያለው መሆን እንደሚገባው ፍትሕ ትጠቁማለች፡፡

ከላይ ባነሳናቸው ጥቂት መስፈርቶች አንጻር እንኳን ካየነው ኢቲቪ በተደጋጋሚ ብዙ ስህተቶችን ፈጽሟል፡፡ ፍትሕ ኢቲቪ ከዚህ ቀደም እንደሰራቸው ስህተቶች ሁሉ ባሳለፍነውም ሳምንት መጀመሪያ ለዕይታ ያበቃው ‹‹ብዙ ሃይማኖቶች አንዲት አገር›› የሚለው ዘጋቢ ፊልም ላይ አደገኛ የሆኑ ስህተቶችን ዳግም ፈፅሟል የሚል እምነት አላት፡፡ ሃይማኖትን የሚያክል ትልቅ ርዕሰ ጉዳይ አንስቶ ከጀርባው የመንግሥትን የፖለቲካ አጀንዳ ለመጨመር መታተር ተገቢ ካለመሆኑ በተጨማሪ ዜጎችን ማሳቱ አይቀሬ ነው፡፡ ይህ ዘጋቢ ፊልም በኢትዮጵያ ውስጥ ለረጅም አመታት ሰፍኖ የቆየው የሃይማኖቶች መቻቻል እና መከባበር በአሁኑ ጊዜ መልኩን እያጣ መምጣቱን ለማሳየት የታቀደ ነው፡፡ አዘጋጁ ለዚህ ማስረጃ ይሆናሉ ያላቸውን የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን አንስቶ ከተለያዩ የሃይማኖት ተቋማት ተወካዮች፣ ከማህበረሰብ ክፍሎች እና ከፖለቲካ ተንታኞች የተውጣጡ የግለሰቦችን አስተያየት አቅርቧል፡፡ ዘጋቢ ፊልሙ፤ በአገራችን ምልክቱ እየታየ መጣ ስለተባለው የሃይማኖት አክራሪነት ምንነትና ምክንያት እንዲሁም መፍትሄውን ለመፈለግ በሙመስል መልኩ ነገር ግን በእጅጉ በተሳሰተ መንገድ የሚባክን ነው፡፡

ፍትህ ለሃይማኖቶች ወግ አጥባቂነትም ይሁን አክራሪነት ምክንያቱ በአገሪቷ እየተንሰራፋ የመጣው የጠባብነት አመለካከትና የዜጎች በህግ ፊት እኩል ያለመዳኘት መሆኑን ታምናለች፡፡ ዜጎች በብሔር ማንነታቸው፣ በእምነት ልዩነታቸው እና በቡድን መብቶቻቸው ላይ አድልዎና መገለል ሲደርስባቸው ለጋራ ችግራቸው የጋራ መፍትሄ ለማበጀት ሲሉ ከነበሩበት ስብስብ የተነጠለ ማንነትን እንዲያበጁ ይገደዳሉ፡፡ እነዚህ መገፋቶች ዞሮ ዞሮ መብትን ከማስመለስ አኳያ የሚታዩ በመሆናቸው ምክንያት መሰረታዊ ጥያቄያቸው ሃይማኖታዊ ወይም ብሔር ተኮር መሆኑ ይቀርና ፖለቲካዊ ይሆናል፡፡

በፍትህ እምነት በሃይማኖት ጉዳይ የተጀመረው እሰጥ አገባ በስተመጨረሻ ‹‹ተበደልን›› የሚሉ ወገኖች ለችግራቸው መፍትሄ የሚበጅለት የመንግስት ስልጣንን በመያዝ ብቻ ነው ወደሚል አመለካከት በማዘንበል አስቀድመው የተነሱለት የመብት ጥያቄ ፈር እንዲስት ማድርጉ አይቀሬ ነው፡፡ ኢህአዴግ በኃይማኖት ተቋማት ላይ ባሳረፋቸው ጣልቃ ገብነቶች ምክንያት ብዙ ምእመናን ተከፍተዋል፡፡ የዚህ ኩርፊያ ድምር ውጤት የሆነው ደግሞ መንግስት አሁን እየተከሰተ ነው የሚለው ‹‹የአክራሪነት መስፋፋት›› እንደ አንድ ማሳያ አድርገን ልንወስደው እንችላለን፡፡

ፍትህ የተቋማት ነፃነት፣ የመናገር፣ የመሰብሰብ፣ የመደራጀት፣ ፍትሓዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት፤ በጥቅሉ ለተወሰኑ ቡድኖች ብቻ ሲያዘነብል፤ ማህበረሰቡ ቀድሞ መታወቂያው የነበረው ኢትዮጵያዊ ማንነቱ በእጅጉ እንዲቀየር ከማድረጉም በተጨማሪ ነባሩ አገራዊ ጨዋነት ከመሰረቱ እንዲናድ ያደርገዋል የሚል አቋም አላት፡፡ ለዚህም ነው ለአክራሪነት መስፋፋት ከማንም እና ከምንም በፊት ኢህአዴግ ራሱ ኃላፊነቱን ሊወስድ ይገባል የምትለው፡፡

ፍትህ በዘጋቢ ፊልሙ ላይ መንግስት አክራሪነትን ለማስወገድ በሚል በማስረጃነት ያቀረባቸው የታሪክ እውነቶች አሁን ላይ ሆኖ ለሚሰማ እና ለሚያይ ታዳጊ ትውልድ በሚመጥን መልኩ የቀረበ አይደለም የሚል እምነት አላት፡፡ በመካከለኛው የኢትዮጵያ ታሪክ የተደረጉ ጦርነቶች፣ በጊዜው የወደሙ ንብረቶችና ኃብቶች መነሻቸው ሃይማኖታዊ ብቻ እንደሆነ አድርጐ ማቅረቡም ትልቅ የታሪክ ስህተት ነው፡፡ ለዚህም ነው አንድን ዘጋቢ ፊልም ከመስራት አስቀድሞ በተመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በቂ እውቀት ሊኖር ይገባል የምንለው፡፡

ፍትህ ደግማ ደጋግማ እባካችሁ ያልተፃፈ ታሪክ አታንብቡልን፣ ያልተከሰተ ድርጊት አትንገሩን፣ ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ ማቅረብ ይበልጥ አጀንዳውን ከማራገብ ውጭ ፋይዳው ሀገራዊ ጥፋት ነው ብላ ማሳሰብ ትፈልጋለች፡፡


ፍትህ

ጋዜጣ

በማስተዋል ህትመት ማስታወቂያ ስራድርጅት በየሳምንቱ የሚታተም

የአሳታሚው አድራሻ
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 11/12
የቤት ቁጥር አዲስ
ፒያሳ ራስ መኮንን
ድልድይ አጠገብ

ሥራ አስኪያጅ
ማስተዋል ብርሃኑ

ዋና አዘጋጅ
ተመስገን ደሳለኝ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ጀሞ
ሳይት የቤ.ቁ. 012

አዘጋጆች
ሙሉነህ አያሌው
ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

ከፍተኛ ሪፖርተር
ኤልያስ ገብሩ

ሪፖርተሮች
ሰውዓለም ታዬ
ሚካኤል ዲኖ

አምደኞች
ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም
ዶ/ር በድሉ ዋቅጅራ
አለማየሁ ገላጋይ
ብርሀኑ ደቦጭ
ኤፍሬም ስዩም
እንዳለጌታ ከበደ
ጌታቸው ታምራት
ታዲዮስ ታንቱ

ጸሐፊ
ቤተልሄም አመነሸዋ

የሽያጭ ሰራተኞች
ደለለኝ ሙሉጌታ
ታመነ ደገፋ

0911 928401
0911 712361
011 8951856
✉ 110744

E-mail:
fetih_gazeta@yahoo.com
www.fetehe.com

አታሚ
ብርሃንና ሰላም
ማተሚያ ድርጅት
ክ/ከተማ፡- አራዳ
ቀበሌ፡- 17
የቤት፡- 984


ነፃ አስተያየት ነፃ አስተያየት

# በሕግ መዳኘት እያለ ፍጥጫ ለምን?



ታምራት ታረቀኝ

አርብ ሰኔ 22/2004 ዓ.ም. የተነበበው ፍትህ ጋዜጣ ‹‹ሠማያዊ ፓርቲና ምርጫ ቦርድ እየተወዛገቡ ነው›› የሚል ዜና አስነበበን፡፡ የውዝግቡ ምክንያት ሠማያዊ ፓርቲ የሕጋዊ ምዝገባ ሰርተፍኬት ስጠኝ በማለት ለቦርዱ ያቀረበው ጥያቄ ምላሽ ያለማግኘቱ እንደሆነና ሰኔ 21/2004 ዓ.ም. ቦርዱ ጽ/ቤት ተገኝተው ላነጋገሩዋቸው የፓርቲው አባላት የቦርዱ ሰብሳቢ ፕ/ር መርጊያ በቃና ‹‹በሚቀጥለው አርብ ለቦርዱ አቅርቤ አስወስናለሁ›› ማለታቸው በዜናው ተገልጿል፡፡ ቦርዱ እስካሁን ያልወሰነ ከሆነ ከዚህ በልት በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን የተደመጠውና የተነበበው ከቦርዱ አካባቢ ይሰጥ የነበረው ምላሽ በማን ውሳኔና ሥልጣን ይሆን? ሁለቱንም ወገኖች የሚገዛና የሚዳኝ ሕግ እያለስ ለወራት የዘለቀ ፍጥጫ ለምን አስፈለገ?

ሠማያዊ ፓርቲ በጥያቄው መሠረት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ቦርዱም የፓርቲውን ጥያቄ ተቀብሎ ለመመዝገብ ወይንም አልመዘግብህም ለማለት ያላቸው መብትና ግዴታ በተሻሻለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ 573/2000 ዓ.ም. በግልጽ የሰፈረ በመሆኑ ለሕግ አልገዛም ማለት ወይንም ራስን ከሕግ በላይ የማድረግ ነገር ከሌለ በስተቀር የሚያፋጥጥም የሚያወዛግብም ለወራት ዜና ሊሆን የሚገባውም አልነበረም፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 ‹‹በዚህ አዋጅ መሰረት የፖለቲካ ፓርቲዎችን የመመዝገብ ሥልጣን የቦርዱ ነው›› በማለት በ17 ንዑሳን አንቀጾች የቦርዱን መብትና ግዴታዎች ወይም ሀላፊነትና ተግባር ይዘረዝራል፡፡ በእነዚህ ውስጥ ከቦርዱ ሌላ የተጠቀሰ አካል የለም፡፡ ታዲያ በአዋጅ ሥልጣን የተሰጠው ቦርድ ያለመወሰኑን የቦርዱ ሰብሳቢ ከተናገሩ ለወራት ለዘለቀው ፍጥጫም ይባል ውዝግብ ምክንያት የሆነው አካል ማነው? ሠማያዊ ፓርቲ ቦርዱ የሕጋዊ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ከለከለኝ ሲል የቦርድ ሰብሳቢ ለቦርዱ አቅርቤ አስወስናለሁ ማለታቸው እንቆቅልሽ ነው፡፡ ችግሩ ያለው የት ጋር ነው የሚል ጥያቄም ያስነሳል፡፡ ሠማያዊ ፓርቲ ቦርዱን ለመኮነን ሲል ያቀረበው ነው እንዳይባልም የቦርዱ ዋናና ምክትል የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊዎች በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ‹‹የሠማያዊ ፓርቲ መስራቾች የሚፈለግባቸውን አሟልተው ስላላቀረቡ ነው›› ማለታቸውን ሰምተናል፤ አንብበናል፡፡ ቦርዱ ውሳኔ ባልሰጠበት ጉዳይ ላይ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊዎቹ መግለጫ የሰጡት በማን ትእዛዝና ውሳኔ ወይንም የትኛው ሕግ በሰጣቸው ስልጣን እንደሆነ ማስረዳት ጋዜጠኞችም መጠየቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ የሕዝብን ድምጽ ወደ ሥልጣን የመቀየር ትልቅ ኃላፊነት ስለተሸከመው የምርጫ ቦርድ አሰራር እንድናውቅ ይረዳናል፡፡ ቦርዱም ተጠያቂነትና ግልጽነት ያለበት አሰራር ቢከተል የሕዝብ አመኔታን ሊያስገኝለት ይችላል፡፡

አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ለምዝገባ ማመልከቻ ሲያቀርብ ተያይዘው መቅረብ ያለባቸው ሰነዶች በአዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 በፊደል ሀ እስከ ሰ ተዘርዝረዋል፡፡

ሀ. የፖለቲካ ፓርቲ መመስረቻ ጽሑፍ

ለ. የፓርቲው ፕሮግራም

ሐ. የመተዳደሪያ ደንብ

መ. የፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች ስምና አድራሻ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች በኃላፊነት ለመስራት የተስማሙ ለመሆናቸው የሚገልጽ በፊርማቸው የተረጋገጠ ሰነድ

ሠ. መስራቾች የፈረሙበትና ለሕዝብ ይፋ የሆነ ሰነድ

ረ. የፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች በፓርቲው ጠቅላላ ጉባዔ የተመረጡ መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ፤

ሰ. የፖለቲካ ፓርቲውን ኦዲተር ስም አድራሻና በኦዲተርነት ለማገልገል የተስማማበት በፊርማው የተረጋገጠ ሰነድ፤ ሲሆኑ የቦርዱ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊዎች ‹‹የሠማያዊ ፓርቲ መስራቾች ያላሟሉዋቸው በማለት በመገናኛ ብዙሃን ሲገልጹ የተሰማው 1 መሥራቾች የፈረሙበትና ለሕዝብ ይፋ የሆነ ሰነድ 2. የሀብትና ንብረት የገቢና ወጪ ሰነዶች›› ናቸው፡፡ የሠማያዊ ፓርቲ አመራሮች ደግሞ ሁለተኛው ጥያቄ በአዋጅ ያልተገለጸና ፓርቲው ሕጋዊ ምስክር ወረቀት ከማግኘቱ በፊት ተግባራዊ ሊሆን የማይችል ነው፡፡ የመጀመሪያው ጥያቄ ደግሞ በማን፣ የት፣ መቼና እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን የሚገልጽ መመሪያ ባለመኖሩ ከቦርዱ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ጋር በመነጋገር አድርጉ ያሉንን ፈጽመናል ይላሉ፡፡ ፓርቲው የተጠየቀውን አሟልቻለሁ ካለ እዛው ላይ ቆሞ ለቦርዱ አቅርቦ ውሳኔ ማስጠት ሲገባ ይህ አለመሆኑ ይመስለኛል አዋጁን የዘነጋ ስህተት እንዲፈጠር ያደረገው፡፡

አዋጁን እያዩ ወይንም እያስታወሱ ቢሰራ ግን ለተነሳው ጉዳይ ምላሽ የሚሰጡ ግልጽ አንቀጾች አሉት፡፡ አንቀጽ 9(8) ‹‹ቦርዱ የምዝገባ ማመልከቻውን ያልተቀበለው የፖለቲካ ፓርቲው ማሟላት ያለበትን ሳያሟላ በመቅረቱ ከሆነ ይህንኑ በ30 ቀናት እንዲያሟላ በጽሑፍ ለአመልካቹ ያሳውቀዋል›› ይላል፡፡ ከሰማያዊ ፓርቲ የሚሰማው ደግሞ የምዝገባ ማመልከቻ ጥያቄ ካቀረቡ ከአምስት ወራት በላይ እንደሆናቸው ነው፡፡


አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 9 ደግሞ ‹‹ቦርዱ የፖለቲካ ፓርቲው ያቀረበውን ማመልከቻ ውድቅ ያደረገው እንደሆነ ይህንኑ ምክንያት ለአመልካቹ በጽሑፍ ያሳውቃል›› ነው የሚለው፡፡ ከፍትሕ ዜና የተረዳነው ግን ቦርዱ ዛሬም ድረስ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ አለመስጠቱን ነው፡፡

ይህ ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 9(5) ‹‹ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 መሰረት የሚቀርብለትን ማመልከቻና አባሪ ሰነዶች በዚህ አዋጅ በተመለከተው መሰረት የተሟሉ እና ትክክለኛ መሆናቸውን ፓርቲው ሕገ መንግሥቱንና ይህን አዋጅ የሚያከብርና የሚያስከብር መሆኑን በማረጋገጥ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲውን ጽ/ቤት በመጎብኘት የምዝገባ ማመልከቻውን በተቀበለ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ የምዝገባውን ፎርማሊቲ አጠናቆ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለአመልካቹ ይሰጠዋል›› በማለት የተገለጸው በቦርዱ ተፈጻሚ ያለመሆኑን ያሳያል፡፡

አዋጁ ግን እንዲህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ቀጣዩ ነገር ምን

■ ወደ ገፅ 6 ዞሯል »

# ‹‹ይቅርታ›› የኢህአዴግ ቃጭል? ወይስ…



ተመስገን ደሳለኝ

**‹‹ይቅርታ›› እንዲህ በአዳዲስ ብልቶች ተከፋፍሎ ትርጉሙ ከመየቀሩ በፊት የቆየ ባህል ነበር። ይህ አንድ እውነት ነው። ኢህአዴግን መደገፍ መብት የሆነውን ያህል፣ አምባገነንነቱንና ሙሰኛነቱን መቃወም መብት መሆኑ ደግሞ ሌላ እውነት ነው። ስለዚህም ገና ከገና ‹‹የአይናቸው ቀለም አላማረኝም›› እየተባለ አንዱን ‹‹ሽብርተኛ›› ሌላውን ‹‹ተላላኪ›› እያሉ ወንጅለውና ፈርደው ሲያበቁ ‹‹ይቅርታ›› በሚባል እጥን አጥኖ ማንነትንም ሆነ ሞራልን ማምከን፤ ቀን ከሌሊት እንቅልፍ አሳጥቶ የሚያሳድረውን ያንን ‹‹የቁጣ ቀን›› መምጫ ዕድሜ ከማሳጠር ባለፈ ጠቀሜታ የለውም።**

## 1998

አዲስ አበባ በለውጥ ፍላጐት ከአፍ እስከ ገደቧ ታጥናለች፡፡ እዚህም እዚያም የፖለቲካ ወግ ይጠሰቃል፡፡ በቡድን ሆነው፣ በስሜት ተውጠው በፖለቲካ ጉዳይ የሚከራከሩ በርክትዋል፡፡ ለዓመታት የፖለቲካ ጉዳይ ‹‹ፆም›› የሆነባቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች ሳይቀሩ ጎራ ለይተው በሚከራከሩ ሠራተኞቻቸው ተፈስገዋል፡፡ ‹‹ቅንጅቱ መንግሥት ለመመስረት የሚያስችል ድምፅ አግኝቷል›› ይላል አንዱ፡፡ ‹‹ቢሆንም ኢህአዴግ ይገግማል!›› ሲል ይመልሳል፤ ኢህአዴግ በምርጫ ስልጣን አይለቅም የሚል አቋም ያለው ተከራካሪ፡፡

…የጋዜጦች እትሞች ከምርጫው በፊት ከነበረው ቅጂ ከሶስት እስከ አምስት እጥፍ ድረስ ጨምረዋል፡፡ ማንበብ የሚችለውም፣ ማንበብ የማይቻለውም ቋሚ የጋዜጣ ሸማች ሆኖአል-እድሜ ለምርጫው፡፡ በኢትዮጵያ ‹‹መንግሥት…›› ሲባል የተቃወመውን በሙሉ የሚገድል እንደሆነ ከልምድ የተገነዘቡ ወላጆች ለልጆቻቸው በመስጋታቸው ጭንቀታቸው ጨምሯል፡፡ እነዚህ ኩነቶች የድህረ ምርጫ 1998 ዓ.ም. ዋነኛ መገለጫዎች ነበሩ፡፡

እንዲህ ውጥረት በነገሠበት አንድ ቅዳሜ ከቅንጅቱ ዋነኛ አመራሮች አንዳቸውን በአካል ልተዋወቅ ወደ ቀጠሮ ቦታ እየሄድኩ ነው-መስከረም 28 ቀን 1998 ዓ.ም.፡፡ በምርጫው ላይ የጎላ ተሳትፎ የለኝም፡፡ የየትኛውም ፓርቲ አባል አይደለሁም፡፡ ድምፄንም ለማንም አልሰጠሁም፡፡ ነገር ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ እልፍ አእላፎችን ከጎኑ ማሰለፍ ከቻለው ‹‹ቅንጅት›› መሪዎች አንዳቸውን ልተዋወቅ ነው፡፡ የሚያስተዋውቀኝ ደግሞ በእጅጉ የማከብረውና የማደንቀው የጋራ ወዳጃችን አብይ ተክለማርያም ነው፡፡ ያኔ ተወዳጇ አዲስ ነገር ጋዜጣ አልተመሰረተችም፡፡ አብይ የሚያዘጋጃት ‹‹መዝናኛ›› የተባለች በድህረ ምርጫ እየገነነች የመጣች ጋዜጣ ግን ነበረች፡፡ ቀጠሮአችንም ጋዜጣው ቢሮ ውስጥ ነው፡፡ ልተዋወቅ እየሄድኩ ያለሁት የቅንጅቱ ምክትል ሊቀመንበር ሆና ከተመረጠች 14 ቀናት ብቻ ካለፉት ከብርቱካን ሚደቅሳ ጋር ነው፡፡ (እርግጠኛ ባልሆንም ብርቱካን ቀድማኝ የደረሰች መሰለኝ) …በጥቂት ደቂቃ ልዩነት ውስጥ ዝናዋ በአጭር ጊዜ ከናኘው እንስቷ ፖለቲከኛ ብርቱካን ጋር ተገናኘን፡፡ ከዚህ ቀደም እንደሚተዋወቁ ወዳጆች የሞቀ ሰላምታ ተለዋወጥን፡፡ ዛሬ ፋይሷ በተዘጋው በመዝናኛ ጋዜጣ ቢሮም ለአንድ ሰዓት ያህል አወራን፡፡ ብዙ ነገሮችን አነሣን፣ ብዙ ነገሮችን ጣልን፡፡ ኢህአዴግ እየተፍረከረከ እንደሆነ ግምቷን ነገረችኝ፡፡ ከኢህአዴግ አመራር ውስጥም ሙሉ በሙሉ መሸነፋቸውን የተቀበሉ ሰዎች እንዳሉ ተነጋገርን፡፡ አንዳች ለውጥ እንደሚኖርም አብዝተን ተስማማን፡፡ ከቆይታችን በእጅጉ የሳበኝ ግን በውስጧ ያለው ጥንካሬ እና ብርቱ የትግል መንፈስ ነው፡፡ ‹‹ዳኛ እና ዐቃቤ ሕግ ሆኜ ሰርቻለሁ›› አለችኝ በስሜት ተውጣ፡፡ ራሴን ላይና ታች በማወዛወዝ እያዳመጥኩ መሆኑን አረጋገጥኩላት፡፡ ቀጠለች ‹‹ነገር ግን እነዚህን ቀናት (ከተመረጠችበት ጊዜ በኋላ ያሉትን ነው) እንደኖርኩት አይነት ደስተኝነት ተሰምቶኝ አያውቅም፡፡›› ንግግሯ በደስታ ሞላኝ፡፡ ኢትዮጵያውያን ወንዶች ብቻ ሳይሆኑ፣ ኢትዮጵያውያን ሴቶችም የለውጡ ፊት መሪ ሊሆኑ እንደተዘጋጁ እርግጠኛ ሆንኩ፡፡ …ብርቱካን እየተናገረች ነው፡፡ እኔም እየሰማሁ ነው ‹‹በየደረስኩበት የሚያገኘኝ ሰው ያበረታታኛል፡፡ ጣቱን እያሳየ ድጋፉን ይገልፅልኛል፡፡ ለዚህ ሕዝብ ዛሬ ብታሰርም አይቆጨኝም›› አለች ቀልብን በሚገዛ ድምፅ፡፡

‹‹እታሰራለሁ ብለሽ ትሰጊያለሽ?›› እንደዋዛ የጠየኳት ጥያቄ ነው፡፡ ‹‹አዎን!›› ስትል በቀላሉ መለሰች፡፡ ግዙፉን ቦርሳዋን እየነካካችም ‹‹መቼ እንደምታሰር ባላውቀውም ዛሬ ብታሰርም ዝግጁ ለመሆን ሻርፕና ቀላል ልብሶችን በዚህ ቦርሳ ይዤ ነው የምንቀሳቀሰው›› አለችኝ መለስተኛ ሻንጣ የሚያክለውን የእጅ ቦርሳዋን መነካካቷን ሳታቋርጥ፡፡ ደነገጥኩ፡፡ ተገረምኩም፡፡ እንዴት አይነት ቁርጠኝነት ነው? ይህ አይነቱ ድፍረትስ ‹‹ተራራን ከማንቀጥቀጥ›› በምን ያንሳል? ለራሴ ያቀረብኩት ጥያቄ ነው፡፡…እንዴት ደስ ይላል ለሀገር ወገንተኛ መሆን፤ ለህዝብ ማድላት!

የሆነ ሆኖ ኢህአዴግ እንደቀድሞ በቀላሉ የማያንበረክካቸው እና የማያስፈራራቸው መሪዎች እየተፈጠሩ እንደሆነ ገመትኩ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ብርቱካን ሚደቅሳ አንዷ ለመሆኗ ደግሞ እርግጠኛ ሆኛለሁ፡፡ ማን ነበር ‹‹እንስቷ ነብር›› ያላት? ብቻ እንጃ፡፡

## ከሶስት ዓመት በኋላ

…ብርቱካን ሚደቅሳን ጨምሮ ሁሉም የቅንጅት አመራሮች ታስረው በይቅርታ ተፈተዋል፡፡ ቴዲ አፍሮም ‹‹ሆ በል ክራር፣
ሆ በል ማሲንቆ
ስታይ ሰው ታርቆ…››

የሚል ነጠላ ዜማ ለቆ በየመዝናኛ ቦታው አዋቂዎችንም፣ ወጣቶችንም… ዕቅል አሳጥቶ እያዘለለ አስጨፍሯል፡፡ ይህ ከሆነ አንድ አመት በኋላ አንድ ነገር ተከሰተ፡፡ ‹‹በሶስት ቀን ውስጥ የብርቱካን ሚደቅሳ ይቅርታ ሊነሳ ነው›› የሚል ወሬ መላ ሀገሪቱን ናጣት፡፡ ‹‹ምክንያቱ ምንድር ነው?›› የሚሉ ጠያቂዎችም እልፍ አዕላፍት ሆኑ፡፡ በስዊድን ሀገር ለደጋፊዎቿ ‹‹(የቅንጅት አመራሮች) የተፈታነው በሕዝብ ጫና ነው ስላለች ነው›› የሚሉ ድምፆች በረከቱ፡፡ ብዙዎች ግራ ተጋቡ፡፡ ‹‹ታዲያ ይህ ምን ወንጀል ነው?›› ሲሉም ጠየቁ፡፡ ‹‹ኢህአዴግን አስኮረፈ!›› አሉ እናውቃለን የሚሉ፡፡ ፖለቲካ ገብቶናል ያሉ ደግሞ ‹‹መጀመሪያውኑም ሲፈቱ ይቅርታ የተደረገላቸው በቅድመ ሁኔታ ነው›› ሲሉ ተነተኑ፡፡

በዚህ መሀል ያ ሶስት ቀን አለፈ፡፡ ብርቱካንም ‹‹ቃሌ›› ስትል በሰጠችው መግለጫ የጣሰችው ሕግ እንደሌለ፣ ጉዳዩ በይቅርታ እንዲያልቅ ሽምጋይ በነበሩት ሽማግሌዎች ስምምነት ከተፈጠረ ‹‹የፓርቲው መሪዎች ያለ ምንም ገደብ የፓርቲውን ስራ እንደሚቀጥሉ›› ጠቅላይ ሚንስትሩ ቃል መግባታቸውን መናገራቸውን ገልፃ፣ ማስተባበልም ካስፈለገ በሚል ስሜት ይመስለኛል ‹‹…በእርግጥም በዚህ ሰነድ ላይ እኔም እንደ አንድ ታሳሪ መፈረሜን ክጄ አላውቅም፡፡ በሽማግሌዎቹም የዕርቅ ማግባቢያ መንፈስ መሰረት በፖለቲካ የተቀሰቀሰውን ክስ ፖለቲካዊ ዕልባት ለመስጠት በማሰብ ለዕርቅ ስል ከሌሎች የፓርቲው መሪዎች ጋር ተስማምቼ ሰኔ 11 ቀን 1999 ዓ.ም በተጻፈው ሰነድ በሽማግሌዎች አማካኝነት መንግስትን እና የኢትዮጵያ ህዝብን ይቅርታ ጠይቄአለሁ፡፡ ይህ ብፈልግም ልለውጠው የማልችለው ሐቅ ነው፡፡›› ስትል በይቅርታ መፈታቷን እንዳልካደች ገለፀች፡፡ መንግስት ሆዬም ‹‹ቃሌ›› የሚለው የማስተባበያ ቃል በቂ አይደለም አለና አሰራት፡፡ አንዳንድ ታዛቢዎችም ‹‹የታሰረችው ቀጣዩ አመት ምርጫ ስላለ፣ ሊቀመንበር ተደርጋ የተመረጠችበት አንድነት ፓርቲ በምርጫው ለኢህአዴግ ከባድ ተገዳዳሪ ሊሆን ይችላል›› ተብሎ ስለተሰጋ ነው ሲሉ ፃፉ፤ እድል ባገኙት ሚዲያም አፅንኦት ሰጥተው ተናገሩ፡፡

…ጠቅላይ ሚኒስትር መለስም ብርቱካንን ካልፈታችሁ ብለው ጫና ለመፍጠር የሚፈልጉ ዕርዳታ ሰጪ ሀገራት እንዳሉ በገደምዳሜ ከነገሩን በኋላ በዚህ ምክንያት ብርቱካንን እንደማይፈቱ አስረድተው ሲያበቁ ‹‹ከጣማቸው ይቀበሉ፤ ካልጣማቸው በሊማሊሞ ያቋርጡ›› የሚል ይዘት ያለው መልስ ሰጡ፡፡ ብርቱካንም ለዕድሜ ልክ እስራት አሰቃቂው ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ገባች፡፡ ይህን ጊዜም ብዙዎች ከይቅርታው ጀርባ አንዳች ጋኔን እንዳለ ጠረጠሩ፡፡ ጠርጥረው ሲያበቁም ህዝብ የሚያውቀው ‹‹ይቅርታ›› እና መንግስት የሚጠቀምበት ‹‹ይቅርታ›› በትርጉም ለየቅል እንደሆኑ ተረዱ፡፡

## 2003

ብርቱካን ሚደቅሳ ለድጋሚ እስር ከተዳረገችበት እስር ቤት፣ በድጋሚ ይቅርታ የተለቀቀችበት ዓመት ሆነ፡፡ በዚህ ይቅርታ ላይም ‹‹…አሮጊት እናቴን መርዳት ልጄን ማሳደግ ሲገባኝ፤ ዘላለማዊውን ኢህአዴግ ከስልጣኑ እንዲወርድ መሞከሬ እግዜርን የመቃወም ያህል ርኩሰት ነው›› አይነት ያለው ትርጓሜ ያዘለ ይቅርታ እንድትጠይቅ መገደዷን ሰማን፡፡ ዘግየት ብሎም መንፈሰ ፅኑዋ ብርቱካን ሚደቅሳ የአዲሱ የፖለቲካ ስልት ‹‹ሰለባ›› እንደሆነች ገባን፡፡

## 2004

…የአውራምባው ዳዊት ከበደ፣ በ1999 ዓ.ም መጨረሻ ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት በይቅርታ ተፈቶ ሲያበቃ ‹‹አውራምባ ታይምስ›› የሚባል ጋዜጣ መስርቶ የመንግሥትን ገመና የሚገልጡ የተለያዩ ፅሁፎችን ማተም ጀመረ፡፡ ሀገሪቱ ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ታመራ ዘንድም የቻለውን ያህል አስተዋፅኦ አበረከተ፡፡ አድሎአዊ አስተዳደርን፣ የተዛቡ ፍትሆችን፣ የመብት ረገጣዎችን… ተቃወመ-በብዕሩ፡፡ ይህንን አበርክቶት ከግምት ያስገባው ዓለም አቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተከራካሪ ድርጅትም (CPJ) ‹‹የ2011 ዓለም አቀፍ ተሸላሚ›› አድርጎ መረጠው፡፡ …ይህ ከሆነ ከወራት በኋላም ዳዊት ከበደ ‹‹(ያ የፈረደበት) ይቅርታ ሊነሳብኝ እንደሆነ አስተማማኝ መረጃ አገኘሁ›› ብሎ ከሀገር ተሰደደ፡፡ ሌላ ‹‹ሰለባ››ም ይሏችኋል ይህ ነው፣ ሌላ አይደለም፡፡

…እነሆም ማሰር፣ ከአሰሩ በኋላ በይቅርታ መልቀቅ፤ ከለቀቁ በኋላ ደግሞ ይቅርታን አንስቶ መልሶ ማሰር የሚባል ‹‹ፖለቲካ›› ስራ ላይ ከዋለ ድፍን አምስት አመት ሞላው፡፡ ይህ አይነቱ ፖለቲካም ውሎ አድሮ ‹‹የሚያከስር›› ወይም ‹‹የሚያተርፍ›› ተወራራጅ ሒሳብ ያለው የገዥው ፓርቲ ‹‹ተቀማጭ›› ሆነ፡፡ አንዳንዶችም ‹‹በይቅርታ ተቀባዩ አንገት ላይ ተንጠልጥሎ ቀሪ ዘመኑን በሞላ ‹ኪል፣ ኪል…› የሚል ‹ቃጭል› ነው›› ሲሉ ምክንያታዊ ትንታኔ አቀረቡ፡፡ …እኛም በቀጣዩ አንቀጽ የይቅርታ መግለጫዎቹን አጀንዳ አድርገን እንያት፡፡

### የፖለቲካው መንፈስ

የዚህ ትውልድ ፖለቲካ አንድምታ፣ ከያ ትውልድ የፖለቲካ አንድምታ እንደወረደ የተተገበረ ነው፡፡ በመጠፋፋት ሳጋ እና ማገር የቆመ ማለቴ ነው፡፡ ሀቅ ነው! ያ ትውልድ ከፍ ሲል በርዕዮት አለም ልዩነት እርስ በእርሱ ተጠፋፍቷል፡፡ ዝቅ ሲልም ‹‹በቃላት አጠቃቀም›› ተገዳድሏል፡፡ ለምሳሌ አንዱ ‹‹ወዛደር›› ሲል ሌላኛው ‹‹ላብአደር ነው የሚባለው›› ብሎ ጦርነት ሲያውጅበት አይተናል፡፡ ‹‹ኢህአፓ›› የተሰኘው ነውጠኛ ድርጅት ‹‹እናቸንፋለን!›› ሲል በመፈከሩ ብቻ፣ መኢሶን የተባለ ሌላ ነውጠኛ ‹‹አብዮተኛ ‹እናሸንፋለን!› እንጂ ‹እናቸንፋለን› አይልም›› ሲል በፈጠረው የሆሄያት ልዩነት ወደጎዳና ላይ መገዳደል መሸጋገራቸው የትላንት ታሪክ ነው፡፡ በነገራችን ላይ የኢህአዴግ መሪዎችም እንደ ታሪክ ተጋሪዎቻቸው በዛ ዘመን መንፈስ የተቀኙ ናቸው፡፡ መፍትሄያቸውም እንደዚያው ዘመን ነው፤ ‹‹ወይ ከኛ ጎን ቁም፤ አሊያም ጥፋ!›› ለዚህም ነው እግዜሩ ‹‹ኑ እንውረድ ሰውን በምሳሌያችን እንፍጠር›› እንዳለው በራሳቸው (በኢህአዴግ) አምሳያ የተፈጠሩ ማህበራትን እንደእንጉዳይ ያፈሉት፡፡ የኦሪቱ ቃልንም በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ቀይረው እንዲህ ያሉት ‹‹ኑ እንታገል ኢትዮጵያውያንንም፣ ኢትዮጵያንም በምሳሌያችን እንፍጠር››፤ እነሆም ቃሉን የሰሙ፣ ሰምተውም በልባቸው ያሳደሩ ‹‹የሰራተኛ ማህበር፣ የመምህራን ማህበር፣ የሀኪሞች ማህበር፣ የጋዜጠኞች ማህበር፣ የነጋዴዎች ማህበር፣ የአርቲስቶች ማህበር፣ የሸማቾች ማህበር…›› ተፈጠሩ፡፡ ለዚህም መሰለኝ የዛሬ ሃምሳ አመት የነበረው ‹‹የዲሞክራሲ›› እና ‹‹የሰብአዊ መብት›› ጥያቄ ዛሬም ዋነኛ አጀንዳ ሆኖ ሀገሬን ያሉ እየታገሉለት ያለው፡፡ በጥያቄው ላይ ያለው ልዩነት ‹‹የአፄ ኃይለ ሥላሴ የብዝበዛ አገዛዝ…›› የሚለው ‹‹የአቶ መለስ ዜናዊ አምባገነናዊ አስተዳደር…›› በሚል መተካቱ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር የማይካደው ልዩነት ይህ ትውልድ እንደ ‹‹ያ ትውልድ›› በፖለቲካ ልዩነት አውሮፕላን አይጠልፍም፤ ለሃሳብ ተቃርኖም ነፍጥ አያነሳም፡፡ ይህ ማለት ግን ስርዓቱ ተቀናቃኙን በትውልዱ የትግል ስልት እየገጠመው ነው ማለት አይደለም፡፡ እንዲህማ ልንል አንችልም፡፡ ምክንያቱም ከ‹‹ቀይ ሽብር›› ማፋፋም አንስቶ ‹‹አሸባሪ›› ብሎ በፍርድ ቤት ወንጅሎ ቃሊቲ እስከ ማውረድ የሚደርሱ መንግሥታዊ ምላሾችን እያየን ነውና፡፡

እዚህ ጋ መነሳት ያለበት ቁም ነገር አለ፡፡ ይኸውም ተቀናቃኝ ወይም ተቃዋሚ ላይ የአፄው መንግሥት የተሻለ ርህራሄ እንደነበረው ነው፡፡ አፄው ግዙፍ ተቃውሞዎችን ሳይቀር ለረጅም ጊዜ ታግሰው አልፈዋል፡፡ አንዳንዴም በ‹‹አስለቃሽ ጢስ››፤ አልፎ አልፎም ‹‹ዱላ›› ብቻ በያዘ ፖሊስ ችግሩን ለመፍታት ይሞክሩ ነበር፡፡ በአፄው ላይ ተማሪዎችን እና ሠራተኞችን ካነሳሱት ውስጥ አንዱ የሆነው የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) መስራች እና ዋና ፀሀፊ የነበሩት አንዳርጋቸው አሰግድ ‹‹በአጭር የተቀጨ ረጅም ጉዞ›› በሚል ርዕስ በፃፉት መጻሕፍ ላይ፡-

‹‹በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን ‹ምኅረት፣ ግዞት፣ የቁም እስር፣ አምባሳደርነት ሾሞ መላክ፣ ከሹመት አግልሎ ማቆየት…› የፖለቲካ ተቃዋሚዎች አያያዝ መንገዶች ነበሩ፡፡ እርሳቸውን የተኩት ሁለቱ መንግሥቶች ወሬውንም የሰሙ አይመስሉም፡፡ ብቻ ደግሞ ‹ምኅረት…ወዘተ› የመንግሥት ጥንካሬ ምልክት ተደርጎ መታየት የለበትም፡፡ የሚያመላክተው ተቃራኒውን ነው፡፡ ሆኖም ግን እንደዚያ ያለው መንግሥት ከገዳይና በእስር ከሚያበሰብስ መንግሥት ይሻላል›› ሲሉ የሰጡት ምስክርነት አንድ ማሳያ ሊሆን ይችላል፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ ፕሮፌሰር አንድሪያስ እሸቴም ባለፈው ቅዳሜ ከሸገር ራዲዮ ጣቢያ ጋር ባደረጉት ቃለ-መጠይቅ ላይ ‹‹አፄ ኃይለሥላሴ ተቃዋሚዎቻቸውን ልጆቼ ናቸው ብለው ያስቡ ነበር›› ያሉት ሌላ ማረጋገጫ ሊሆን ይችላል፡፡ በእርግጥ አንዳርጋቸው አሰግድ ‹‹ሁለቱ መንግስታቶች ወሬውንም የሰሙ አይመስሉም›› ሲሉን፤ ወሬውን የሚያውቁት አንድሪያስ እሸቴ ደግሞ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ ሆነው እያለ ‹‹ተቃዋሚዎችን እንደ ልጆችህ ተመልከት›› ብለው አለመምከራቸው በፕሮፌሰሩ ላይ ያለውን ምፀት ይበልጥ ያጎላዋል፡፡ የኩነናው ባለድርሻም ያደርጋቸዋል፡፡

## ይቅርታ ወይስ…

በ1996 ዓ.ም ወርሃ ሚያዚያ የወጣው ‹‹ነጋሪት ጋዜጣ›› የይቅርታን አዋጅ የሚመለከት እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ነገር ግን አዋጁ በክፍል 3፣ አንቀጽ 16 ላይ ‹‹የይቅርታ ዓላማ የህዝብን ደህንነትና ጥቅም ማስከበር ነው›› ከማለቱ ውጭ ስለይቅርታ ምንም አይነት ማብራሪያ የለውም፡፡ የሚያተኩረውም በይቅርታ አቀራረብ ሥርዓት ላይ ነው፡፡

ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ በሚወጡ አዋጆች ላይ ካሉ መሠረታዊ ችግሮች አንዱ ይህ ነው፡፡ ያልተብራሩ ወይም ግልፅ ያልሆኑ ሀሳቦችን አጭቆ ማቅረብ፡፡ ይህ ደግሞ ለትርጉም አሻሚ ይሆንና ብዙ ክፍተት ይፈጥራል፡፡ በይቅርታ አዋጁ ላይም ‹‹ይቅርታ›› ማለት ምን ማለት እንደሆነ አልተገለፀም፡፡ ወይም ይቅርታ የተደረገለት ሰው ሊነፈግ ስለሚችለው መብት አልተዘረዘረም፡፡ ለዚህም ነው በኢትዮጵያ በተለይም ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ ታስረው በይቅርታ የሚፈቱ ዜጐች፣ የተሰጣቸው ይቅርታ ሙሉ ነፃነትን የሚያጎናፅፍ ሳይሆን፣ በተንቀሳቀሱ ቁጥር ‹‹ኪል፣ ኪል…›› እያለ ‹‹ቀይ መስመር›› መኖሩን የሚያስታውስ ባንገት የሚጠለቅ አስደንባሪ ‹‹ቃጭል›› እንዲሆን ያደረገው፡፡ ልክ በምርጫ 2002 ዕለት ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው ‹‹ምርጫው እየተጭበረበረ›› ለመሆኑ ማስረጃ እንደደረሳቸው ተናግረው ሳይጨርሱ፣ በምርጫ 97 ማግስት የተጠለቀላቸው ‹‹ቃጭል›› መደወሉን ተከትሎ በኢቲቪ ያስተባበሉት አይነት ማለት ነው፡፡ አዲሱ ምህዳር ማጥበቢያ-የይቅርታ ፖለቲካ ማለትም ይህ ነው፣ ሌላ አይደለም፡፡

## ይቅርታ ማለት ምንድር ነው?

የ‹‹ከሳቴ ብርሃን ተሠማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት›› ይቅርታ ለሚለው ቃል አቻ ትርጉም ‹‹አንድ ነገር ሲሳት ወይም በንግግር ማኻል አንድ ነገርን ጣልቃ ከተደረገ በኋላ ለማድረግ ይቅርታ ማለት ነው›› ይላል፡፡›› መቼም ለዕድሜ ልክ ፍርደኞች የተሰጠው ይቅርታ በዚህ የሚገለፅ ነው ባንልም ‹‹ይቅርታ›› የምትለዋን ቃል ግን ትንሽ ሰፋ ያደርጋታል፡፡ ምክንያቱም በሀገራችን ይቅርታ በገዥዎችም፣ በተገዥዎችም መካከል የነበረ እና ሀገሪቷን ከመፈራረስ አግዶ ያቆየ ባህል ነው፡፡

እናም ‹‹ይቅርታ›› እንዲህ በአዳዲስ ብልቶች ተከፋፍሎ ትርጉሙ ከመየቀሩ በፊት የቆየ ባህል ነበር፡፡ ይህ አንድ እውነት ነው፡፡ ኢህአዴግን መደገፍ መብት የሆነውን ያህል፣ አምባገነንነቱንና ሙሰኛነቱን መቃወም መብት መሆኑ ደግሞ ሌላ እውነት ነው፡፡ ስለዚህም ገና ለገና ‹‹የአይናቸው ቀለም አላማረኝም›› እየተባለ አንዱን ‹‹ሽብርተኛ›› ሌላውን ‹‹ተላላኪ›› እያሉ ወንጅለውና ፈርደው ሲያበቁ ‹‹ይቅርታ›› በሚባል እጥን አጥኖ ማንነትንም ሆነ ሞራልን ማምከን፤ ቀን ከሌሊት እንቅልፍ አሳጥቶ የሚያሳድረውን ያንን ‹‹የቁጣ ቀን›› መምጫ ዕድሜ ከማሳጠር ባለፈ ጠቀሜታ የለውም፡፡ በይቅርታ የሚለቀቅ እስረኛም በገደብ እንደተለቀቀ ተደርጎ ‹‹ይቅርታህ ሊነሳ ነው›› የሚለው ጨዋታም አትራፊ አይደለም፡፡ ምንአልባት አገሪቱም ፖለቲካውም የኢህአዴግ ነው ወደሚል ግልፅ አምባገነንነት ካልተሄደ ማለቴ ነው፡፡

የሆነ ሆኖ በኢትዮጵያ አብዮታዊ ዴሞክራሲን ‹‹እንደግል አዳኝ›› አድርጎ ለመቀበል አይነተኛ መፍትሄ ሆኖ እየወጣ ያለው ተቃዋሚዎችን እና ነፃ ጋዜጠኞችን ማሰር፤ ከአሰሩ በኋላ

ወደ ገፅ 6 ዞሯል »

# ኑ በአማርዝኛ እንነጋገር!



በድሉ ዋቅጅራ (ዶ/ር)

አማርኛን ፈልቅቆ ቢገባ የማይፈረድበት ቃል ሊኖር ይችላል። አንዳንድ ጽንሰ ሃሳቦች ከባህላችን ባዳ፣ ለዘመናዊ ኑሮአችን እንግዳ ይሆኑና ለአማርኛ ያስቸግራሉ፡ ፡ እንዲያ ሲሆን የእንግሊዝኛ ቃል አያስደንቅም፤ አቻ ቃል ከአማርኛ እስኪገኝ። ነገር ግን "የህዳሴን ዳም"፣ "የኢትዮጵያን ማፕ"፣ "ለወጣቱ የሚሰጠው ትሬኒንግ" ቢባል "አማርዝኛ ነው" ከማለት ውጪ ምን ይባላል!

## መቼም ቋንቋ ሲነውር ህሊናን ያደማል እንጂ ጥይት ተኩሶ አያቆስል!


/ካለፈው የቀጠለ/

ባለፈው ሳምንት በአዲስ አበባ ከተማ ሁለንተና ላይ የሚታየውን የቋንቋ አጠቃቀም አስመልክቼ መፃፍ ጀምሬ ነበር፡ ፡ እነሆ ዛሬ ጉዳዬን እቋጫለሁ። ባለፈው ሳምንት የተለየ ትኩረት አድርጌ የነበረው "በማስታወቂያ" ሰሌዳዎች ላይ ነበር። ግን በየመንገዱ ዳር በእንግሊዝኛ እና በአማርዝኛ ተጽፈው የተሰቀሉት ነገሮች ማስታወቂያ ናቸው? ሊሆኑ አይችሉም። ለምን ቢሉ ማስታወቂያ አንድን ነገር ያስተዋውቃል፤ የሚገልጸው የሚያግባባው ነገር አለ። አንድ ሙሉ በሙሉ በእንግሊዝኛ ወይም በአማርዝኛ የተጻፈ "ማስታወቂያ" ለማን ነው ጉዳዩን የሚያስታውቀው? እነዚህ ጽሁፎች ማስታወቂያ ያለመሆናቸውን ለማሳየት መረጃ ልጥቀስ።

በአንድ ወቅት በሸገር የኤፍ ኤም የሬድዮ ጣቢያ በሚተላለፍ "ከቤት እስከ ከተማ" በተሰኘ ሳምንታዊ ፕሮግራም የመንገድ ዳር ማስታወቂያዎችን በተመለከተ አንድ ጥናታዊ ዳሰሳ ቀርቦ ነበር። በዚህ ዳሰሳ እንደተገለጸው ከመስቀል አደባባይ እስከ ቦሌ ድልድይ ከስድስት መቶ በላይ ማስታወቂያዎች በተለያየ መጠን በመንገዱ ግራና ቀኝ ተሰቅለዋል። ከነዚህ ውስጥ ወደ ዘጠና ከመቶ የሚሆኑት በእንግሊዝኛ የተጻፉ ናቸው። በተለይ ደግሞ ከመስቀል አደባባይ እስከ ደንበል የገበያ አዳራሽ እና ከፒኮክ እስከ ቦሌ ጫፍ ባሉት የጎዳናው ክፍሎች በሚገኙ 205 ማስታወቂያዎች ላይ ተደረገው ዳሰሳዊ ጥናት እንደሚያሳየው፣ በነዚህ ቦታዎች ላይ ከሚገኙት 205 ማስታወቂያዎች ውስጥ አንድ መቶ አርባ አንዱ (69 ከመቶ) በእንግሊዝኛ፣ የተቀሩት ስልሣ አራቱ /31 ከመቶ/ በአማርኛ የተጻፉ ናቸው። የሚገርመው ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ከተፃፉት ስልሣ አራት ማስታወቂያዎች ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት /52 ከመቶ/ አማርኛውን በእንግሊዝኛ የፃፉ ናቸው። ከስልሳ አራቱ ማስታወቂያዎች ውስጥ በአማርኛ ቋንቋና ፊደል የተፃፉት አስር በመቶ የሚሆኑት ብቻ ናቸው። እና የነዚህ ጽሁፎች አላማ ማስታወቅና መረጃ መስጠት ከሆነ እንዴት ሁለት መቶ ሺህ የማይሞላው መጤ /ኢትዮጵያዊ ያልሆነ/ 69 ከመቶ የሚሆነውን ድርሻ ይወስዳል? እስቲ አሁን አንድ ከአምስት የማይበልጡ ኮምፒውተሮችን የያዘ ኢንተርኔት ካፌ በእንግሊዝኛ ቤቱን የሚያህል ማስታወቂያ በራፉ ላይ ማቆሙ ቤቱን ከፀሀይ ለመከለል ካልሆነ በቀር፣ ከመጤዎቹ ጋር ለመግባባት፣ ኢንተርኔት ቤቱን ለእነሱ ለማስተዋወቅ አስቦ ነው? ማለቴ አስበው የሰሩት ከሆነ።

ሙሉ በሙሉ በእንግሊዝኛ የተፃፉትን ለምሣሌ እንደ ጃሉድና ናቲ የሙዚቃ ድግስ ማስታወቂያ አይነቶቹን / በነገራችን ላይ የት እንደሆነ አሁን ትዝ ባይለኝም የጃሉድ አንድ ማስታወቂያ በአማርኛ ተጽፎ አይቻለሁ/፣ የተማረው እንግሊዝኛውን፣ ያልተማረው የፊደል አጣጣሉንና የቀለም ውህደቱን አድንቆ ሊያልፍ ይችላል። በጣም አንጉል የሚያደርገው ግን በአማርኛ ፊደል የተጻፈው እንግሊዝኛ እና በእንግሊዝኛ ፊደል የተፃፈው አማርኛ ነው።

የአንድ ህንፃ ወይም ካፌ ባለቤትስ እሺ በቃ ውቃቢው ስለወደደው ወይም ስንት ጊዜ ሞክሮ ቪዛ ስለተከለከለ "ዋሽንግተን" ብሎ ህንፃውን ወይም ካፌውን ሊሰይም ይችላል። እኔ የሚገርመኝ ለቋንቋና ባህል መጠበቅ ሀላፊነት ያለባቸው አካላት





ከላይ ኮፒ አድርጌ ያስቀመጥኩትን የግብዣ ወረቀት ተመለከታችሁት? አይገርምም?! የአዲስ አበባ ወጣቶች ማኅበር በንባብ ልምድ አለመኖር ልቡ አዝኖ ችግሩ እንቅልፍ ቢነሳው አንድ ዝግጅት አዘጋጅቶ የጋበዘበት ወረቀት እኮ ነው! ታዋቂ ደራስያንንና አርአያ ይሆናሉ ያላቸውን ጋብዞ ለወጣቶች እንዲያነቡ ሲያደርግ የጥሪ ወረቀቱ ሙሉ በሙሉ በእንግሊዝኛ የተፃፈ ነበር። ‹‹ምናልባት የማህበሩ የስራ ቋንቋ እንግሊዝኛ ይሆናል›› አለኝ አንድ ወዳጄ። ለወጣቱ ሁለንተናዊ ጤንነት ሃላፊነት ያለበት ማህበር ይህችን ፈተና ሲወድቅ ማየት አያናድድም። ለነገሩ ለአፍሪካ ዋንጫ ያለፈው የሴቶች ብሔራዊ ቡድናችን ታንዛንያን አሸንፎ ሲመጣ፣ አዲስ አበባን የዞረበት ግልጽ መኪና የተሸፈነበት ጨርቅ ላይ የተጻፈው ጽሁፍ ሙሉ በሙሉ እንግሊዝኛ አልነበረ!? እኔ ያየሁት በኢቲቪ ስለሆነ ካሜራው ባላነሳው በኩል በአማርኛ ተጽፎ ይሆናል ብዬ ጉመዠሁና አንድ በቦታው የነበረ ሰው ደውዬ ብጠይቅ "አይ ሁሉም በእንግሊዝኛ ነበር፣ አሪፍ አይደል!" አለኝ "በጣም" ብዬው ስልኩን ዘጋሁት፡ ፡ በዚያን ወቅት ያየሁት በአማርኛ የሆነ ነገር ባንዲራችን ብቻ ነው። ተጫዋቾቹ የያዙት ያው በአማርኛም፣ በአፋርኛም፣ በኦሮምኛም፣ በትግሪኛም፣ ... በእኛ ቋንቋዎች ሁሉ ሲተረጉም "አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ የሆነውን ሰንደቅ አላማችንን ነው። ምን እንደናፈቀኝ ታውቃላችሁ? ደግሞ እንደናፈቀኝ አይቀርም፤ አንድ ቀን አንዱ ባለ ህንፃ፣ ወይ ባለ መአት ኮከብ ሆቴል ግራጫ፣ ነጭና ቡላ ባንዲራ ደጁ ላይ ሰቅሎ፣ ‹‹የኢትዮጵያ ባንዲራ በእንግሊዝኛ ሲተረጉም ይህን ይመስላል›› ካላለ ምን አለ በሉኝ።"

አንዳንድ ሰዎች "ኧረ ችግሩ ስር ሳይሰድ፣ ይህ አማርኛን በእንግሊዝኛ መተካት፣ ወይ መደባለቅ መላ ይፈለግለት" ይላሉ። እኔ ግን "ኧረ የምን ስር መስደድ አመጣችሁ! በደንብ ለምልሞ ፍሬ እያፈራ ነው" እላለሁ። አንድ ሰው ለአማርኛ የንባብ ዝግጅት፣ በእንግሊዝኛ መጥሪያ ሲጽፍ፣ ብሔራዊ ቡድኑን በእንግሊዝኛ መፈክር ሸፍኖ ከተማ ሲያዞር፣ ምንም ካላደናቀፈው፣ ነውረኝነት ካልተሰማው፣ ጭራሽ ኩራት ከተሰማው ችግሩ ስር ከመስደድ አልፎ ለፍሬ ለመብቃቱ እማኝ የሚሆን ይመስለኛል።

ስር የሰደደው ገና ድሮ ነው፡ ፡ መሪዎቻችን በየአለማቀፍ ስብሰባው በእንግሊዝኛ ሲናገሩ፣ ጋዜጠኞቻችን በዜና መሀል ሳይቀር በሚጠቀሙት እንግሊዝኛ

ወደ ገፅ 10 ዞሯል

# በሕግ መዳኘት እያለ...

ሊሆን እንደሚችል ወይንም እንደሚገባ በግልጽ አስፍሯል።

አንቀጽ 9(7) ‹‹ቦርዱ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (5) በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ የምዝገባ ማመልከቻ ያቀረበውን የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ ህግ መሰረት እንደመዘገበው ይቆጠራል›› በማለት ራሱ አዋጁ የምዝገባ ጥያቄ ላቀረበው ፓርቲ ሕጋዊነትን ያጎናጽፈዋል። እንደሰማነው ሠማያዊ ፓርቲም ይህን አንቀጽ መሰረት በማድረግ ሕጋዊነቱን አውጇል።

ቦርዱ ከላይ በተገለጹት የአዋጁ አንቀጾች መሰረት የሰማያዊ ፓርቲን ጥያቄ ውድቅ አድርጎ በጽሑፍ አልገለጸም የምዝገባውን ፎርማሊቲ አጠናቅቆ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ የምስክር ወረቀቱን አልሰጠም። እንደውም ቦርዱ እንዳልወሰነና ሰብሳቢው ገና ለውሳኔ ሊያቀርቡ እንደሆነ ነው ከፍትህ ዜና ያነበብነው። ከአምስት ወራት በላይ ውሳኔ ያልሰጠው ቦርድ አሁን ውሳኔ ለመስጠት የትኛውን የአዋጁን አንቀጽ መሰረት እንደሚያደርግ የምንሰማው ይሆናል። አዋጁ ሕጋዊነት የሰጠውን ፓርቲ ሕጋዊ አይደለህም የሚል ውሳኔ ላይ ይደርሳል ተብሎ ግን አይታሰብም። ቦርዱ ከአዋጁ በላይ አይደለምና።

ይህም ብቻ አይደለም ቦርዱ የሠማያዊ ፓርቲን ሕጋዊነት አልቀበልም። የምሥክር ወረቀትም አልሰጥም ለማለት የሚያስችለው የአዋጅ ክፍል አለ። አንቀጽ 11። አንቀጽ 11 ‹‹የሚከተሉት ድርጅቶች ወይንም ማሕበራት በዚህ አዋጅ መሠረት በፖለቲካ ፓርቲነት ሊመዘገቡ አይችሉም የሚላቸው

1. በንግድ ሕግ ወይንም በፍትሐ ብሔር ሕግ ወይም አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የንግድና ኢንዱስትሪ ስራዎችን ለማከናወን የተቋቋሙ ማህበሮች ወይም ድርጅቶች፣
2. ዓላማቸው ትርፍ ለማግኘት ያልሆነ ወይም ለበጎ አድራጎት ተግባር የተቋቋመ ማሕበራት ወይም ድርጅቶች
3. የብዙሃን የሰራተኛና የሙያ ማህበራት
4. የመረዳጃ ማህበራት
5. የሃይማኖት ድርጅቶች
6. እድርና ዕቁብን የመሳሰሉ ማሕበራዊ ተቋሞች ናቸው።

ከእነዚህ ውስጥ ሰማያዊ ፓርቲን የሚመለከቱ ስለመኖራቸው በተደጋጋሚ በሀገር ውስጥና በውጪ ራዲዮኖች የተደመጡት የቦርዱ የሕዝብ ግንኙነት ዋናና ም/ል ኃላፊዎች ሲናገሩ አልሰማንምና ቦርዱ አልመዘግብም የሚልበት ሕጋዊ ምክንያት ያለው አይመስለኝም።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የአዋጁ አንቀጾች ከአንቀጽ 8 (ሠ) በስተቀር ግልጽ ናቸው። በአንድ አዋጅ ውስጥ መቼ እንዴትና በማን ተፈጻሚ እንደሚሆኑ በግልጽ ያልሰፈሩ አንቀጾች ተብራርተው የሚቀርቡት በመመሪያና ደንብ መሆኑ ቢታወቅም ከዜና አውታሮች የምንሰማው ቦርዱ የአዋጅ 573/2000 ዓ.ም ማስፈፀሚያ መመሪያ የሌለው መሆኑን ነው። ይህን ቦርዱም አላስተባበለም። እንደውም ምክትል የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ለአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ ሲናገሩ መመሪያ ባይኖርም ቦርዱ ሲከተለው የኖረውን አሰራር ማክበር ያስፈልጋል ነው ያሉት። በሕግ ሳይሆን በዘልማድ እንስራ እያሉ መሆኑንና ከሕግ የሚቃረን ልማዳዊ አሰራር ተፈጻሚነት እንደማይኖረው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መደንገጉን ያወቁ አይመስለኝም።

ይህም ሆኖ ግን ለወራት በዘለቀው የመገናኛ ብዙሃን ዜና እንደተከታተልነው ከሆነ የቦርዱ ጽ/ቤት ኃላፊዎችና የሰማያዊ ፓርቲ አመራሮች የመመሪያና ደንብ ያለመኖር የፈጠረውን ክፍተት ተማምነው በአንቀጽ 8(ሠ) የተገለጸውን ተግባራዊ የሚያደርጉበትን መንገድ ተነጋግረዋል። እንደ ሠማያዊ ፓርቲ አመራሮች ገለጻ ከሆነ ደግሞ በተስማሙበት መሰረት ተፈጻሚ አድርገዋል። ይህ ከሆነ ታዲያ ፍጥጫም ይባል ውዝግብ ምን አመጣው?

ከላይ እንደተመለከትነው አዋጅ 57/2000 ዓ.ም. ለቦርዱ የሚቀርብ የምዝገባ ጥያቄ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ በማይወጡ ግለሰቦች ወይንም ግልጽነትና ተጠያቂነት በጎደለው አስተዳደራዊ አሰራር ምክንያት እንዳይዘገይ የሶስት ወር የጊዜ ገደብ ወስኗል። በዚህም ሳያበቃ ቦርዱ የአዋጁን ድንጋጌ አክብሮ በተሰጠው የጊዜ ገደብ አመለካቹን ፓርቲ የማይመዘግበው ከሆነ ውዝግብም ፍጥጫም ክስና ወቀሳም ሳይከተል አዋጁ ራሱ ሕጋዊ እንደሚያደርገው ደንግጓል። ይህን የመሰለ ግልጽ ድንጋጌ የያዘ አዋጅ እያለ ተመዝጋቢና መዝጋቢ ፍጥጫ ውስጥ ናቸው ተብሎ የመገናኛ ብዙሃን ዜና መሆኑ የሕግ የበላይነትን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው። ሕግን በወረቀት ላይ ከመጻፍ የበለጠ ዋጋ ያለው ተግባራዊ ማድረጉ ነውና።

ጉዳዩ እንዲህ የመገናኛ ብዙሃን ዜና እንደሆነ ከቀጠለ ሰማያዊ ፓርቲ ራሱን ለማስተዋወቅ የሚያስፈልገውን የፕሮፓጋንዳ ስራ ይቀንስለታል። በአንጻሩ በቁጥር ሲነገር እንጂ በስምም ሆነ በተግባር የማናውቃቸውን ከ90 የሚልቁ ፓርቲዎች ሲመዘግብ ኮሽታ ያልተሰማበት ቦርድ ዛሬ ሰማያዊ ፓርቲ ላይ ምንአየ? የሚል ጥያቄም ጥርጣሬም ይፈጥራል። በሕግ አውጪው አካል ጸድቀው በነጋሪት ጋዜጣ የታተሙ አዋጆች ተፈጻሚ የሚሆኑት በኃላፊዎች ፍላጐት ላይ ተመስርቶ ነውን? የሚል ጥያቄም ሊያስነሳ ይችላል። የሚበጀው ግን ለሕግ ተገዢ በመሆን የአዋጁን ድንጋጌዎች ተፈጻሚ በማድረግ ለጉዳዩ እልባት ማበጀት ነው። የዘገየ ፍትሕ እንደተነፈገ ይቆጠራል የሚለውን የሕግ ብሂል ማስታወስም አይከፋም።

# ‹‹ይቅርታ›› የኢህአዴግ ቃጭል...

ደግሞ ፍርድ ቤት ማመላለስ፣ ማመላለስ፣ ማመላለስ... ዳኛ መሣይ፣ ዐቃቤ ሕግ መሣይ፣ ምስክር መሳይ፣ ማስረጃ መሳይ... ብዙ መሣይ ነገሮችን ማዘጋጀት። በመጨረሻም እድሜ ልክ ወይም አስራአምስት እና ሃያ ዓመት እስር መፍረድ። ከፍርዱ በኋላም ‹‹የይቅርታ ጠይቅ›› ግፊትን እንደደራሽ ውሃ በር ተቆልፎበት በተዳከመ እስረኛ ላይ መልቀቅ። አስከትሎም በግፊቱ ለወደቀው አዲሱን ማህተም (ቃጭል) በአንገት አስጠልቆ ቀሪ ዘመንን ለሀገሩ እንግዳ፣ ለሰዉ ባዳ ማድረግና ከሁለት አማራጭ ጋር ፊት ለፊት ማላተም። የመጀመሪያውም አማራጭ ሀገር ለቆ መሠደድ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ኢህአዴግ ሲዘፍን እስክስታ እያስወረዱ አጃቢ አድርጎ ማስቀመጥ ይሆናል ማለት ነው።

በአናቱም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል በፅንፈኝነት የሚናወዝ፣ አቻቻይ ለሆነ አማካይ መንገድ ትዕግስት የሌለው እንደሆነ ይታወቃል። ፖለቲካዊው ስነ-ልቦና ስርዓቱን የሚቃወሙ ዜጐች በታላቅ መከራ ውስጥ ቢያልፍም በገገሯው ቡድን ተገደው እንኳን የሚስማሙባቸውን ጭብጦች ለመረዳት ዕድል አይሰጥም። የተቃወሙትን ይቅርታ መጠየቅ የተንበርካኪነት ተመሳስሎ ተደርጎ ይወሰዳል። ኢህአዴግ ይህን በሚገባ የተረዳ የሚያስመስለው፣ በግፍ ያሰራቸውን ዜጐች በተለያዩ መንገዶች አንገታቸውን እንዲሰብሩ ካደረገ በኋላ በይቅርታ እንዲፈቱ ማስገደዱ ነው። በይቅርታው የሚወጡት ፖለቲከኞችም የደጋፊዎቻቸው መሰረት እንደሚላላ ኢህአዴግ በሚገባ የተረዳው ይመስላል። ፓርቲው ራሱ በብክለቱ ውስጥ የተሳተፈበትን የፖለቲካ ተለምዶት በዚህ መልክ ሊያተርፍበት እንደሞከረ ከላይ የቀረቡት ትርክቶች በበቂ የሚያሳዩም ይመስለኛል።

መቼም ኢህአዴግ በዚህ አያያዙ እስር ቤት ባሉ ፖለቲከኞች እና ጋዜጠኞች፣ እንዲሁም እንደ ሰሞኑ ወሬ ከሆነ ደግሞ የ‹‹ቃጭል›› ማህተም የሚያስሩ ወይም እንዲያስሩ አስገዳጅ አማራጭ የሚቀርብላቸው ዜጐች ቁጥር ከኢኮኖሚ ‹‹እድገቱ›› በላይ መናሩ አይቀሬ ነው። ሁኔታውን አንዳንዴ ሳስበው፣ ሳስበው አቶ መለስ ፓርቲያቸው ለ40 እና 50 ዓመት በስልጣን ላይ እንዲቆይ እየሰሩ ያሉት ሠርክ እንደሚነግሩን ‹‹ልማታዊ መንግሥት›› ሆነው ሳይሆን ‹‹ተቺዎቻቸው››ን እና ‹‹ተቀናቃኞቻቸው››ን በሙሉ እያሰሩ፣ በይቅርታ እየፈቱ ቃጭል አንጠልጥለውባቸው በማሽማቀቅ ይመስለኛል።

የሆነ ሆኖ ከዚህ በኋላ የሚኖረው ትግል ‹‹ቃጭል›› በማሰር እና ‹‹ቃጭል›› አላስርም በሚሉ የነፃነት ፍናወጊዎች መካከል መሆኑ አይቀሬ ነው። ጎበዟ ርዕዮት አለሙ ከቃጭሉ ይልቅ ‹‹ይግባኙን›› መርጣለች። ምንአልባት ‹‹እምቢ ባይነት›› እየመጣ ለመሆኑ ይሄ አንድ ምልክት ሊሆን ይችላል። ሌሎችም አሉ ‹‹ኪል፣ ኪል፣ ኪል...›› የሚል የቃጭል ድምፅን መስማት የማይፈልጉ፡ ፡ ...ብርቱዎቹ እየመጡ ይሆን? ማን ነበር ‹‹ቆንጆዎቹ ገና አልተወለዱም›› ያለው?

ከእንዲህ አይነቱም ‹‹ብቅል›› እና ‹‹ጌሾ›› የሚዘጋጅ ፅዋ ‹‹አውዳሚነት›› በሚጎነጨው ብቻ የሚገደብ ነው ማለቱ ከታሪክ አለመማር ነው። አዜውን የበላው የወጣቶች ጎርፍ ነው። ደርጉንም ያንኮታኮተው ‹‹ወታደራዊ ሳይንስ የማያውቁ›› ተብለው ሲተቹ የነበሩ ተማሪዎች እና አርሶ አደሮች ናቸው። መቼም ከዚህ በላይ ይግባኝ የሌለው የታሪክ ብያኔ የትም የለም። ለዚህም ነው ጋዜጠኞቻችን ‹‹ዜና መዋዕል›› ከመፃፍ ወይም ከማይታይና ከማይዳሰሰው ‹‹ልማት›› የተጣባ ዜናቸው ባለፈ ሀገራዊ ጥቅምን ያቀነቅኑ ዘንድ ግድ የሚላቸው።

መቼም ለሀገራዊ ጥቅም እቆማለሁ ተብሎም፣ መስዋዕትነትም ተሸሽቶ የሚሆን ነገር አይደለም። በተቀረ ከይቅርታው ደብዳቤ ጀርባ በደን እንደተዋጠ ተራራ የተደበቀ አንዳች እንቆቅልሽ ለመኖሩ ግልፅ ነው። ሆኖም ዛሬ ይህ እንቆቅልሽ እንዲፈታልን አንጠይቅም። ነገ ግን ሌላ ቀን ነው። ምናልባትም ነገሩ ሁሉ ‹‹የነጋበት ጅብ ታሪክ››ን መልሶ ሊያመጣ ይችልም ይሆናል፡ ፡ ማን ያውቃል? ድሮ ድሮ በያ ትውልድ የትግል ዘመን፣ ትግላችን በሚባለው መጽሔት ላይ እንዲህ የሚል ግጥም ሠፍሮ ነበር።

‹‹ጉበዝ ዝም አትበሉ

ዝምታ ለበግም አልበጃት

አስራ ሁለት ሆና

አንድ ነብር ፈጃት።››

ይህም እምቢ ባዮች እልፍ እየሆኑ መሄዳቸው አይቀሬ ለመሆኑ ምሳሌ ነው። እውነትም ነው። መኢሶኖች ‹‹የየካቲቱ ገጣሚ›› እያሉ የሚንቆለጳጰሱት ያ ምርጡ ገጣሚ ዮሐንስ አድማሱ ያለውም፡-

‹‹አሉ ቁጢጥ ቁጢጥ፣
በሰማይ ደመና
ከእንግዲህ ቀረች
እንቅልፍና ጤና

መንግስት ብረት እንጂ አይገዛም ልቦና››ም እንዲሁ እውነት ነው። ...ቀጣዩን የከርሞ ሰው ካለን የምናየው ይሆናል።

# ምርጫ 2002ን በምርጫ 97 የሚደጉመው የአቶ በረከት ስምኦን መጽሐፍ



ርዕስ፡- የሁለት ምርጫዎች ወግ
ደራሲ፡- በረከት ስምኦን(አቶ)
የታተመበት ዘመን፡- 2003 (?)ዓ.ም
የታተመበት ማተሚያ ቤት፡- አልተገለጸም
ገጽ፡- 316
ዋጋ፡- 90 ብር
የርዕስ አሰጣጥ፡-
ምርጫ 97 እና የመጻሕፍቱ ትርክት

**በብርሀኑ ደቦጭ**
**(የታሪክ ተመራማሪ)**

የምርጫ 97 ትርክት መንስኤ ስለሆናቸው መጻሕፍት በተለያዩ አጋጣሚዎች ለማውሳት እድል አግኝተናል፡፡ በድጋሚ ስለእነርሱ በዝርዝር ማየት ስለማያስፈልገን ጠቅለል ያሉ ጉዳዮችን በዚህ አጋጣሚ እንመለከታለን፡፡ ከነርሱም ዋንኛው ርዕስ ጉዳያቸው ነው፡፡ የመጻሕፍቱ ፍሬ ነገሮች የምርጫው ሂደት፣ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ጉዞ፣ በተፎካካሪ ፓርቲዎች (ግንባር፣ ንቅናቄ፣ ውህደትና ሕብረቶች) መሃል የነበሩ መተ ጋገሎች፣ ታዋቂ የፖለቲካ መሪዎች የነበራቸው አሉታዊና አዎንታዊ አስተዋጽኦ፣ የፖለቲካና የማህበረሰብ አስተሳሰብ መደላድሎች፣ ምርጫውን ተከትሎ የተፈጠረውን ቀውስ ለመፍታት የተሄደባቸውን ውጣ ውረዶች እንዲሁም የሕግና የፍትህ ሂደቶች፣ የዓለምአቀፉ ማህበረሰብና ዲፕሎማቶች ሚናና የታዛቢዎች ሁኔታ ላይ ትንተና፣ አስተያየትና ግምገማ እንዲሁም ወደፊት ምን ቢደረግ እንደሚሻል ጠቋሚ ሃሳቦች ናቸው፡፡

ሌላው አንኳር ጉዳይ መጻሕፍቱ የተጻፉበት መንፈስ ነው፡፡ በተቃዋሚው በኩል የተጻፉት አመዛኙ በቁጭትና ጸጸት መንፈስ በአቀራረባቸው እንዲህ ቢሆን ኖሮ እንዲህ ባይሆን ኖሮ የሚሉ ናቸው፡፡ አንድን ወገን/ግለሰብን ‹‹ለመከላከል›› አሊያም ‹‹ለማጋለጥ›› በማለም የተዘጋጁ የሚመስሉም አሉ፡፡ እንዲህ እንዲህ እያልን መዘርዘር ከጀመርን ትኩረታቸውን በምርጫው ላይ ባያደርጉም እነ መ/ር ገብረ ኪዳን እና ይትባረክ ግደይ በምርጫው ዙሪያ በተደረጉ እሰጥ አገባዎች ተቆስቁሰው የጻፏቸውን መጻሕፍትም ስለምርጫው ስናነሳ አንድምታቸውን ልንዘነጋው የማይገባ ሊሆንብን ስለሚችል ይቆየን ብለን ብንተወው ይመረጣል፡፡

እጅግ አነስተኞቹ ደግሞ በክስተቱና ተዋንያኑ ዙሪያ ከተደረገው ትረካ ገፋ ባለ መልኩ ሠፋ ያለ ጽንሰ ሃሳብ/መርህን ለማንሳት የሞከሩ ናቸው፡፡ እነዚህ የሚያነሷቸውን (ቢያሳምነንም ባያሳምነንም) ሀሳቦች በተሻለ ደረጃ ማቅረብ የቻሉ ሊባሉ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ የዶ/ር ብርሃኑ (በእስር ቤት ውስጥ መጻፉ ሲታሰብ)፣ የአቶ ልደቱ እና የፕ/ር መስፍን ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ድምዳሜዬ የመጻሕፍቱን ዋና ባህሪ በማሰብ እንጂ በዝርዝር አንዱ ካንዱ የሚወራረሰውና የሚጋራቸው ጠባያት መኖራቸው አይሳትም፡፡

በትንተናም ሆነ በሥራዎቻቸው መግፍኤ ሀሳብ የተለዩ ቢሆኑም በምርምር ተቋማት አካባቢ የተሠሩ ሥራዎችን መጥቀስ ያሻል፡፡ ለምሳሌ የምርጫው ውጤት ያስከተለው ጽልመት ያስጨነቀው አ.አ.ዩ. ዝምታውን ለመስበር ቅድምናውን በመውሰድ በፍሬደሪክ ኤበርት ሽቲፍቱንግ ስፖንሰርነት በተዘጋጀ ውይይት ላይ ከተለያዩ ክፍሎች (ከመንግሥትም ከተቃዋሚዎች ወገንም) የመጡ ተናጋሪዎች ያቀረቡትን አስተያየት አካቶ እ.ኤ.አ በ2009 ያወጣው "Democracy and the Social Question: some contributions to Dialogue in Ethiopia" መጽሐፍ አንዱ ነው፡፡ መጽሐፉ ምን ዓይነት ዲሞክራሲና ከዲሞክራሲና ከኢኮኖሚ ዕድገት ለሃገሪቱ ባሰቸኳይ የሚያስፈልጋት የቱ ነው የሚሉ ጥያቄዎችን ያስተናገደ በመሆኑ፤ በይዘትም ከነገረ ምርጫ 97 መጻሕፍት ጋር የሚጋራው መልክ እንዳለው ይጠቁማል፡፡ ልክ እንዲሁ ምንም እንኳን አዘጋጆቹ መነሻ ዓላማቸው ሌላ ቢሆንም ምርጫ 97 ጥላውን ያሳረፈበት በ2010 እኤአ ‹‹Documenting the Ethiopian Student Movement: An Exercise in Oral History›› በሚል ርዕስ ታትሞ የተማሪዎችን እንቅስቃሴና ወደፓርቲ ፖለቲካ ያደገበትን ሁኔታ ለማጥናት የዘመነኛ ተሳታፊዎችን ትውስታ በ1997 ዓ.ም መጠናቀቂያ ወርኃ ጳጉሜ ላይ እንደወረደ ቀርጾ ለማስቀረት የተጣረበት መጽሐፍም ተጠቃሽ ነው፡፡ ኢህአዴግ አዲስ አበባ በገባ በዓመቱ የቀድሞ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ተዋናዮችን ባገናኘ ሎንዶን (በ1992 እኤአ) ላይ በተዘጋጀ ዝግጅት ያኔ በአዲሱ መንግሥት ውስጥ ያሉትንም ከውጪ ያሉትንም ማሳተፍ ተችሎ ነበር፡፡ የ1992ቱ ዝግጅት አስተባባሪ ነበሩት ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያምን ጨምሮ አዲሱን መጽሐፍ ለማዘጋጀት መሳተፍ የነበረባቸው በምርጫው ሂደት በሁለቱም ወገን ሆነው ይፋለሙ ስለነበር ሳይካተቱ ቀርተዋል፡፡ ከዚህ ውጪ ምርጫ 97 በክስተቱ ክብደት በአገሪቱ ታሪክ የዘመን መለያ ሆኖ ሊያገለግል እንደሚችል ታሳቢ ያደረገውን ‹‹the Quest for Expression: State and the University in Ethiopia under three Regimes, 1952-2005›› መጽሐፍም በኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ላይ የተደራጀ መጽሐፍ የጻፉት ራንዲ ባልስቪክ ከምርጫው ጋር ተያይዞ የነበረውን የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች እንቅስቃሴ አካተው ስላቀረቡበት የምርጫው ወላፈን የነካው መጽሐፍ አድርገን ልንወስደው እንችላለን፡፡

የዛሬው አስተያየቴ መነሻ የሆነኝ የአቶ በረከት ስምዖን ‹‹የሁለት ምርጫዎች ወግ›› መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፉን መመዘን የሚገባን አንድም ጸሐፊው ለርዕሰ ጉዳዩ ካላቸው ቅርበት አኳያ ነው፡፡ በኢህአዴግ በኩል በዚህ ደረጃ ባለ ባለሥልጣን እንደውም በምርጫዎቹ ሂደት መሃል ላይ ግንባሩን ወክለው በዋና ተደራዳሪነት እና የቅስቀሳ ቡድኑን በመምራት የሚታወቁ ሰው መሆናቸውም እሰየው የሚያስብል ነው፡፡ በእርግጥም የመጣበት አቅጣጫ የመጻሕፍቱ ትርክት በአንድ በኩል ብቻ እንዳይሆን ረድቶናል ማለት ይቻላል፡፡ የአቶ በረከት መጽሐፍ በወጣበት ሰሞን የቀድሞ የትግል አጋራቸውን ጨምሮ የተለያዩ ወገኖችን አስተያየት አስነስቷል፡፡ ብዙዎቹ የጭብጥና ዝርዝር ጉዳዮች መዘለል ወይም አለመሟላት ላይ ያተኮሩ ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡ የእኔ አስተያየት ደግሞ ርዕሰጉዳዩ በጸሐፊው ደረጃ እና በተጻፈበት ጊዜ ለመጻፍ ምክንያት ሊሆኑ በሚችሉ ከመጽሐፉ በተገኙ አንድምታዎች ዙሪያ ይሆናል፡፡

ስለምርጫ 97 ብቻ ሊጽፉ እንዳሰቡ የነገሩን አቶ በረከት ለምን ስለሁለቱ ምርጫዎች በአንድ ጊዜ ለመጻፍ ፈለጉ? ለሚለው ጥያቄ በመቅድሙ የገለጹልን ምክንያት አለ (የጊዜና በሥራ የመጠመድ ጉዳይ ነበር-ገጽ7)፡፡ የቀረበው ምክንያት ተቀባይነት ሊኖረው እንደሚችል ይሰማኛል፡፡ ይሁን እንጂ እርሱን ብቻ በቂ አድርጎ መውሰድ እንደማይቻልም ይታየኛል፡፡

የመጽሐፉን ቀልብ መረዳት የቻለ እንደሚገነዘበው መጽሐፉ ስለምርጫ 97 ‹‹የሚያትት›› ክፍል (አንድ) ቢኖረውም አብይ ጉዳዩ ምርጫ 2002 (ክፍል ሁለት) እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡ በሌላ አነጋገር ክፍል አንድ የተጠናቀረው ክፍል ሁለትን ለመገንዘብ/ለማመን/ለመቀበል እንድንገደድ በሚመስል አኳኋን ነበር፡፡ ጸሐፊው በምርጫ 97 ጉዳይ ላይ፣ በተለይም ተቃዋሚዎች ከእስር ቤት ወጥተው በመሃላቸው ክፍፍል መፈጠሩ ሳይገለጥ (ራሱ የእነ አቶ በረከት ቡድን ምን ያህል ለክፍፍሉ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ተለክቶ ባይታወቅም) ቢጽፉት በካውንተር ፋክቸዋል ሂትሪ ትንተና የመጽሐፉ አቀራረብም ሆነ ዓላማው የተለየ ይኾን ነበር ብሎ ማሰብ ስህተት አይሆንም፡፡ ጸሐፊው ድርጅታቸው ከምርጫ 97 ሰቆቃ አገግሞ በቀጣዩ ምርጫ ሁሉንም ሊባል በሚችል መልኩ በሁለቱም ምክርቤት ያሉ መቀመጫዎችን መያዝ ከቻለ በኋላ መሆኑን ልብ እንበል፡፡ እንግዲህ በምርጫ 97 ምርጫ ቦርድ በተቀበለው መጠን ያህል የተሸነፈ ቡድን በቀጣዩ በዚህ ደረጃ ‹‹ማሸነፉ›› ጥያቄ ማስነሳቱ አልቀረም፡፡ ለዚህ ደግሞ ማሳመኛ ምክንያትና ማብራሪያ መስጠት ግድ ቢሆን አይደንቅም፡፡ ማብራሪያው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ግምገማን አስመልክቶ ያለው ሃቲት የሚያመለክተውን ‹‹ፍጹም ወደኋላ የተመለሰ ነው›› የሚል ዕይታ ምን ያህል እንደሚያስታግስ ወደፊት የሚታይ ቢሆንም፤ ለጊዜው ግን የአቶ በረከት መጽሐፍ ይዘት የዚሁ ማብራሪያውን የመስጠት ጥረት አካል መገለጫ አድርገን ልንወስደው እንችላለን፡፡

እንደእኔ እንደእኔ የአቶ በረከት ‹‹የሁለት ምርጫዎች ወግ›› ከማብራሪያም በላይ የሆኑ አንድምታዎችን ያረገዘ ነው ቢባል እመርጣለሁ፡፡ እነርሱም በአገርውስጥና በዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን፣ በተለያዩ የሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት እንዲሁም ተቃዋሚና የሲቪል መብት ተከራካሪ ድርጅቶች የሚነሳበትን ትችት መመከት፣ በዓለምና በአገር ውስጥ ለሚገኙ የግንባሩ ደጋፊዎችና አባላት የሥነልቦና ብርታት ማስገኘት፣ ከዚያም አለፍ ሲል ተጻራሪውን ክፍል ማሳጣት፣ ማንኳሰስ ከተቻለም ማዳከም ናቸው፡፡ በዚህ ጽሑፍ የተወሰኑትን አንድምታዎች ለመቃኘት እሞክራለሁ፡፡

## ምርጫ 97ንና የፈጠረውን መንፈስ ማሳነስ

የአቶ በረከት ስምዖን ‹‹የሁለት ምርጫዎች ወግ›› የመጀመሪያ ክፍል በማሟሻ ወግ ተጀምሮ የቅድመ ምርጫ 97 ሂደት፣ ድምጽ አሰጣጡ፣ ቆጠራውና ውጤቱ እንዲሁም በድህረ ምርጫ ስለተከሰተው ቀውስ የሚያትቱ በድምሩ አራት ምዕራፎች አሉት፡፡ በእነዚህ ምዕራፎች ግንባሩና መንግስት የነበረበትን ሁኔታ (በኤርትራ ጦርነት ዙሪያ፣ በኢህአዴግ ውስጥ ስለተፈጠረው ክፍፍል፣ የአርማጊዶን ምልክቶች ስለተሰኙ የከተማ ረብሻና የርሃብ ጉዳይ፣ ከናዳው ለማምለጥ ይረዳል ስለተባለ በፍጥነት የማምለጥ ዘዴ፣ ስለተሐድሶ መጀመር፣ ‹‹እንከን የለሽ ምርጫ›› ለማካሄድ ስለተወሰነበት ምክንያት) የሚዘረዝር ሲሆን፤ በአንጻሩ በምርጫ ክርክሩ በተቃዋሚው በኩል መንግሥትን የማጥላላት ዘመቻው፣ ስልጣን በአመጽም ቢሆን ለመያዝ የመፈለግ አዝማሚያው ኃላፊነት የጎደለው መነሻ ያላቸው እንደነበረ ተሰምሯል፡፡ ሁለቱ የሚያዝያ ሠልፎች፣ በድምጽ መስጫው ቀን የተከሰተው፣ መንግስት ‹‹የተጋጋለውን ስሜት ለማብረድ›› የወሰነው ሰላማዊ ሰልፍ ክልከላ፣ ስላልታሰበው ውጤት፣ የቅንጅት አገር ለመምራት የማይችል መሆን፣ የሰኔው ግጭት፣ የፓርላማ የመግባትና ያለመግባት ጉዳይ፣ የዶ/ር ብርሃኑ ከንቲባነት፣ የታዛቢዎች ሪፖርትና የመሳሰሉትም ተነስተዋል፡፡

ጸሐፊው አቶ በረከት አንድግለሰብ ቢሆኑም (በአርትኦትና በመሳሰሉት የተሳተፉትን የግንባሩን አባላት መጥቀሳቸውን ልብ ይሏል) ይህ ክፍል የግንባሩን ተቋማዊ ስነልቦና ቁልጭ አድርጎ ያሣያል፡፡ ግንባሩ ሕይወቱና እጣፈንታው የአገሪቱን ሕይወትና እጣፈንታ ፍጹም ወሳኝ እንደሆነ አድርጎ ያቀርባል፡፡ አርማጌዶንና ከናዳው ለማምለጥ ይደረግ የነበረው ጉዞ ትንተና የሚያሳየው ይሄንኑ ነው፡፡ ግንባሩ በፖለቲካ ትክክለኛነቱ ነቅ እንደሌለበት ሆኖ እንደሚቀርበው ሁሉ፤ ተቃዋሚዎች ለሥልጣን፣ ዲፕሎማቶች በገርነት የለመዱትን ጥምዘዛ ለማስፈጸም፣ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ገንዘብ የሚሰጧቸውን አካላት ፍላጎት ለማስፈጸም የሚሯሯጡ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

ይህ አይነቱ አቀራረብም በምርጫ 97 (ቢያንስ እስከ ድምጽ መስጫው ቀን) የተፈጠረውን አዝማሚያ አዎንታዊ ገጽ ፍጹም ሽምጥጥ አድርጎ የሚክድ ነው፡፡ ወታደራዊ መንግስት ከወደቀ በኋላ በኢትዮጵያ አራት ምርጫዎች ተካሂደዋል፡፡ ምርጫዎቹ ዲሞክራሲያዊ ከመሰኘት የዘለለ ፋይዳ ያላቸው አይደሉም በሚል ወቀሳ፣ ዘገባና ጥናት ሲጻፍ መክረሙ ይታወቃል፡፡ በዚህ መጽሐፍ ምርጫ ማድረጉ የሕዝብ ሉዓላዊነት ማረጋገጫ እንደሆነ ስለዲሞክራሲ ለአመል ያህል ካነሱባቸው አጋጣሚዎች በአንዱ ቢመሰክሩም፣ አንድም ጊዜ ቢሆን በምርጫ መሸነፍ እንደሌለበት ከዘረዘረውና በሰኔ 1985 ዓም በምስጢር በተላለፈው የግንባሩ ስትራቴጂ ሰነድ ጋር ለማጣጣም አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ከዚህ ሰነድ የተወሰዱ ይዘቶችን በሽግግር መንግስቱ ወቅት የመንግሥት አማካሪ ሆነው የሠሩት ኤም ቬስታል በጻፉት "Ethiopia: A Post Cold War African State" መጽሐፍ አሊያም 'Ethiopian Register' (3) እ.ኤ.አ 1996 ዓ.ም በታተመው ላይ ሙሉውን የእንግሊዝኛ ትርጉሙን ማግኘት ይቻላል፡፡ በእርግጥም በኢትዮጵያ ምርጫ አማናዊ ዲሞክራሲን ከማስፈን ይልቅ የአስተዳደሩን ሥርዓት ማዳመቂያ ነው በሚል የሚተቹ አስተያየቶች የተለመዱ ናቸው፡፡ ውጤቱ ተቃራኒ ቢሆንም አቶ በረከት እንደጠቀሱት እንከን የለሽ ምርጫ ለማድረግ ሲታቀድ አንዱ አላማ የአገሪቱ(የመንግሥትን) ገጽታ ለመገንባት የታለመ ነበር፡፡ ይህ አለመሆኑም ታላቅ ቁጭት በግንባሩ ውስጥ ስለመፍጠሩ ምልክቶቹ በርካታ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ጸሐፊው አገሪቱን እየቀየረ ነው ያሉት የለውጥ ተሐድሶ ስር ሳይሰድ ምርጫ 97 የመጣ መሆኑ፣ በምርጫ ክርክሩ በቂ ዝግጅት ሳይደረግ የተገባ መሆኑና የሚያዝያው ሰልፍ ሁኔታ በቁጭት የሚታወሱ የገገሯው ግንባር መጥፎ ቅዠቶች መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡ ያም ሆነ ይህ ምርጫ 97 የተለየ እንደሆነ ጭክ ተብሎ ሲወራለት ከርሟል፡፡ ከሌሎቹ የሚለየው ብዙ ነገሮች እንዳሉት ቢነገርም፤ ሁሉንም ወገን የሚያስማማው ግን የሕዝብ ተሳትፎ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህም ሕዝቡ በምርጫው መሳተፌ ልዩነት ይፈጥራል ብሎ የመታመኑ ውጤት (political efficacy) ነው፡፡

በ‹‹የሁለት ምርጫዎች ወግ›› ግን ማንኛውም የተቃውሞ እንቅስቃሴ፣ መነቃቃትና ተሳትፎ ሁሉ በጤናማነት የሚታይ አልነበረም፡፡ ይህንንም የምርጫ 97ን ክርክሮች ‹‹ክርክር ከተባሉ›› በሚል፣ በግንባሩ ላይ የሚነሱ ተቃውሞዎችን ከስክነት ማነስ ጋር በማያያዝ (ገጽ 88) እና በሚያዝያ 97ም በተቃዋሚው ወገን የወጣውን ‹‹ግብታዊ›› በማለት በማጥላላት ያንኳስሳሉ፡፡ አለ የሚባል መልካም ነገር ብለው የሚጠቅሱት ካለ የግንባሩን/የመንግስትን ከውቅያኖስ የሚጠልቅ ትዕግስትና ለጋስነት (የተትረፈረፈ በሚድያ የመጠቀም ዕድል ገጽ 112፣119) ብቻ ነው፡፡ ጸሐፊው ለራሱ ለግንባሩ እንደውጤት ሊቆጠሩ የሚችሉ ነገሮችን ሁሉ ዋጋ ማሳጣታቸውን የተረዱ አይመስልም፡፡ ጥሩ አንባቢ ሊያነሳ የሚችለው አንድ ጉዳይ እንዲህ ግንባሩንም ጭምር ዋጋ ሊያሳጣው የሚችል ነገር ለማድረግ የተገደዱበትን ሁኔታ ማወቅ ነው፡፡ ለዚህ መልሱን ጸሐፊው መጽሐፉ እንዲሸፍን በፈለጉት ጉዳይ ውስጥና በስለምን ትንታኔያችን ውስጥ ልናገኘው እንችላለን፡፡ መጀመሪያ ምርጫ 97 ላይ ጸሐፊው መጀመሪያ ሊጽፉ የፈለጉ መሆኑን ስናስብ፤ ግንባሩ ስኬታማ አልነበርሁባቸውም የሚላቸውን ዓመታት የሚሸፍን በመሆኑ፤ ለጸሐፊው የተመቸ አይመስልም፡፡ በዚህ ክፍል በተለይ ምርጫውን ተከትሎ የነበሩት ሁለት አመታት የጣር ጊዜ የነበሩ ሲሆን፤ ኢህአዴግ ከፋም ለማም በዲሞክራሲ ዙሪያ ገንብቶት የነበረው ስምና ዝና ክፉኛ የተናደበት ነበር፡፡ ለዚህም ነው፣ የአቶ በረከት ስዩም መጽሐፍ ክፍል አንድም ይህን ለግንባሩ ‹‹ጳላሄ›› የሆነበትን እንቅስቃሴ ለማጣጣል ያላንገራገገረው፡፡

በማጣጣሉ ሂደትም ጸሐፊው ለመክሰስ የሚያመቻቸውን ነገር ሁሉ ሲወረውሩ በእሳቸው ደረጃ የማይጠበቅና ራሳቸውንም ስለማሳመኑ በእርግጠኝነት መናገር የማይቻልባቸውን ስሞታዎች ሲደረድሩ ተስተውሏል፡፡ የጂን ሻርፕ ሥራ ትርጉም የሆነው ጽሑፍ በከተማው መገኘቱን (ገጽ 68) በመጋቢትና ሚያዝያ መሃልም የአይ. አር. አይ. ባለሙያ የሆነ ሰው ኢህአዴግን ያገለለ ሰነድ አዘጋጅቶ ሊያፈራርም መጠየቁን (ገጽ 78-81፤ ይሄ ሰው ኢህአዴግ ሳያውቀው ገብቶ፣ ከተቃዋሚዎች ጋር ሲያሴር ከርሞ… ነቃንበት ዓይነት) የአመጽና የቀለም አብዮት እንቅስቃሴ ስለመኖሩ ማረጋገጫ ሆነን የሚሉ ስሞታዎችን ደርድረዋል፡፡ መቼም ይሄንን ግንባሩ ቢያምንበት እንኳን በግል ጥያቄ ሊነሳበት ይገባ ነበር፡፡

## በምርጫ 1997 ምርኩዝነት ለምርጫ 2002 ቅቡልነት መታተር

በምርጫ 97 የሕዝብ ተሳትፎም ሆነ የተቃዋሚዎች‹‹መጠናከር›› የመጥላላቱን ያህል ስለምርጫ 200 የተነገረው ሁሉ እርሱን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ ክፍል

ወደ ገፅ 14 ዞሯል



# በካንጋሮ ፍርድ ቤት የመጨረሻው ፍርድ ሰጪ ማን ነው?



በሙሉነህ አያሌው
muleayalew@yahoo.com

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በኢትዮጵያ መንግሥት እየተወነጀሉ ለፍርድ በሚቀርቡ ሰዎች ላይ እየተወሰደ ባለው የፍትሕ እርምጃ ላይ ተመሳሳይ ነገሮችን ማየት እንችላለን:: ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርበው የፍርድ ሂደታቸው እየታየላቸው የሚገኙ ዜጎች በአብዛኛው (አልያም በአጠቃላይ ማለት ይቻላል) የተቃውሞ ፖለቲካውን የሚመሩ ወጣት ፖለቲከኞች እና የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች ናቸው:: የእነዚህን ፍርደኞችና ተከሳሾች የተወንጃይነት መልክ በአግባቡ በመረዳት የፍትህን ብሉይ ትርጓሜና የአቶ መለስ በፍርድ ቤት ስርዓቱ ላይ ያላቸውን ግዙፍ ተፅዕኖ አሰባጥሮ ማየት ስለጉዳዩ የሚሰጠን ስዕል ይኖራል::

## የሶቅራጠስ መርከብ

ማርቲን ሉተር ኪንግ "Letter from Birmingham Jail" በሚለው ደብዳቤው ላይ ፍትሕ የመጨረሻ ውሳኔዋን እንዴት እንደምታገኝ፣ ለማን እንደምትሰራ እና እንደምታደላ በጊዜው ከደረሰበት የዘር መድሎ አንፃር፡-

‹‹ኢ-ፍትሐዊ ሕጎች የሚደነገጉት አብዛኞቹ ወይም የስልጣን ባለቤት የሆኑ ግለሰቦች ጥቂቶቹ እንዲቀበሉ የሚፈልጓቸውን ነገሮች ለማስገደድ የሚወጡ ሲሆኑ በራሱ ግን ፍትሐዊ እና ተቀባይ ናቸው ተብለው ሊወሰዱ አይችሉም›› ሲል ፍትሕ አልባነት በፍትሕ ስም እንዴት የሕጋዊነት ሽፋን እየተሰጠው እንደነበር ይጠቁማል::

ሌላው የግሪክ ፈላስፋ ፕሌቶ አንድ ፍትሐዊ የሚባል ማኅበረሰብ ሊያሟላ ይገባዋል የሚላቸውን ወሳኝ ነጥቦች ይዘረዝራል:: ከነዚህ መካከል ትምህርት መስፋፋት እንደሚገባው፣ ፈላስፋ ንጉስ መሆን እንዳለበት እና የአርስቶክራሲ መንግሥት ፍትሐዊ ማኅበረሰብን ለመመስረት ወሳኝ መሆናቸውን ያወሳል:: ፕሌቶ የተማረ ማህበረሰብ እና በሞራል ስብዕና ላይ የተገነባ የፈላስፋ መሪ ፍትሕን ማምጣት ይችላሉ የሚል አቋም ነበረው:: ከተሞች የፖለቲካ እውቀትን ከተካኑ መሪዎች ይልቅ የሞራል ልዕልናን የተላበሱ መሪዎች እንደሚያስፈልጓትም ምክንያቶቹን በመግለጽ ያስረዳል::

የታዋቂው የፖለቲካ ምሁር ቶማስ ሆብስ የፍትሕ ምንነት አረዳድ ፕሌቶ የሶቅራጠስን ምይይጥ (Dialogue) ባሰፈረበት "The Republic" በሚለው ድርሳን ውስጥ የተቀመጠው የግሪክ ፈላስፋ ገፀ-ባህሪ ሀሳብ ጋር ይዛመዳል:: ትራሲማከስ የተባለው ይህ ፈላስፋ ‹‹ፍትሕ የሚለውን ቃል በቀላሉ ስንተረጉመው ኃይለኞቹን ለመጠበቅ ሲባል የተቋቋመች መገልገያ መሳሪያ ነች›› ይላል:: ቶማስ ሆብስም ይህንኑ ነው የሚለው:: እንደ ሆብስ ክርክር፤ ማናቸውም በመንግስት ደረጃ የሚወጡ ህግጋቶች ላይ ማኅበረሰቡ ቅራኔ ቢኖረውም የማኅበረሰቡን ጥቅም ያስጠብቃሉ እስከተባሉ ድረስ መተግበር አለባቸው:: በየትኛውም አኳኋን በመንግሥት ደረጃ የሚወጡ ሕግጋቶች በሙሉ ፍትሐዊና ሕጋዊ ተደርገው መወሰድ እንዳለባቸው ይሞግታል:: እንደ ሆብስ አረዳድ ለማንኛውም ነገር የመጨረሻው ወሳኙ አገሪቷን የሚያስተዳድረው ግለሰብ ነው::

ከሆብስ ፍትሐዊ ትርጉም አረዳድ ጋር በተቃራኒው የቆመው ሌላኛው ምሁር ሩሶ (Jean-Jacques Rousseau) ነው:: ሩሶ እንደሚለው ከሆነ አንድ ሕግ ፍትሃዊ ነው ወይም ተቀባይነት አለው የሚባለው ሁሉም ዜጎች በጉዳዩ ተወያይተው፣ ተስማምተው ኃሳባቸውን በሚገባ ካሰፈሩ በኋላ የሚደርሱበትን የጋራ ተግባቦት (Consensus) ተከትሎ የሚመሠረት የሆነ እንደሆነ ብቻ ነው:: በሩሶ እምነት በፍትሕ የመጨረሻው ወሳኙ አካል አብዛኛው የማኅበረሰብ ክፍል መሆን አለበት::

በየጊዜው የነበሩት አረዳዶች ፍትሕን የተለያየ ትርጉም ቢሰጧትም ዋናው ተልዕኮ አብዛኛውን የማኅበረሰብ ፍላጐት (Common good) ማሟላት እስከቻለ ድረስ ብቻ መሆን አለበት በሚለው ብዙዎቹ ይስማማሉ:: ሕግጋት መውጣት ካለባቸው የብዙሃኑን ፍላጐት ማርካት ዋነኛ ተልዕኮ መሆን አለበት ብለው ከሚያምኑ የዩቲሊተሪያኒዝም (Utilitarianism) ፍልስፍና አራማጅ ከሆኑት (በዋናነት ጆን ስትዋርት ሚል) ጋር እስማማለሁ::

በግል ፍትሕ እና ፍትሐዊ ስርዓቱ ለመሪዎቹ መተው አለበት ብዬ አላምንም:: ምን አልባት እነ ፕሌቶ እንደሚሰጉት ሞራል አልባ የፖለቲካ መሪ ስልጣን ላይ ቢወጣ የፍትሕ ትርጉም ማኅበረሰባዊ ፋይዳነቷ ይቀርና ስልጣን መጠበቂያ ብቻ ትሆናለች:: ለዚህም ነው አገርን ከጥፋት ለማዳን ቢያንስ ቢያንስ በሚወጡ ሕግጋቶች ላይ ሩሶ እንደሚለው የአብዛኛው ሕዝብ ልብ ትርታ እና ስምምነት ሊንፀባረቅበት የሚገባው::

በዘመናዊ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ሕግ የማውጣት ስልጣን የተሰጠው ፓርላማ በውስጡ ያቀፋቸው ተወካዮች ሕዝብን እና የሕዝብን ፍላጐት በትክክል ያሟላሉ ብዬ ለመናገር አልደፍርም:: በተቋማቶቻችን ላይ ያለን መተማመኛ በጣም ዝቅተኛ የሚባል ነው:: ፓርላማ ውስጥ በተደጋጋሚ በሚንሸራሸሩ ኃሳቦች ላይ ተገዳዳሪ ሙግቶች እያመጣ የሚሟገት አንድ ግለሰብ ብቻ ባለበት አገር ውስጥ የህዝብን የተለያየ ጥቅምና ፍላጐት የሚያስጠብቅ ሕግ ይጸድቃል የሚል እምነት የለኝም:: በኢትዮጵያ የሕግ-አወጣጥ ስርዓትም በዙፋኑ ዙሪያ የተሰባሰቡ ፖለቲከኞችን ጥቅምና ፍላጐት ለመጠበቅ እንጂ ማህበረሰባዊ ፋይዳ ያለው፣የአገርን ደህንነትን ለመጠበቅ የሚረዱ ናቸው ብዬ በግሌ አላምንም:: የተለየ የፖለቲካ አጀንዳ ይዞ አደባባይ

> የዳኞች አሿሿም ሂደት ላይ የሚያነሱት ጥርጣሬ ነው። ጠ/ሚኒስትሩ የሀገሪቷ ርዕሰ መስተዳደር፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ መሆናቸው ሕገ-መንግሥቱ ይደነግጋል (አንቀጽ 74) ። ከእነዚህ ዋና ዋና ተቋማት በተጨማሪም እጃቸው የዳኝነት አሿሿም ሥርዓቱ ላይም ያርፋል። ስለዳኞች አሿሿም በሚደነግገው አንቀጽ 81 ላይ የጠ/ሚኒስትሩን ሚና በግልፅ ያስቀምጠዋል።

መውጣት በሚያስፈርድበት አገር ውስጥ ሆነን ፍትሕ የጠንካሮቹ መጠቀሚያ አይደለችም ብለን ለመከራከር ሞራሉ አይኖረንም:: ጥያቄው የፍትሕ ስርዓቱ የቱን ማስቀደም አለበት፣ አገርን ወይንስ ዙፋንን መጠበቅ (Nation security or Regime security)? የሚል ነው::

ሶቅራጠስ ሞራል በሌላቸው ፖለቲከኞች አልያም ፈላስፋ ባልሆኑ ግለሰቦች የምትመራን ከተማ በባህር ላይ በምንትሰፈፍ መርከብ ይመስላታል:: ፍትህ የተዛባባትን ከተማ የሰከረ ባለስልጣን ካፒቴን ሆኖ እንደሚመራት በባህር ላይ የተንሳፈፈች መርከብ ትመስላለች:: የመርከቧን ካፒቴን ወደ ወደቡ እንዴት መድረስ እንደሚገባው የሚያማክሩት ሌሎች ግለሰቦች (ፖለቲከኞች) በመርከቧ ላይ ስልጣን ይሰጣቸው ዘንድ የተሳሳተ ምክር በመለገስ መርከቧን ያዋክቧታል:: ወደ ወደቡ እንዴት መድረስ እንዳለባቸው የሚያውቅ አንድ አሳሽ (ፈላስፋ) ብቻ ነው ይላል:: ስለዚህ ይላል ሶቅራጠስ፣ መርከቧ በሰላም ወደወደቡ መድረስ ካለባት ኃላፊነቱ ለዚህ ግለሰብ ሊሰጥ ይገባል::

## ጠ/ሚኒስትሩ- ሕግ-አውጪ፣ አስፈፃሚ፣ ተርጓሚ

በአገራችን የሚሰጠው የፍርድ ሂደት እና ፍፃሜው ተመሳሳይ ነው:: ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በፓርላማ ቀርበው ሪፖርት በሚያቀርቡበት ወቅት ቀጣይ ተረኛ ታሳሪ በየትኛው እንቅስቃሴ ላይ እየተሳተፈ እንደሚገኝ ፍንጭ ይሰጣሉ:: ፍንጭ መስጠትም ብቻ ሳይሆን ‹‹ብለው፣ ብለው፤ መክረው፣መክረው›› እንቢ ያሉ ቡድኖች መሆናቸውንና ከየትኛው ድርጅት አካባቢም እንደሆኑ ስም በመጥቀስ ሁሉ በእልህና በንዴት አቤቱታቸውን ያቀርባሉ:: ይሄኛው የመጀመሪያው የክስ ደረጃ ሲሆን ጠ/ሚኒስትሩ በዚህ ጊዜ የፖሊስን ኃላፊነት ተቀብለው የከሳሽነት ሚናን አልያም የመወንጀልን ኃላፊነት ይወጣሉ::

የጠ/ሚኒስትሩን የንግግር ዱካ ተከትለው የመንግሥት ፕሬስና ካድሬዎቹ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ጉዳዩን እያነሱ ማስተጋባት ይቀጥላሉ:: ጉዳዩን እንዲህ ማራገባቸው አንድም የሰዎቹን መታሰር አይቀሬ መሆኑን ሲያመላክት በሌላ በኩልም ኅብረተሰቡ የክሱ ሂደት ድንገተኛ እንዳይሆንበት በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ግንዛቤ እንዲኖረው እንዲያስችል ያደርገዋል:: ነገሩ በዚህ መንገድ ከተከወነ በኋላ ሁለተኛው ደረጃ ይቀጥላል::

እንደተባለው የጠ/ሚኒስትሩ ቀዳሚ ንግግር ደርዝ ከያዘች በኋላ የተባሉት ግለሰቦች በፖሊስ ተይዘው ወደ ማዕከላዊ ምርመራ ጣቢያ ይወሰዳሉ:: ዳግም ጠ/ሚኒስትሩ ለሁለተኛ ጊዜ በፓርላማ ይቀርቡና የሰዎቹን መታሰር አስመልክተው ከዚህ ቀደም ተጠንቀቁ ብለው ተናግረው እንደነበርና እንቢ የማለታቸው ውጤት እንደሆነ ዲስኩራቸውን ያሰማሉ:: ምን አልባት ፖሊስ በስህተት እንዳይሆን አንዳንዶቹን ያሰራቸው? እነዚህ ሰዎች በገሃዱ ከሚሰሩት የተለየ ምን አድርገው ነው? የሚለውን ሞራል ነክ ጥያቄዎች ማኅበረሰቡ በማንሳት እንዳይወናበድ ሲሉ ጠ/ሚኒስትሩ ንግግራቸውን ረገጥ እያደረጉ ‹‹ከበቂ በላይ ማስረጃ አለን:: ከበቂ በላይ፡ ፡ ህጋዊ ሽፋን እየተጠቀሙ የራሳቸውን የሁከት ፖለቲካ አጀንዳ ሲያራምዱ፣ ከአሸባሪ ቡድኖች ጋር ሲተባበሩ፣ ገንዘብ ሲቀበሉ አግኝተናቸዋል:: ወንጀለኛ ለመሆናቸው ምንም ጥርጥር የለንም::›› ሲሉ የፍርድ ቤቱን ሚና አስቀድመው ይወስዳሉ:: አሁን ጠ/ሚኒስትሩ ያልተፈቀደላቸውን የዳኝነት ሚና በሕግ-አውጪው ምክር ቤት ውስጥ ሆነው ፤በዳኞች ካባ ፍርዱን ይጨርሱታል:: ከዚህ በኋላ የዳኞቹ ሚና ምን ሊሆን እንደሚችል ለመተንበይ ነብይ መሆን አይጠበቅብንም::

ሕገ-መንግሥቱን ለማስከበር በሚል ሰበብ ሕገ-መንግሥቱን ይንዱታል:: የተከሰሱ ሰዎች መብት (አንቀጽ 20) ላይ ‹‹በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ በተከሰሱበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር፣ በምስክርነት እንዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አላቸው::›› የሚለው አንቀጽ ለማን እንደተፃፈ? እና ማንን እንደሚመለከት? እንድንጠይቅ ያደርገናል:: ሕገ-መንግሥቱ ጠ/ሚኒስትሩን አይመለከትም እንዳንል በአንቀፅ 74 ላይ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣንና ተግባር በሚለው ስር ‹‹ጠ/ሚኒስትሩ ሕገ-መንግሥቱን ያከብራል፣ ያስከብራል›› የሚል ተፅፎ እናገኛለን::ከፍርድ ቤት ብያኔ አስቀድሞ በፓርላማ ፍርድ ይሰጣል::

ከዚህ በኋላ ያለው የፍርድ ቤት ድራማዊ ሂደት ከጉንጭ አልፋ ክርክር የዘለለ ፋይዳ እንደሌለው እንገነዘባለን:: የመጨረሻው ውሳኔ የፍርድ ቤቶች ኃላፊነት ነው ብለን በተስፋ እንዳንጠብቅ ጠ/ሚኒስትሩ ያለስልጣናቸው የፍርዱን ውሳኔ አስቀድመው ጨርሰውታል:: በዳኞች ሕገ መንግስታዊ ነፃነት ላይ በተዘዋዋሪ መንገድ የፖለቲካ ባለስልጣኖቹ ጣልቃ ገብተውበታል::

የአሜሪካ መንግሥት እ.ኤ.አ. በ2010ዓ.ም ላይ የኢትዮጵያ መንግሥት ሰብዓዊ መብት አጠባበቅ ዙሪያ ባወጣው ሪፖርት ላይ የዳኝነት አካላትን ተቋማዊ ነፃነት ጥያቄ ውስጥ የሚገባ መሆኑን የሚያመላክት ሪፖርት አቅርቦ ነበር::‹‹ሕገ-መንግሥቱ የዳኝነት ስልጣን ነፃነት እንዳለው ይናገራል:: የሲቪል ፍርድ ቤቶች በአንፃራዊ መልኩ በነፃነት ስራቸውን የሚተገብሩ ቢሆንም ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ግን በጣም ደካማ፣ ስራ የበዛባቸውና ለፖለቲካ ጣልቃ ገብነት የተጋለጡ ናቸው›› ሲል ኮንኗል::

ይህንን የእስርና የፍርድ ሂደት ተከትሎ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ቡድኖች የተለመደውን ቁጣና ማስፈራሪያ፣ የሪፖርት ጋጋታ ያወጣሉ:: ሂደቱ ተመሳሳይና አሰልቺ ከመሆኑ የተነሳ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አይቸግረንም:: የፍርድ ውሳኔው አልቆ ትንሽ ጫጫታው ጋብ ካለ በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ ጠ/ሚኒስትሩ የምህረት እጃቸውን ዘርግተው በእስረኞች ቀጣይ እጣ ፈንታ ዙሪያ ምን ሊሆን እንደሚችል ለሕዝቡ ፍንጭ ለመስጠት ብቅ ይላሉ:: ‹‹እኛ ማንንም ሰው ያለበቂ ማስረጃ አልያዝንም:: ሁሉም ጥፋተኞች መሆናቸውን ፍርድ ቤቱ አረጋግጦልናል:: የሚገባቸውንም ቅጣት ተቀብለዋል:: ምን አልባት ከጥፋታቸው ተፀፅተው ከሆነ በኢትዮጵያዊነት ባህል እና ሥነ-ምግባር መሠረት ጥፋታቸውን አምነው ይቅርታ ጠይቀው መውጣት የሚችሉበት አሰራር ሊኖር ይችላል›› ሲሉ ምህረት ሰጪም ጭምር እንደሆኑ ያስገነዝባሉ::

ጠ/ሚኒስትሩ ከሕገ-መንግሥቱና ከተቋማዊ ነፃነቶች በላይ ሆነው የሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈፃሚና ሕግ ተርጓሚ ሆነው ይታያሉ:: ሦስቱ የመንግሥት አካላት አንዱ አንዱን የመቆጣጠር ስልጣኑ ከጠ/ሚኒስትሩ በታች ይሆናል:: ይሄ ደግሞ ሕገ-መንግሥት እያላቸው ነገር ግን አምባ-ገነን የሆኑ መንግሥታት ልዩ ባህሪ ነው:: የትኛውም ሕግ-ተርጓሚ አካል ጠ/ሚኒስትሩ ያለሥልጣናቸው ጣልቃ እየገቡ ነው ብሎ የሚከሳቸው አይኖርም:: ከሳሽ፣ ፈራጅ፣ መሃሪም አንድ ግለሰብ ብቻ የሆነበት የፖለቲካ ሥርዓትን የፖለቲካ ተንታኞች ወጥ አምባ-ገነንነት (Totalitarian state) ይሉታል::

## የሌሳው ብኩርና?

ሕገ-መንግሥቱ ‹‹በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማንኛውም የመንግሥት አካል፣ ከማንኛውም ባለሥልጣን ሆነ ከማንኛውም ሌላ ተፅዕኖ ነፃ ነው›› ይላል:: ሕገ-መንግሥቱ በአብዛኛው ሁሉንም ሊያግባቡ የሚችሉ አንቀፆችን በውስጡ ያቀፈ ቢሆንም ተግባር ላይ ሲቀመጥ አገልግሎቱ ኃይል ለጨበጡት ገዢዎች ብቻ ይሆናል:: በተለያዩ የአለም አቀፍ ተቋማት የተሰሩ የጥናት ውጤቶች እንደመሰከሩት ከሆነ ኢትዮጵያውያን መተማመኛ ከሌሏቸው ተቋማቶቻቸው መካከል የዳኝነት ሥርዓቱ ዋነኛው ነው:: ለዚህም በምክንያትነት የሚያነሱት በየጊዜው ለከፍተኛ ፍርድ የሚቀርቡት ዜጎች ላይ ከዳኝነቱ ይልቅ አስፈፃሚው አካል ቀድሞ ፍርድ የሚሰጥበት አካሄድ መሆኑ አንዱ ሲሆን በዳኞቹ የአሰለጣጠን እና አሿሿም ላይም ጥርጣሬ የሚያጭሩ መከራከሪያዎች አሉ::

ይህንን ጥርጣሬ የሚያጭሩ ግለሰቦች ሁለት መሠረታዊ ነጥቦችን ያነሳሉ:: ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ሌሎችም የዳኝነት ወንበር ላይ የሚሰየሙት ዳኞች በአብዛኛው ምንጫቸው የመንግሥት ሰራተኞች ከሚሰለጥኑበት የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ምሩቃን መሆናቸው ነው:: እዚህ ኮሌጅ ገብቶ ለመማር ቀዳሚው መስፈርት ሰልጣኙ የመንግሥት ሰራተኛ መሆንና በኢህአዴግ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፍልስፍና የተጠመቀ መሆን ይጠበቅበታል:: እነዚህ ግለሰቦች ተመርቀው ወደ ዳኝነቱ መስክ ሲመጡ ከአብዮታዊ እና ኢህአዴጋዊ ፍልስፍና በተቃራኒ በቆሙት ግለሰቦች ላይ የሚኖራቸው ፖለቲካዊ አቋም ኢህአዴጋዊ በመሆኑ ምክንያት ሕገ መንግስቱ የሚጠይቀውን ‹‹ዳኝነት ነፃ እና ገለልተኛ መሆን አለበት›› የሚለውን መርህ ይገዳደርባቸዋል::

ሁለተኛው ነጥብ የዳኞች አሿሿም ሂደት ላይ የሚያነሱት ጥርጣሬ ነው:: ጠ/ሚኒስትሩ የሀገሪቷ ርዕሰ መስተዳደር፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ መሆናቸው ሕገ-መንግሥቱ ይደነግጋል (አንቀጽ 74) :: ከእነዚህ ዋና ዋና ተቋማት በተጨማሪም እጃቸው የዳኝነት አሿሿም ሥርዓቱ ላይም ያርፋል:: ስለዳኞች አሿሿም በሚደነግገው አንቀጽ 81 ላይ የጠ/ሚኒስትሩን ሚና በግልፅ ያስቀምጠዋል::

81፥1 ‹‹የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት የፌዴራል መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ::››

81፥2 ‹‹ሌሎች የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞችን በተመለከተ የፌዴራል የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የቀረቡለትን እጩዎች ጠ/ሚኒስትር ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያሾማል::››እነዚህ ሁለቱ አንቀጾች የጠ/ሚኒስትሩ ከከፍተኛ የፌዴራል ዳኞች ጋር ያላቸውን ቀጥተኛ ትስስር ያሳያል የሚሉት ተንታኞች ዳኞቹ ባገኙት ሹመት ነፃነታቸውን አሳልፈው እንደሚለውጡበት ይከራከራሉ::ኤሳው ለሆዱ ሲል ብኩርናውን በያዕቆብ ምስር እንደለወጠው፡ ፡ እንዲህ አይነቱን ፍርድ ቤት የህግ ሰዎች የካንጋሮ ፍርድ ቤት ይሉታል::

## ከእስር ወደ እስር

ኢህአዴግ ተመሳሳይ የማሰርና የመፍታት ስትራቴጂዎች አሉት:: ወንጀለኛ ተብለው የተጠረጠሩ ግለሰቦች ይታሰራሉ:: ይከራከራሉ:: ጥፋተኞች ናችሁ ይባላሉ:: ፍርዳቸውን ይቀበላሉ:: ከዚህ በኋላ ሁለተኛው እንቅስቃሴ ይጀመራል:: የሃይማኖት አባቶች ይመጣሉ፣ ሽማግሌዎች ይዘጋጃሉ፣ አምባሳደሮች በእስር ቤት ደጃፍ ምልልስ ያደርጉና የይቅርታ ፎርም እንዲሞሉ ይደረጋል:: በዚህ የይቅርታ ፎርም ውስጥ ኢህአዴግ በቀጣይ ታሳሪዎቹ ከእስር ቤት ውጭ በማንኛውም የፖለቲካ መድረክ የማይንቀሳቀሱበትን ሌላ እስር ያበጅላቸዋል:: የፎርሙ መሞላት ሁለት አንድምታዎች ይኖሩታል:: የመጀመሪያው ኢህአዴግ ጥፋተኛ ናቸው ብሎ ያሰራቸው ግለሰቦች ላይ የተሰነዘረበትን ሂስና ትችት መሠረተ ቢስ መሆኑን ታሳሪዎቹ በራሳቸው ፍቃድ ለማመናቸው ማረጋገጫ ሲያስገኝለት ሁለተኛው በይቅርታ ከተፈቱ በኋላ ዳግም አጥፍተው ቢገኙ የሚደርስባቸውን ከባድ ቅጣት እያሰቡ ወደ ጋዜጠኝነቱም ይሁን ወደ ፖለቲካው ላለመግባታቸው ዋስትና እንዲያገኝ ያስችለዋል::

ይሄ ተለምዷዊ አካሄድ አሁን አሁን በወጣት ታሳሪዎች ዘንድ ተግዳሮቶች እየገጠሙት ለመሆኑ ርዕዮት አለሙ አንድ ማሳያ ነች:: ሌሎቹ ታሳሪዎች የይቅርታ ፎርሙን ለመሙላት መንገድ የጀመሩ ቢሆንም እርሷ ግን ጉዳዩን ዳግም እንዲታይላት በመጠየቋ ምክንያት በድጋሚ ፍርድ ቤት ለመቅረብ በቅታለች:: ባለፈው ሳምንትም ጥፋተኛ ናችሁ ተብለው በፍርድ ቤት ብያኔ የተሰጠባቸው ጋዜጠኞችና ፖለቲከኞች በፍፁም የእስር ማቅለያ እንደማይጠይቁና የሰሩት አንዳችም ጥፋት እንደሌለ መናገራቸው ነባሩን የአፈታት ተሞክሮ ጥያቄ ምልክት ውስጥ እንደሚከተው ይጠበቃል::

ኢህአዴግ አሁን ካለበት ጫና አንፃር በተለይ ሁለቱን የውጭ አገር ጋዜጠኞች ለመፍታት ሲል የእኛንም አገር ዜጎች መፍታቱ የሚጠበቅ ስለሆነ እንቢ ያሉትን ለማሳመን የኃይል እርምጃ ሊወስድባቸው ይችላል የሚለው የብዙዎቹ ግምት ነው:: በተለይ ከፍርድ ሂደቱ በኋላ እስረኞቹ የደረሰባቸው ወከባ እና እንግልት የዚህ አንዱ ማሳያ መሆኑን ታዛቢዎች ይመሰክራሉ::

## ዳኛው የኢትዮጵያ ህዝብ....

በ1953 ዓ.ም. ብ/ጄ መንግሥቱ ንዋይ በንጉሠ ነገሥቱ ላይ መፈንቅለ መንግሥት በማድረግ ወንጀል ተከሶ ፍርድ ቤት በቀረበበት ወቅት የተላለፈበትን የሞት ቅጣት ውሳኔ ከሰማ በኋላ የተናገረው ንግግርና እንዲለም አራጌ የቅጣት ማቅለያ ማቅረብ እንደሚችል በተሰጠው እድል ወቅት የተናገረው ንግግር ተመሳሳይ ናቸው::ይህ ክስተት ከዘመናት በኋላ የተደገመ ታሪካዊ ግጥጥሞሽ ከመሆኑም በላይ በሀገራችን ፍርድ ቤቶች ከዳኞቹ በላይ የማን እጅ እንዳለበት ከጥንት ጀምሮ ተመሳሳይ እንደሆነና በዳኝነት መተማመኛ ላይ አሁንም ያልተሻሻልን መሆናችንን ያመላክታል::

‹‹…እናንተ ዳኞች የፈረዳችሁብኝን የሞት ፍርድ ያለይግባኝ ተቀብየዋለሁ:: ይግባኝ ብዬ ጉዳዩን የሚመለከትልኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢሆን ኖሮ ይግባኝ ማለት በፈለግሁ ነበር:: ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት፣ ነፃነት እርምጃ የተነሳሁ ወንጀለኛ ነኝ እንጂ ላፋጀው የተነሳሁ ወንበዴ አይደለሁም::

…ከእናንተ ከዳኞችና የሞት ፍርድ እንድትበይኑብኝ ካዘዛችሁ ሰው ይልቅ ፍርድ ተቀባዩ የዛሬው ወንጀለኛ የነገው ባለታሪክ ነኝ::

…ዋ! ዋ! ዋ! ለእናንተና ለገዢአችሁ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀሳቤ በዝርዝር ገብቶት በአንድነት በሚነሳበት ጊዜ የሚደርስባችሁ መዓት የሚያሳቅቅ ይሆናል›› ብ/ጄ መንግሥቱ ንዋይ (መጋቢት 19 ቀን 1953 ዓ.ም)

‹‹ያሳለፍነው ግማሽ ምዕተ ዓመት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሰብዓዊ ክብሩና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ የታገለበት ዘመን ነው:: ይሁን እንጂ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ ባለቤት ለመሆን እስካሁን አልታደለም:: እኔም በተፈጠርኩበት በዚህ ዘመን፣ ለራሴ፣ ለልጆቼና ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ዴሞክራሲና ነፃነት እንደሚገባን በማመን አቅሜ በፈቀደው መጠን ታግያለሁ::

ይኽን በማድረጌ በማንም ላይ በክፋት አልተነሳሁም፣ ይኽን በማድረጌ ሕግ ጥሼ አላውቅም፤ ይኽን በማድረጌ በደሃዋ ሀገሬ ጥቅም ላይ አልተነሳሁም፣ ይኽን በማድረጌ ፈጣሪዬን፣ የኢትዮጵያን ሕዝብም ሆነ ሕሊናዬን የሚያሳዝን አንዳች ነገር ፈፅሜያለሁ ብዬ አላምንም:: ፍፁም ሰላም ይሰማኛል::

እኔን እዚህ ያቆመኝ የነፃነት ናፍቆት ነው:: በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶችም ፍትሕን ለምኜ ስነፈግ ይኽ የመጀመሪያዬ አይደለም:: ከሳሾቼ እንድጠጣው የሚፈልጉትን የግፍ ፅዋ በፀጋ ከመጠጣት ውጭ ባልፈፀምኩት ወንጀል ማቅለያ የመጠየቅን አማራጭ ህሊናዬ ስላልተወልኝ አዝናለሁ::›› አንዱአለም አራጌ (ሰኔ 20 ቀን 2004 ዓ.ም)

አጼ ኃ/ሥላሴ በግፍ የሰቀሏቸውን የጄኔራሉን ድምፅ መስማት ባለመቻላቸው አልፎም የንዋይ ልጆች ለስይረ-መንግሥት የተነሳሱባቸውን ገፊ ምክንያቶች ለመረዳትም ሆነ ስርዓታቸውን ለማረም ባለመጣራቸው፣ ራሳቸውንም፣ ሀገሪቷንም ለግብታዊው አብዮት ዳርገው አለፉ:: ከሃምሳ አንድ ዓመታት በኋላ ሀገሪቱን የሚገዛው ኢህአዴግ ስለሀገራቸው ነፃነትየባከኑ ዜጎችን በግፍ ወደ እስር ቤት እየወረወረ ነው:: አንዱአለምን ፍርድ ቤት ያቆመውን ‹‹የነፃነት ናፍቆት›› ለመተርጎም ከእርሱ ፍርድ በኋላ ወደ አደባባይ የሚወጡ ወጣቶች ስላለመምጣታቸው ማን እርግጠኛ መሆን ይቻለዋል?

# የስኳር ፖለቲካ፤ ከወላይታ ሶዶ እስከ ጅንካ
## (የጉዞ ትዝብት)

ዳንኤል ተፈራ

ባለፈው ሳምንት በጣም አደገኛ እየሆነ ስለመጣው የኢትዮጵያዊነት መደብዘዝና የብሔርተኝነት ማንሰራራት ለመፃፍ ሞክሬ ነበር:: በዚያውም ይሄ ሀገር ይረከባል የሚባለው ወጣት ትውልድ ከአባቶቹ በወረሰው የኢትዮጵያዊነት መንፈስና በገገርዎች እየተጫነበት ባለው ዘውጌ ተኮር ፖለቲካ መካከል ተጣብቆ ‹‹የመከነ ትውልድ›› እንዳይሆን ራሱ ወጣቱ ኢትዮጵያዊነቱ እንዲያብብና ለእሱም እንዲተጋ ለመጠቆም የተሰነዘረ ሀሳብ ነበር::

የመጥበቡ ነገር (ብሔርተኝነቱ) እያንሰራራ ነው ስንል እዚሁ አዲስ አበባችን በኪሳችን ይዘናት በምንዞራት መታወቂያ ላይ ከተፃፈው ‹‹ብሔር›› አንስቶ እስከ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብና ሰሜን አቅጣጫዎች ተዘርግቶ እናገኘዋለን:: ክልሌን ረገጥህ፣ ከብቶችህ ድንበር አለፉ... እየተባባሉ ልዩነቱ እስከመገዳደል ይዘልቃል:: በአንድ የስራ ጉዳይ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ በዘለቅሁበት በዚህ ሳምንትም ዕታዘብ ዘንድ ዕድል ያገኘሁት ያንኑ የብሔር ፖለቲካ ውላጅና የቋንቋ ፌዴራሊዝሙን ጦስ ነው:: ግለሰቦች በየጎሳ አጥራቸው ተደብቀው እርስ በእርስ ይጠባበቃሉ:: ታዲያ እንዴት ልምድ መለዋወጥ ይችላሉ? አንዱ ብሔር ያለውን መልካም ዕሴት ሌላውም ለእኔ ይሆናል ብሎ ካልተጠቀመበት እንዴት እንለወጣለን? እንዴትስ ውበት ይኖረናል? ይሄን ጥያቄ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ተባብረን መመለስ እንዳለብን ይሰማኛል:: ዋናው የጉዞዬ ዘውግ ግን እንዲህ ነበር፡-

ዓርብ ሰኔ 22 ቀን 2004 ዓ.ም. በማለዳ ነው የተነሳነው:: ለነገሩ መዳረሻችን ሩቅ ስለነበር በማለዳ መነሳታችን ተገቢ ነበር:: የኬንያ ጠረፍን ‹‹በቱስታ›› ልትል ትንሽ ወደሚቀራት ጅንካ ከተማ:: የምንሄደው ለስራም ቢሆን እግረ መንገዱን ጉዞው የተወጠረ ጭንቅላትን ለማፍታታትም ይጠቅማል:: በተለይ ባለፈው ሳምንት ደግሞ ‹‹ደገኛ›› ሳምንት አልነበረም ለእኔ:: ምክንያቱ ደግሞ በእነ አንዷለም አራጌ የክስ መዝገብ፣ በእነ እስክንድር ነጋና ሌሎች በሽብርተኝነት ስም የተያዙት ፖለቲከኞች ላይ ፍ/ቤቱ ያስተላለፈው ውሳኔ ውስጤን ስላወከው ነው:: የዐቃቤ ሕግን የክስ ዝርዝር ላነበበ፣ የዐቃቤ ሕግን ምስክር ላዳመጠ፣ በኋላም ተከሳሾች ያቀረቧቸውን የመከላከያ ምስክሮች ለተከታተለና በመጨረሻ ፍ/ቤቱ የወሰነውን ‹‹ጥፋተኛ ናችሁ›› ተጉልቶ ያየ ሰው ባይታወክ ነው የሚደንቀው:: የምንታወከው ‹‹ህሊና›› የሚባል ክቡር ዳኛ ተሸክመን ስለምንዞር ነው:: በዚሁ ዙሪያ አንድ ቀን ዘርዘር አድርጌ እንደምፅፍ ተስፋ አደርጋለሁ:: ያነሳሁላችሁ ግን እንደኔ እንድትታወኩ ሳይሆን ወደ ጅንካ ያደረግነው የስራ ጉዞ የህሊና ሸክም ለበዛበት ሰው እንደማስታገሻ ክኒን የሚቆጠር ነበር ለማለት ነው::

ከአዲስ አበባ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ የሚያስገቡ ሁለት ዋና መንገዶች ቢኖሩም የእኛ የጉዞ መስመር በዓለም ገና በኩል ሆነ:: አለምገና፣ ጌጃ፣ አዋሽ ለሁለት ሰንጥቆ የሚያልፋትን አዋሽ መልካና ለአቅመ ከተማ ያልደረሰችው፣ ለኦሮሚያ ክልል የመጨረሻ ከተማ ሌመን:: ከዚያም ወደ ደቡብ ክልል ገብተናል ማለት ነው::

ከዚያም ባለትክል ድንጋዩዋ ጢያን፣ ቡኢሶዶ፣ ኬላና በጉራጌ ዞን ትልቅ ልትባል የምትችለውን ከተማ ቡታ ጅራ እናገኛለን:: (በነገራችን ላይ እንደ አፍዊ ትርክቱ ቡታ ጅራ ስያሜዋን ያገኘችው ከአንድ ሽፍታ ነው ይባላል:: ሽፍታው ስሙ ቡታ ይባላል አሉ:: ታዲያ ነጋዴዎች ለማለፍ ቡታ መኖሩን ማረጋገጥ አለባቸው:: ስለዚህ በኦሮምኛ ‹‹ቡታ ጅራ?›› ብለው ይጠይቃሉ:: ቡታ አለ? ማለታቸው ነው:: እናም ቡታ ጅራ ተባለች አሉ:: ሌላ ትርክት ካለ ለመቀበል ተስማምተን እንቀጥል)

በዚሁ መስመርም የስልጤ ዋና ከተማ ወራቤ ትገኛለች:: ወራቤን ስናቋርጥ ትውስ የሚሉን የኢህአዴጉ ዋና ካድሬና ከጠ/ሚኒስትሩ አማካሪዎች አንዱ የሆኑት አቶ ሬድዋን ሁሴን ናቸው:: በብሔር ፖለቲካ አቀንቃኝነታቸው ከተቃዋሚነት ወደ ዋና የኢህአዴግ ሰውነት የተሸጋገሩትን ሲሉ ትዝ ይሉናል:: በሀድያ ዞን ደግሞ አጫሞ፣ በሌሳ፣ በስተግራ ዋቾም ዩኒቨርስቲ፣ ሆሳዕና፣ ከምባታ፣ ወላይታ፣ ዲዮገና እንልና ምክትል ጠ/ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ የትውልድ አካባቢ የሆነውን አረካ እናገኛለን:: አረካ የምትታወቀው በአቶ ኃይለማርያም ሀገርነት ብቻ ሳይሆን በርካታ የጉዲፈቻ ልጆች የሚሰበሰቡባትና የሚላኩባት ሀገር በመሆኗም ነው:: አንድ ግዙፍ በጣሊያናዊ የሚመራ የሕፃናት መሰብሰቢያ ማዕከል ያለ ሲሆን እንደሌሎቹ አቻ ከተሞቿ በሙስና እጅና እግሯ የታሰረ ከተማ ናት ይባላል:: ቀጥሎ ወላይታ ሶዶ ቁልቁለት ላይ ከትማ ትታየናለች:: ከአዲስ አበባ ጀምሮ ወላይታ እስክ ንደርስ የምናገኛት ትልቅ ከተማ ወላይታ ሶዶ ናት::

ወላይታ ሶዶ የፖለቲካ ከተማነት ወግ አላት:: በደኢህዴን/ኢህአዴግ ውስጥ የተሻለ ቦታ አላቸው የሚባሉት የወላይታ ተወላጆችና የፌደራሉ ጥግ ላይ የደረሱት እነ አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝና አምባሳደር ተሾመ ቶጋ ይጠቀሳሉ:: እንደ ሶዶ ከተማ ኗሪዎች ገለፃ ከሆነ አስተዳደሩ ወንድም፣ የአጎት ልጅ፣ የአክስት ልጅ፣ ዘመድ... እየተባለ የተዋቀረ ነው:: ይሄ ደግሞ ለሙሰኝነት ወለል ብሎ የተከፈተ በር ነው ሲሉ ይደመጣሉ:: የፖለቲካ ትኩሳት ካለባቸው ከተሞች አንዷ ከመሆኗ በተጨማሪ ከስኳር ጋር በተያያዘም ስሟ ሲነሳ ሰምቻለሁ:: የስኳሩን ነገር ወረድ ብለን እንቀጥላለን::

ሁምቦ ላይ አብያታ ሀይቅ ደረቱን ገልብጦ ይታያል:: አሁን ወደ ጋሞ ድንበር እየተጠጋን ነው:: የወላይታንና የጋሞን ድንበር የሚለይ ሀመኝ የሚባል ትልቅ ወንዝ አለ:: ወንዙ የሚያገለግለው በዋናነት ለመስኖ ሳይሆን ሁለቱን ለመለያየት ነው:: ጋሞ ጐፋ ወይም ጋሞ ስንገባ ዋጅፎን እናገኛታለን፣ የምዕራብ አብያ ብርብር ከተማ፣ የተፈጥሮ ፀጋ የበዛላት አርባ ምንጭ፣ የኮንሶ ዋና ከተማ ካራት፣ ወይጦ በረሃ፣ ቀይ አፈር፣ ፀማይና በና ከዚያም ጂንካ በማለት ጉዞው ይጠናቀቃል::

በዚህ ጉዞ መታዘብ የሚቻለው ‹‹የግብርና መር ኢኮኖሚ እከተላለሁ›› የሚለው የኢህአዴግ ስርዓት ለከተሞች መስፋፋት ቦታ እንዳልሰጠ ነው:: ከአዲስ አበባ እስከ ጅንካ ባለው ከ700 ኪ.ሜ በላይ መንገድ የከተማ ወግ ያላቸው ከአራት አይበልጡም:: የከተሞች መስፋፋት (Urbanization) በኢትዮጵያ አልተጀመረም ማለት ይቻላል:: በየመንገዱ የሚገኙ ሚጢጢ ከተሞች የሚታይባቸው መሰረተ ልማት ሳይሆን እጅና እግር ያለው ድህነት ነው:: በከተሞች የጉዳና ዳር ድህነት ራሱ ሲተራመስ ይታያል::

በኢትዮጵያ ወደ 83 ፐርሰንት የሚጠጋው የገጠር ኗሪ ሲሆን፤ ይሄ የገጠር ኗሪ በአቅራቢያው የሚያገኛቸውና ንቃተ ህሊናውን የሚያዳብሩ ወይም ቀልቡን የሚማርኩ ከተሞች የሉትም:: ለአንዲት ሀገር እድገት የከተሜነትና የከተሜነት አስተሳሰብ መስፋፋት ወሳኝ እንደሆነ ባለሞያዎች ይናገራሉ:: መንግሥት ከተሞች ላይ እየተከተለ ያለው ፖሊሲ በተለይ ደግሞ የመሬት ፖሊሲ ለከተሞች አቅመ ቢስ መሆን እንደምክንያት ሊቀርብ ይችላል:: ግለሰቦች ከተሞች ላይ መዋዕለ ነዋያቸውን እንደያፈሱ የሚጋብዝ ነገር የለም:: ስለዚህ አይነግቡ ከተሞችን ማጣት ብቻ ሳይሆን ከተሞች የድህነት መናኸሪያ ሲሆኑ እያየን ነው:: ወደ ከተማ የሚገባው ብር ያለው አርሶ አደር ሳይሆን የከፋው፣ የተቸገረና ‹‹ሽቅዬም ቢሆን እበላለሁ›› ብሎ የሚያስበው ነው:: በደቡብ ኢትዮጵያ ያየሁዋቸው ሚጢጢ ከተሞችም የተበላሸ ፖሊሲና የተከፋ ሰው መጠራቀሚያ መሆናቸውን ነው::

በዚህ ፅሑፍ መግቢያ ላይ እንደጠቀስኩት ዜጎች ሊያስማማቸው የሚችለው የኢትዮጵያዊነት ምስል ደብዝዞባቸው ይልቁንም በጎሳቸው ውስጥ ተደብቀው ዕርስበርስ ሲጠባበቁም ይታያል:: ሁሉም ዞን፣ ሁሉም ልዩ ወረዳ፣ ሁሉም ክልል መሆን ይፈልጋል:: ይሄን የ‹‹እኔ ትልቅ ነኝ›› በሽታ ግን ሕዝቡ እንዳልፈጠረው እርግጠኛ ሆኖ መናገር ይቻላል:: ችግሩ የተፈጠረው አብሮ፣ ተሳስቦ፣ ተጋብቶና ተዋልዶ የኖረው ሕዝብ በቋንቋውና በብሔሩ እንዲለይ ሲደረግ ነው::

በደራሼ ልዩ ዞን ጊዶሌ ከተማ ላይ ከሀገሬው ኗሪዎች አንደበት እንደሰማሁት በተለይ ከአጉራባቾቻቸው ኮንሶዎች ጋር በበጎ አይን አይተያዩም:: በተጉሳቆለችው ጊዶሌ ላይ ብሔርተኝነት የወለደው ፖለቲካ ተንቦግቡጎ ሲነድ ይታያል:: ደራሼዎች ወደ ጅንካ በሚሄደው አውራ ጎዳና በኮንሶዎች ማለፍ ተቆጥተው የመንገድ ስራው እንዲስተጓጎል እስከማድረግ ዘልቀዋል:: ደራሼዎችና ኮንሶዎች በመንገድ ይጣላሉ:: ሁለቱን እኩል ተጠቃሚ የሚያደርግ አስተሳሰብም፣ ስርዓትም የለም:: የአንደኛው መጠቀም ለአንደኛው ጉዳት ተደርጎ ይቆጠራል:: አንደኛውም አንደኛውን ሊረዳ አይፈልግም:: ይሄ ኢህአዴግና ስርዓቱ ለባለፉት 21 ዓመታት የዘሩት ክፉ ዘር ውጤት ነው::

ዋነኛው ግን የስኳሩ ጦርነት ነው:: የስኳር ፖለቲካው ከወላይታ ሶዶ አንስቶ እስከ ደቡብ ኦሞ ዋና ከተማዋ ጅንካ ይዘልቃል:: (በነገራችን ላይ ጅንካ በተፈጥሮ ሀብት የታደለች ነገር ግን አንጀት የምትበላ ከተማ ናት:: አንድ አስፓልት እንኳ የሌላት ምስኪን:: በደቡብ ኦሞ 16 ብሔሮች ይኖራሉ:: እነርሱም ዲሜ፣ ኮይጉ፣ ሙሪሌ፣ ባጫ፣ ማሌ፣ ካራ፣ አሪ፣ ኤርቦና፣ ሙርሲ፣ በና፣ ብራይሌ፣ ቦዲ፣ ዳሰነች፣ ኛንጋቶም፣ ሀመር እና ፀማይ የሚባሉት ናቸው:: የእነዚህ ብሔሮች ከተማ ደግሞ ጅንካ:: ታዲያ የእነዚህን ብሔሮች ድንግል ባህልና ከሌላው የከተሜ ኑሮ ጋር የሚቃረን የአኗኗር ዘዬ ለመጐብኘት የሚመጡ ቱሪስቶች ጅንካ ላይ ይፈሳሉ:: ጅንካ ግን የምትነቃ አይመስልም:: የተስተካከለ የከተማ ፖሊሲ ቢኖር ኖሮ ጅንካን የቱሪስት መዳረሻ ከማድረግ የሚያግድ ነገር አልነበረም:: ጅንካም እንደሌሎች ከተሞች እስረኛ ናት::)

ዋናው የፖለቲካ ትኩሳት የሚነሳው ከደቡብ ኦሞ ነው:: በደቡብ ኦሞ ኩራዝ የሚባል ግዙፍ የስኳር ፋብሪካ እየተገነባ ነው:: የስኳር ፋብሪካው ከሙርሲ ጀምሮ ኦሞራቴ ድረስ የሚዘልቅ ሰፊ ቦታ አለው:: ‹‹ወደዚህ የስኳር ፋብሪካ የሚወስደው መንገድ በእኛ ማለፍ አለበት›› የሚለው ጥያቄ በአካባቢው ያሉ ብሔሮች ሁሉ ጥያቄ ነው:: ምክንያቱም የሚጠቀሙት በብሔራቸው ብቻ እንደሆነ የሚነግር ሰንኮፍ ተሰክቶባቸዋል::

የስኳር ፋብሪካው መቋቋሙ መልካም ቢሆንም ከጅንካ እስከ ወላይታ ሶዶ ያሉ ኗሪዎች የሚያስጨንቃቸው ‹‹እዚያ ያሉ አርብቶ አደሮችን የት ሊጥሏቸው ነው?›› የሚለው አይደለም:: የመንገዱ ማለፊያ ጉዳይ ነው ጭንቀታቸው:: ጅንካ ከተማ ውስጥ ስለዚሁ የስኳር ፋብሪካ ጉዳይ አስተያየት የሰጡኝ ወጣቶች የስራ ዕድል ለእኛ መሰጠት አለበት በማለት አጥብቀው ይናገራሉ:: ‹‹ወላይታዎች ሰፊ የስራ ዕድል እየተሰጣቸው ነው›› ሲሉም ይከሳሉ::

የስኳሩ ፖለቲካ ግን በስራ ዕድልና በመንገዱ ጥያቄ ብቻ የሚቆም አይመስልም:: ‹‹የስኳሩ ማጠራቀሚያ መጋዘን የት ሊሰራ ነው?›› የሚልም ጥያቄ አለ:: የጅንካ ኗሪዎች ‹‹መጋዘኑ ወላይታ ይሰራል ተብሏል ስለዚህ እኛ እየተገፋን ነው›› በማለት ይናገራሉ:: ከስኳር ፋብሪካው ጅንካ ተጠቃሚ እንዳትሆን በዕቅድ እየተሰራ ነው ሲሉ ይከሳሉ:: የወላይታ ባለስልጣናት እጅ አለበትም ይላሉ::

እኔ ግን ኢህአዴግ የዘራውን እያጨደ ይመስለኛል:: ‹‹ጅንካ ያለው የስኳር ፋብሪካ ለወላይታው፣ ለከንባታው፣ ለሀድያው፣ ለትግሬው፣ ለአማራው፣ ለኦሮሞው እኩል ሀብቱ ነው›› የሚለው አስተሳሰብ በዘውጌው ፖለቲካ የተነሳ ጠፍቷል:: ስለዚህ ብሔሮች እንዴት እንብላ? ሳይሆን እከሌ ለምን በላ? በሚል ክፉ የዘረኝነት በሽታ ተጠቅተዋል:: እንዲጠቁ ያደረጋቸው ደግሞ ቋንቋን መሰረት ያደረገው የኢህአዴግ ፌዴራሊዝም ነው:: የስኳር ፖለቲካው የተጧጧፈው ገና በችግኝ ተከላ ላይ እያለ ነው:: ስለዚህ ‹‹የሺ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ›› እንደሚባለው በኢትዮጵያዊነት ገመድ ካልተሳሰርን በቀር መጪው ጊዜ???

# ክፍተቱና ለውጡ

በሚኪያስ ዲኖ

በመዲናዋ ሰማይ ላይ የለውጥ ደመና አንዣቧል:: ይሄ ደመና መዝነቡ እንደማይቀር ታምኖበታል:: እርግጥ ነው ሀገሪቱ በለውጥ ሙቀት ተነቃቅታለች:: በፍርሃት ቆፈንም እንዲሁ ተቀፍድዳለች:: በነዋሪዎቿ ልብ ውስጥ ፍርሃት ከተስፋ ተቃይጧል::

ወሬው ሁሳ አንድም ‹‹አምቦ ደርሰዋል›› አልያም ‹‹በኬንያ ሾልከዋል›› አይነት ብቻ ነው:: ይባስ ብሎ ‹‹አንድ ጥይትና አንድ ሰው እስኪቀር እንዋጋለን›› ብለው የፎከሩት ጓድ ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም ‹‹ያ አንድ ሰው ማለት እኔ ነኝ›› ብለው መፈርጠጣቸው ተሰማ::

ይሄ የመጨረሻው ደውል ማለት ነበር:: የአስራ ሰባት አመቱ አገዛዝ በአስራ ሰባት አመት ትግል ሊወድቅ መቃረቡ ግልፅ ሆነ:: የተሽመደመደውን አስተዳደር አጠናክሮ ለመቀጠል የሞከረው የሌ/ጄ ተስፋዬ ገ/ኪዳን መንግስት እድሜም ከአንድ ሳምንት ሊዘል አልቻለም::

ለውጥ መንታ ገፅታ አለው:: ለውጥ ከተካሄደ በኋላ አለመንቀሳቀስ፣ ባሉበት መርጋት የያዙትን አለመልቀቅ አይቻልም:: ለውጥ ወደ የትም ይሁን በነበሩበት፣ ከነበሩበት አለመገኘት ነው::

በወርሃ ግንቦት 1983 ዓ.ም. ኢትዮጵያ እንዲህ ባለው ወሳኝ ምዕራፍ ላይ የተገኘችበት ጊዜ ነበር:: በውጤቱም የታገሉት ወደ ዳገት ያልታደሉት ወደ ቁልቁለት ጥቂቶች ወደ ቅንጦት ብዙሃኑ ወደ ዕጦት የተሸጋገሩበት ዋዜማ...

ህዝቤ ‹‹በምን ይፈጠር ይሆን?›› ስጋት ተውጧል:: ዙሪያው ‹‹ነፃ አውጪ ነን›› ባሉ ታጋዮች ተከቧል:: ውስጡ ደግሞ እስከ አፍንጫው በታጠቀው የደርግ ወታደር ተሞልቷል:: እረኛውን እንዳጣ መንጋ ወታደሩ በየመንደሩ በየተራራው ተበትኗል::

የህዝቡ ፍርሃት ምክንያታዊ ነበር:: ‹‹ለታጋዮች›› ያለው ፍርሃት ምንጩ የደርግ ፕሮፓጋንዳ ነበር:: በልጅነት ተረት እንደሚነገሩት ‹‹ሰው በላ ጭራቆች›› ተደርገው ተስለውለታል:: እናም የነዚህ ሀይሎች በቅርብ ርቀት መገኘት አስፈርቶታል::

በዚህ በኩል የደርግ ወታደር ራሱ የተበተነ፣ የተሸነፈ፣ የተፈታ ጦር ነው:: ተስፋ የቆረጠ በዚያ ላይ የታጠቀ ነውና በቀጣይ ምን ዕርምጃ ሊወስድ እንደሚችል መገመት ይከብዳል::

ህዝቡ ቤቱን በመተው የእምነት ተቋማትን ተተግኖ ፀሎቱን ተያያዘው:: ይሄ ሁሉ ስጋት ይሄ ሁሉ ሽሽት እንዲህ ያለው ብሄራዊ ጭንቅ የሚሆነው የዛሬ ሃያ አንድ አመት በወርሃ ግንቦት ነው::

ወዲያው ግን የተበተነው የደርግ ሰራዊት ባህርይ ታወቀ:: እናማ አንድ ስጋት ቀለለ:: ባልተጠበቀ መልኩ ወታደሩ ጃኬቱን አንጥፎ መለመን ጀመረ:: እየለመነ፣ ሲመቸው እየተደራደረ መሳሪያውን በመሸጥ በአዘቦት ልብስ እየቀየረና ወደ ገጠር መሰደድ ጀመረ::

አንድ ማለዳ ታዲያ ብዙሃኑ ሀሳቡን ቀይሮ ከ‹‹ፀሎት›› ወደ ‹‹ስርቆት›› ተሸጋገረ:: የዘረፋው ኢላማዎች የአራት ኪሎ ቤተ-መንግስትን ጨምሮ ሙሉ በሙሉ መንግስታዊ ተቋማት ነበሩ::

የአባትህ ቤት ሲዘረፍ

አብረህ ዝረፍ በሚል ወቅታዊ አባባል እየታጀበ ከልጅ እስከ አዋቂ ከዘይትና ስኳር እስከ መስኮትና በር ተመዘበረ::

የወታደራዊው ደርግ ‹‹ወጣት በል›› አገዛዝ ለአስራ ሰባት ዓመታት ካተራመሰ ደም ካፋሰሰ በኋላ በአዙሪቱ ህግ መሰረት በሀይል ሊወድቅ ተቃርቧል:: ለአመታት ሲንቀለቀል፣ ሲቀጣጠል የነበረው የበረሃው ቋያ ወላፈኑ ከሰሜንም አልፎ የወበቁ ቀለበት ዋና ከተማዋን ከቧታል::

* * *

እነሆ ግንቦት 20 1983ዓ.ም. ደመናው በእርግጥም ዘነበ:: ‹‹ህወሓት›› መራሹ ‹‹ኢህአዴግ›› አዲስ አበባ ለመግባት በቃ:: ከምናቡ ምስል ያልገጠሙለት ሕዝብ ‹‹እነዚህ ደቃቆች ናቸው ደርግን...!›› እያለ አሽሟጠጠ (በዚህ እልህ ይመስላል ያለዕረፍት ተመግበው ደልበው፣ ወዝተው ‹‹ንጣት›› የወረሰውን ህዝብ ‹‹እንቁልልጭ›› ያሉት) (ቅንፍን ቅንፍ ይጠራዋልና ሌላ ቅድመ ጥርጣሬ እናስቀምጥ ምናልባት አንባቢ ይሄ ልጅ ሰኔ መጨረሻ ላይ ስለግንቦት 20 ለምን ይጨቀጭቀኛል ብሎ ቢጠይቅ የኔ ተግባር የገዢዎቻችንን ማህደር ማገላበጥና ከዚያ ውስጥም ያገኘኋትን ዝነኛ አባባል ማበርከት ነው እሷም ‹‹የአፈፃፀም ችግር ነው›› ትላለች::)

ከተማዋን የተቆጣጠረው ነፃ አውጪ ቡድን የቀበሌዎችንና መሰል ተቋማትን መዘረፍ ለማወቅ ጊዜ አልፈጀበትም:: ከወሬ በተጨማሪም ሁኔታዎች ሁሉ ድርጊቱን በሚገባ የሚያሳዩ ነበሩ::

ወዲያውም ህዝቡን በመሰብሰብ ‹‹የተዘረፈ እቃ በአስቸኳይ ይመለስ::›› የሚል ትዕዛዝ አስተላለፈ:: ከዚህም ጋር ተያይዞ ‹‹ኢህአዴግ ሌባ አይወድም›› ከሚል ወሬ ጋር በአባሪነት የመቀጣጫ ግድያ መበራከት ድንጋጤን ፈጠረ

* * *

እስቲ ለናሙና ያህል በኛ ቀበሌ የተከናወነውን ልተርክላችሁ

* * *

እያንዳንዱ ዘራፊ የወሰዳትን እቃ ራሱ እንዲመልስ ተወስኖበታል:: በዘረፋው ያልተሳተፈው ነዋሪ ጉዳዩን ለመመልከት ግልብጥ ብሎ ወጥቷል:: ጥቆማውንና ደብቆ በፍተሻ ከተገኘበት የሚጠብቀውን ቅጣት በመፍራት ሁሉም የወሰደውን ተሸክሞ፣ አንጠልጥሎ፣ እየገፋ መምጣት ጀመረ...

እጅግ አሳፋሪ በትንሹ ደግሞ አስቂኝ ትዕይንት ነበር:: በተለይም የስነ-ምግባር መገለጫ ተደርገው የሚታሰቡ በማህበረሰቡ ውስጥ የመካሪነት፣ የተቆጪነት፣ የሁሉን አዋቂነት ክብር የተሰጣቸው ትላልቅ ሰዎች...

ኩንታል ስኳር ተሸክመው፣ ባዶ በርሜል እየገፉ፣ ትልቅ የቤት በር ተሸክመው፣ ጀሪካን ዘይትና እሽግ ፓስታ አንጠልጥለው፣ በመፅሐፍ መደርደሪያ ሸክም ጉብጠው...

ዳርና ዳር የተሰበሰበው ህዝብ በጭካኔ እየሳቀባቸው... ፊታቸው ላይ ደግሞ ሲወስዱ የነበረ የማይመስል ሀፍረት እየተነበበባቸው... ያው ደግሞ ‹‹ስምና መንገድ›› እንደሚባለው ከክስተቱ ጋር ተያይዘው የመጡ ‹‹ቅጥያ ስሞች›› ፀድቀው...

በዚህ የአገዛዝ ቅይይር በተፈጠረው ክፍተት የታየው ስርዓት አልበኝነት /ስርቆት/ መንግስት ፀንቶም አልተወገደም:: ከዚያም ይልቅ ህዝባዊ ሆኖ የታየውን ሌብነት መንግስት ቀምቶ ‹‹የመንግስት ሌቦች›› በማለት በስሩ አቅፎት ሲተዳደርበት...

እንዳለመታደል ሆኖ ኢትዮጵያ ስልጣን ያለ‹‹ደም ግብር›› አይሸጋገርም:: እንዲህም ሆኖ ለውጡ ‹‹የግለሰብ›› እንጂ ‹‹የስርዓት›› አልሆነም:: መንግስቱ ኃ/ማርያምን አባረን መለስ ዜናዊን አነገስን እንጂ ‹‹አገዛዝን›› አስወግደን ‹‹ዴሞክራሲን›› አልሰየምንም::

የተመለከትናቸውም ለውጦች በሙላ የህዝቡን ብሶት የህዝቡን ምኞት እንደ ደጋን ተጠቅመው ይወነጨፉና ከፍታው ላይ ሲደርሱ ተመልሰው ራሱን ሊወጉት ይጀምራሉ::

ገዢዎቻችን መሪነትን እንደሚገባቸው ‹‹ርስት›› እንጂ እንደተጣለባቸው ‹‹ሀላፊነት›› አልተመለከቱትም:: ህዝቡም ከተከለለለት ባለመውጣት ከተከለከለው ባለመግባት ‹‹እንደተፈለገው›› ሆኖ ተገኝቷል::

**ትላንት**

የንጉሱን ‹‹አምላክ አከል›› አገዛዝ ተማሪው

ወደ ገፅ 13 ዞሯል »

በጌታቸው ታምራት (LLB)

# የፍትህ ዓምድ

በዚህ ዓምድ የአገራችንን ህጎች ፣ ዓለም አቀፍ ህግጋት ፣ በሀገራት መካከል የተደረጉ ስምምነቶችን እንዲሁም ለንፅፅር እና ለማገናዘቢያ ይረዳን ዘንድ ሌሎች ሀገሮችን ህጎች መሰረት በማድረግ ከማንኛውም አይነት የፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መልኩ ትንታኔ ይሰጣል፡፡

# አዲሱ የቴሌኮም ረቂቅ አዋጅ ምን ይላል?

ተንቀሳቃሽ ስልኬን አንስቼ ቴሌኮም ለመረጃ ወደዘረጋው የነፃ ጥሪ 994 ደወልኩ፡፡ ከቆይታ በኋላ አንዲት ወጣት የስልክ መስመሬን ተቀላቀለች፡፡ ትህትና በተሞላበት አነጋገር የፈለኩትን ዕርዳታ ጠየቀችኝ፣ የአንዳንድ ሀገራትን ስም በመጥራት ወደነዚህ ሀገራት ብደውል የደቂቃ ታሪፍ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ፈልጌ እንደደወልኩ ነገርኳት፡፡ ለሁሉም ዓለም አቀፍ ጥሪዎች በደቂቃ ቫትን ጨምሮ 12፡33 ሲሆን ከቫት በፊት 10፡72 እንደሆነ ነገረችኝ፡፡ በመቀጠልም ይህ ታሪፍ ጅቡቲን እንደማይጨምር ካስረዳችኝ በኋላ ለጅቡቲ ጥሪ ቫትን ሳይጨምር በደቂቃ 7 ብር ከ72 ሳንቲም ነው፤ በማለት የአስራ አምስት በመቶ የቫት ዋጋ እንድጨምርበት የሒሳብ ስራ ሰጥታኝ፣ በመደወሌ አመስግና ስልኩን ዘጋችው፡፡ እርግጠኛ ለመሆን ደጋግሜ ደዋወልኩ፡፡ ተመሳሳይ ነው፡፡ ታዲያ ይህን ታሪፍ ሽሽት ነው ብዙ ሰዎች ውጭ ሀገር ካሉ ዘመድ ወዳጆቻቸው ጋር ለመገናኘት ሲፈልጉ በቅናሽ ወደሚያስደውሉ ኢንተርኔት ቤቶች የሚሄዱት፡፡ በእነዚህ ቤቶች ቴሌ በደቂቃ ከሚያስከፍለው ታሪፍ በግማሽ የቀነሰ እንዲሁም ለአንዳንድ ሀገራት ከ75% በመቶ በታች ቅናሽ ነበር፡፡ አሁን ግን ይህ የማይቻል ሆኗል፡፡ አዲስ በተረቀቀው የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል መቆጣጠሪያ አዋጅ ደዋይም አስደዋይም በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆኑ በረቂቅ አዋጅ ተካቷል፡፡ ይህንንም ፍራቻ ይመስላል በእንዲህ ዓይነቱ ስራ ውስጥ ይንቀሳቀሱ የነበሩ አንዳንድ ቤቶች ተዘግተዋል፤ በሌሎቹም ቢሆን ግርግሩ እንደበፊቱ አይደለም፡፡ ይህ አዋጅ በአሁኑ ወቅት በአብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል ትልቅ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆኗል፡፡ ለመሆኑ አዋጁ ለምን አስፈለገ? በውስጡስ ከደዋይና አስደዋይ ክልከላዎች ሌላ ሌሎች ምን ነገሮችን ይዟል?

ለመነሻ ያህል ረቂቅ አዋጁ በመግቢያው ላይ ይህ አዋጅ አስፈለገ ያለበትን ምክንያት እንጥቀስ፡፡ ‹‹…የቴሌኮም ማጭበርበር ድርጊት ለበርካታ ጊዜያት የቆየ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት የቴሌኮም ኢንዱስትሪው በፍጥነት እያደገ ካለው የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ጋር በመዋሀድ ምክንያት እጅግ እየተወሳሰበና ዘርፈ ብዙ ስጋቶች እያስከተለ ይገኛል፡፡›› አዋጁ መግቢያውን ይቀጥልና በሌላ አንቀፅ እንዲህ ይላል ‹‹ለምሳሌ ያህል ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ፣ የብሔራዊ ደህንነት አደጋ ላይ መውደቅ፣ ዜጎች በመንግሥት ላይ አመኔታ እንዲያጡ ማድረግ፣ በተለያዩ የሽብር ሃይሎች መጠቀሚያ መሆን፣ ለሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር ይገኙበታል፡፡›› በእርግጥ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እያደገ መምጣት ነገሮች በአንድ መልኩ እየተወሳሰቡ እንዲሄድ ቢያደርግም በሌላ መልኩ ደግሞ ለጊዜ አጠቃቀም እንዲሁም ስራዎችን በቀላሉ ለመተግበር የራሱ የሆነ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን በባንኮች እየተዘረጋ ያለው የግንኙነት አውታር (Network) ስራን እንዴት የተቀላጠፈ እያደረገው እንደሆነ ስንገነዘብ ነው፡፡ ስለዚህ በአንድ ወገን የሚገኝ የደህንነት ጥበቃን በማሰብ በቴክኖሎጂው ላይ የመስፋፋት ክልከላ ከማድረግ ይልቅ የራሱን ቴክኖሎጂ ከጊዜው ጋር በማቆራኘት በሚደረግ ቁጥጥር መግታት የሚችልበት ሁኔታ ቢፈጠር በሁለቱም ዘርፍ ማለትም በተጠቃሚውም በተቆጣጣሪውም ወገን ቴክኖሎጂው የሚያድግበት መንገድ ይኖራል፡፡ ከቴክኖሎጂው ዕድገት የሚገኙትን ትሩፋቶችን በጥሩ ሁኔታ መጠቀምም ይቻላል፡፡ በመግቢያው ላይ እንደ ምክንያትነት የተጠቀሰው ሌላው አዋጅ ያስፈለገበት ምክንያት ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ነው፡፡ በሕገ-ወጥ መንገድ ከፍተኛ በሆነ ደረጃ የራስ ቴሌኮምንኬሽንን አቋቁሞ ያልተገባ ትርፍ ማግኘት የሚያደርሰው ኢኮኖሚያዊ ኪሣራ በዛ ያለ በመሆኑ በሕግ ክልከላ ቢደረግበት የሚያስኬድ ምክንያት ተደርጐ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ቢሆንም ይህ ሕገ-ወጥነት ለምን ሊመጣ ቻለ? የሚለውን ጉዳይም አብሮ መመዘኑ ግን ተገቢነት አለው፡፡ ረቂቅ አዋጁ ያተኮረው በመንግሥት ላይ በነዚሁ ሕገ-ወጥ የቴሌኮም ተግባራት እየደረሰ ያለውን ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ብቻ ሲሆን ቴሌኮም ራሱ ባስቀመጣቸው ውድ የስልክና ሌሎች በስሩ በሚተዳደሩ የግንኙነት ታሪፎች ምክንያት በኅብረተሰቡ ላይ የሚደርሰውን ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ትኩረት አልሰጠውም፡፡ ቴሌ በሞኖፖሊ በተቆጣጠረው የግንኙነት መስክ ውስጥ የክፍያ ታሪፎችን ባሻው መልኩ እንደፈለገ ከፍና ዝቅ ስለሚያደርገው በተለይ ዓለምአቀፍ ጥሪዎች ለማድረግ የሚጠይቀው ክፍያ የአብዛኛው ኅብረተሰብ ወደ ውጭ የሚያደርጋቸውን የስልክ ግንኙነቶች አሁን በረቂቅ አዋጅ ሕገ-ወጥ ተብለው በተቀመጡ ዘዴዎች እንዲጠቀም አስገድደውታል፡፡ ይህ የሞኖፖሊ ማርኬት መሰረታዊ ችግር እንደሆነ ሁሉም ኢኮኖሚስቶችን ያስማማል፡፡ መንግሥት የሚከራከርበትን ‹የወተት ላሟ› ቲዮሪ ወደጐን በመተው ተወዳዳሪ የቴሌኮም ተቋማት በዘርፉ የሚሰማሩበት ሁኔታ ቢኖር በቁጥጥሩ መስክ ብቻ በመሳተፍ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም ከግብርና እና ከሌሎች ክፍያዎች መሰብሰብ ይችል ነበር፡፡ የቴሌኮም የወንጀል ህጐችን ማውጣት መስኩን ለመቆጣጠር የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ ቢኖረውም ሕገ-ወጥ ዘዴዎች እንዳይስፋፉ መንግሥት ከነጋዴነት ራሱን በማራቅ በቁጥጥሩ ሂደት መሳተፍ ይገባዋል፡፡ የሕገ-ወጥነቱ ሁኔታ እየተስፋፋ መምጣቱ መንግሥት ከቁጥጥሩ ይበልጥ በሞኖፖሊ የመስኩ ብቸኛ ነጋዴ የመሆኑ ውጤት ነው፡፡ የቴሌኮም ዘርፍንም በተገቢው ሁኔታ እንዳያድግ ያደርገዋል፡፡ በመንግሥትና በዜጐች ሊደርስ የሚችለውንም ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ይቀንሰዋል፡፡

**በአንቀፅ 3 ውስጥ ከቴሌኮምንኬሽን መሳሪያዎች ጋር የተያያዘ ወንጀሎች በሚል በሕግ ከተፈቀዱት መሳሪያዎች ውጭ ይዞ መገኘት ከ10 እስከ 15 ዓመት ፅኑ እስራትና ከ100,000 እስከ 150,000 የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ያስቀጣል።**

ረቂቅ አዋጅ ለምን አስፈለገ? ለሚለው ጥያቄ ረቂቁን ያዘጋጀው አካል /መንግሥት/ ‹‹ሌላ ምክንያት አለኝ›› ብሎ በመግቢያው ላይ አስቀምጦታል፣ የብሔራዊ ደህንነት ጉዳይ የቴሌኮም ኢንዱስትሪው ሞኖፖሊ መያዙ ከላሟ የሚገኘው ወተት አመርቂ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ዋናው ጉዳይ የደህንነት አጀንዳ ነው ተብሏል፡፡ ባለሀብቶችን ወደዘርፉ ሳያስገቡ መንግሥት ለብቻው በተቆጣጠረው የቴሌኮም ኢንዱስትሪ ውስጥ ማናቸውንም ዓይነት የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ግንኙነቶችን ያለ ችግር መቆጣጠር ይቻላል፡፡ የግንኙነት መስመሮቹ ከመንግሥት እጅ ቢወጡ መንግሥት አሁን እንደሚያደርገው በፈለገው መልኩ በደህንነት ሰበብ ኢንዱስትሪውን በተቀላቀሉት የግል ባለሀብቶች ጣልቃ ለመግባት አይመቸውም፡፡ የሚፈልጋቸውን ግለሰቦች መከታተል፣ ግንኙነታቸውን መጥለፍ፣ የኢ-ሜይል አድራሻቸውን መበርበር እና መሰል ተግባራት መፈፀም ኢንዱስትሪውን ለግሉ ዘርፍ አሳልፎ ከሰጠ የማይሆን ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ለብቻው ከመቆጣጠር በተጨማሪ የዚህ ዓይነት አዋጆች እንዲያግዙት ማድረጉ የኢኮኖሚ ወይም የሌላ የዳቦ ሰዎች ፍላጐት ሳይሆን ስልጣንን የማስጠበቅና በመንግሥት ቋንቋ የብሔራዊ ደህንነት ጉዳይ ነው፡፡ የቴሌኮም ኢንዱስትሪው በተፈለገው መስክ እንዲስፋፋ አለመደረጉ አብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል ላይ ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ እያደረሰበት ሲሆን በኅብረተሰቡ መስዋዕትነትና በሀገር ደህንነት ሰበብ ቴሌኮም የስልጣን ማስጠበቂያ መሳሪያ ሆኗል ማለት ነው፡፡ በአዲሱ ረቂቅ አዋጅ መሰረት ያለፍቃድ የቴሌኮምንኬሽን አገልግሎት መስጠት ከ7 ዓመት እስከ 15 ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራትና በዚህ ሕገ-ወጥ ተግባር የተገኘው ገቢ ሶስት እጥፍ መቀጮ እንደሚያስቀጣ ሆኖ ተሻሽሏል፡፡

ሌላው አዋጁ ያስፈለገበት ምክንያት ተደርጐ በመግቢያው ላይ የተቀመጠው ጉዳይ በሌሎች የቴሌኮም ዘርፎች ምክንያት ‹‹ዜጐች በመንግሥት ላይ አመኔታ እንዲያጡ ያደርጋል›› የሚለው ነው፡፡ ከአንድ ወገን ብቻ የሚገኝ መረጃን መሰረት በማድረግ ዜጐችን በአንድ አቅጣጫ እንዲሄዱ ማድረግ በመንግሥት ላይ ዓመኔታ እንዳይኖራቸው ማድረግ ሳይሆን እውነታውን እንዲያውቁ አለማድረግ እና ከዓለም አቀፍ የግንኙነት አውታሮች ማራቅ ሲሆን በትክክለኛው ቋንቋ ደግሞ የዕውቀት ገደብ መፍጠር ወይም አፈና ነው፡፡ ዜጐች በመንግስት ላይ አመኔታ እንዲኖራቸው ከሁሉም በላይ መረጃ በበቂ ሁኔታ የሚያገኙበት መንገድ መመቻቸት አለበት ከዚህ ሌላ ራሱ መንግሥት ተዓማኒነት የሚኖራቸውን ተግባራት መፈፀም ይጠበቅበታል እንጂ ‹‹የእኔን ብቻ ስሙኝ ሌላውን አትስሙ›› የሚል አመለካከት አመኔታን አይፈጥርለትም፡፡ ‹‹ዜጐች በመንግሥት ላይ ለምን እምነት ያጣሉ?›› የሚለው ጉዳይ መንግሥታቸው በውስጡ የያዛቸው ግለሰቦችና የሚፈፅሟቸው ተግባራት አስረጂነት ሊመዘን ይችላል እንጂ በቴሌኮም ዘርፍ በሚደረግ ክልከላ ግቡን ሊመታ አይቻለውም፡፡ ነገር ግን በረቂቅ አዋጅ እንደ አንድ ምክንያት ተደርጐ ተቀምጧል፡፡

ረቂቅ አዋጁ በውስጡ የተለያዩ የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል ብሎ ያካተታቸው ድርጊቶች ይገኛሉ፡፡ በአንቀፅ 3 ውስጥ ከቴሌኮምንኬሽን መሳሪያዎች ጋር የተያያዘ ወንጀሎች በሚል በሕግ ከተፈቀዱት መሳሪያዎች ውጭ ይዞ መገኘት ከ10 እስከ 15 ዓመት ፅኑ እስራትና ከ100,000 እስከ 150,000 የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ያስቀጣል፡፡ አንቀፅ 4 የቴሌኮምንኬሽን አገልግሎት ከመስጠት ጋር በተያያዙ ወንጀሎች ደግሞ ከ7 እስከ 15 ፅኑ እስራትና በሕገ-ወጥ ተግባር የተገኘውን ገቢ ሶስት እጥፍ መቀጮ እንደሚያስቀጣ ሆኖ መሻሻሉን ይገልፃል፡፡ አንቀጽ 5 ከጠለፋና ተደራሽነት ጋር የተያያዙ ወንጀሎች ከ10 እስከ 15 ዓመትና 100,000 እስከ 150,000 በሚደርስ መቀጮ እንደሚያስቀጣ አርቅቋል፡፡ አንቀፅ 6 የቴሌኮምንኬሽን አገልግሎት ለሕገ-ወጥ ዓላማ ማዋል ከ3-8 ዓመትና ከ30,000-80,000 ብር በሚደርስ መቀጮ እንደሚያስቀጣ ይዘረዝራል፡፡ ኮልባክ (call back) /መልሰህ ደውልልኝ/ አገልግሎት ከ3 ወር እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ እስራትና ከብር 2,500-20,000 ብር በሚደርስ መቀጮ እንደሚያስቀጣ በአንቀጽ 9 ውስጥ የተቀመጠ ሲሆን ሕገ-ወጥ የቴሌኮም ኦፐሬተርን የሚመለከቱ ወንጀሎችና ሌሎች ከቴሌው ጋር የተያያዙ ወንጀሎች ከ3 ወር እስከ 2 ዓመት በሚደርስ እስራትና የገንዘብ መቀጮ እንደሚያስቀጡ ተዘርዝሯል፡፡ በሌላ ፅሁፍ እነዚህ ወንጀሎች ምን መልክ እንዳላቸው ለመዳሰስ እንሞክራለን፡፡ ቸር እንሰንብት፡፡

# ከከሰረው የትምህርት ፖሊሲ…

ኢህአዴግ፤ የትምህርቱን የጥራት ደረጃ ለዚህ ግቡ ሲል እየጨፈለቀው ስለመሆኑ ብዙ ምሁራን ይስማማሉ፡፡ ሀገሪቱ ካስቀመጠችው አነስተኛ ማለፊያ ነጥብ እጅግ ያነሰ ውጤት የሚያመጡ ተማሪዎች ከመጀመሪያ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ባሉት የትምህርት እርከኖች ቁጥራቸው እየበዛ መምጣቱ ሳያንስ፤ ወደ መሰናዶ ትምህርት የገቡት በሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ ወደ ዩኒቨርስቲ የሚገቡበት አሳዛኝ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ለየትምህርት ክፍሎቹ በማይመጥኑ መምህራን መማር፣ በአነስተኛ ደረጃ መሟላት ይገባቸው የነበሩት የትምህርት መሳሪያዎች እጦት አልፎም የአካዳሚያዊ ነፃነት በፖለቲካዊው ስርዓት በጥልቁ መጣስ፤ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መሰረታዊ መለዮ ሆኗል፡፡ የኢኮኖሚው የሰለጠነ የሰራተኛ የሰው ኃይል ፍላጐት ከሚሸከመው በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች መመረቅ፣ ከዚህ በባሰም የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ከሚጠይቁት የሙያ ክሂል በእጅጉ ያነሰው የምሩቃኑ አቅም፤ ኢትዮጵያን በተማሩ ስራ አጥ ወጣቶች እንድትሞላ እያደረጋት ነው፡፡ ኢህአዴግ ለነዚህ ስራ-አጥ ወጣቶች፤ በሀገሪቱ ክልሎችና ከተሞች ውስጥ ባሉ መንደሮች ድንጋይ ማንጠፍን ታላቅ የስራ እድል መስጠት አድርጎ ማሰብ የጀመረ ይመስላል፡፡ ከዚህ ቀደም፣ የተሻለ ስራ ፍለጋ ወደ ከተሞች የሚመጡትን የገጠር ወጣቶችና የጎዳና ተዳዳሪዎችን በማፈስ ጭምር ይህን ስራ እንዲሰሩ ሲያስገድድ የነበረው ኢህአዴግ፣ በከፍተኛ ትምህርት ያለፉ ወጣቶችን ወደዚህ ‹‹ስራ›› እስከማዛወር ደፍሯል፡፡

አካልን ክፉኛ በሚያዝል፤ ድንጋዩን ከካባ ፈልጦ የምትፈለገውን ተነጣፊ ድንጋይ ለማግኘት ለሚከወነው አታካች ሂደት የ17 ቀናት ስልጠና በቂ እንዳልሆነ የሚናገሩት የፕሮጀክቱ ሰራተኞች፤ ይህንንም ስራ ከመደራጀት ውጪ ሊሰጣቸው ያለመቻሉን በማንሳት ስርዓቱን ይወቅሳሉ፡፡ በዚህ ዓውድ ላይ፣ ሁለተኛ ዲግሪ ጭምር ያላቸውን ወጣቶች በዚህ የድንጋይ ማንጠፍ ስራ ላይ ማሰራማቱን ገዢው ፓርቲ እንደ ስኬት ቢያወራውም ፣ ለብዙ የሀገሪቱ የትምህርት ስርዓት ተከታታዮች ሁነቱ የፓርቲው የትምህርት ፖሊሲ ድቀት ጠርዝ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

# ኑ በአማርዝኛ…

ሲኮሩ … ያኔ ነው ስር መስደድ የጀመረው፡፡ እኔ የምለው በአንዳንድ ሀገሮች ማለቴ፣ በፈረንሣይ፣ በጃፓን በቻይና፣ . . . መሪዎች አትቀኑም? በትልልቅ አለምአቀፍ ስብሰባዎች ላይ በሀገራቸው ቋንቋ ሲናገሩ፡ ፡ እኔ እቀናለሁ፡፡ ለቅናት የዳረገኝን ገጠመኝ ደግሞ ላጫውታችሁ፡፡

የዛሬ አስር አመት ገደማ ነው፡፡ አውሮፓ ተማሪ እያለሁ አንድ ኔፓላዊ ጓደኛ ነበረኝ፤ መኖሪያችን አንድ ላይ ነበር፡፡ አንድ ቀን የተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ እየተካሄደ ሁለታችን ቡና እየጠጣን ቴሌቭዥን ስንመለከት፣ የሴኔጋሉ መሪ በፈረንሳይኛ ተናገሩ፡ ፡ ከዚያ ደግሞ የእኛ መሪ በእንግሊዝኛ ገና ንግግር ከመጀመራቸው ያ ኔፓላዊ ጓደኛዬ “ኦው! እናንተ ቅኝ የተገዛችሁት በእንግሊዞች ነበር እንዴ” አለኝ፡፡ ወይ ነዶ ወይ ጀግና አለማወቅ! ተቃጠልኩ፡፡ ልክ ልኩን ነገርኩት፤ በእንግሊዝኛ፡፡ “ሀገሬ የነፃነትና ያለመገዛት ምሳሌ ናት፡፡ የባንዲራችንን ቀለም በአፍሪካ የነፃነት ታጋዮች አርማ ውስጥ ፈልግ፤ ቢያንስ አንዱን ታገኛለህ” ብዬ ነገርኩት፡፡ ገረመው፡፡ ንዴቱ ወዲያው በረደ፡፡ ንዴቱ ሲበርድ ቅናት ጀመረኝ፡፡ በፈረንሳይ፣ በጃፓን፣ በቻይና … በሌሎቹም ሀገር ሰዎች መቅናት ጀመርኩ፡ ፡ ቀናሁ እንጂ ግን እነሱን መሆን አልተመኘሁም፡ ፡ በእንግሊዝኛም ቢሆን ኢትዮጵያዊነት ታላቅ ስሜት ይሰጣል፡፡ እዚያ የተሰበሰቡት መሪዎችም እኮ እንደ ጓደኛዬ የመሪያችንን የእንግሊዝኛ ንግግር ሲሰሙ በእንግሊዝ ቅኝ የተገዛን ሊመስላቸው ይቻላል! ይህን ሳስብ ደግሞ ተናደድኩ፡፡ ግን እኮ መሪዎቻችን በአማርኛ ቢናገሩ ቢያንስ ተሳታፊዎቹ “በምን ቋንቋ ነው ደግሞ የሚናገረው?” ብለው ይጠያየቁ ነበር፡፡ ወይም ደግሞ ከስብሰባው በኋላ “ጐግል” ከፈት አድርገው “አማርኛ” የሚባል ቋንቋ እንዳለ እሱም የኢትዮጵያውያን የጋራ መግባቢያ እንደሆነ ያውቁ ነበር፤ በርግጥ በማግስቱ ሊረሱት ይችላሉ፡፡

ጋዜጠኛው “what I mean is…” እያለ ቃለ መጠይቁን ለአማርኛ ተናጋሪ በእንግሊዝኛ “ግልጽ” አድርጐ ሲያቀርብ፣ ለዚህ አገላለጹ ሲሸለም፣ ያኔ ነው ችግሩ ስር መስደድ የጀመረው፡፡ ዛሬ ፍሬው ላይ ነን፡፡ የንግድ ፈቃድን ተመልከቱ፤ ኢንጂነሪንግ፣ ኢንፖርት-ኤክስፖርት፣ ኤጀንሲ … የሚል ቃል ለሌላው የንግድ ድርጅት ስያሜ የሚመለከተው ክፍል ፈቃድ መስጠት ያቆመ ይመስላል፡፡


ይህ ጉራማይሌ ቋንቋ የጉራማይሌ አስተሳሰባችንና ኑሮአችን መገለጫ ነው፡፡ አንድ ማህበረሰብ ጉራማይሌነት የሚገንበት ደግሞ አንድም፣ ሀገሪቱ በምትከተላቸው ፖለቲካዊ፣ ማህበረ-ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች ችግር፣ አልያም ፖሊሲውን ከሚያስፈጽመው አካል ብቃት ማነስ ነው፡፡ የሀገሬ ችግር ሁለተኛው ይመስለኛል፤ የአስፈጻሚ አካል ብቃት ማነስ! ሁኔታውን የፖሊሲ ችግር የሚያደርጉት አሉ፡፡ እኔ በዚህ አልስማማም፡፡ የፖሊሲ ችግር ነው ለማለት እኮ ቢያንስ ፖሊሲው ተፈጽሞ ማየት ያሻል፡ ፡ እኔ በአግባቡ የተፈጸመ የመንግስት ፖሊሲ ያለ ስለማይመስለኝ “ፖሊሲዎቹ አስፈጻሚ ርቧቸዋል” እላለሁ፡፡

ግን የቋንቋና ባህል ጉዳይ ማንን ነው የሚመለከተው? “በቋንቋህ ተግባባ“ ብሎ ላደለው ሀገርማ የመገናኛ ብዙሀን ለቋንቋ አጠቃቀም ሽንጣቸውን ገትረው ሙግት ይቆማሉ፡፡ የሀገሬ መገናኛ ብዙሀን በዚህ ረገድ ያላቸውን አዎንታዊ ድርሻ ለመጥቀስ ግማሽ ምእተ-አመት ወደሁዋላ መሄድ ያሻል፡፡ በዋናነት ችግሩ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴርን የሚመለከት ይመስለኛል፡፡ እነሱም ቢሆኑ ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ድምጽ ያለው ጩኸት አሰምተው አላዳመጥኩም፡፡ በስራ አጋጣሚ የተዋወቅን አንድ የባህልና ቱሪዝም መስሪያ ቤት ወፈር ያለ ክፍል ሀላፊ፣ “ይህ ችግር እንዴት ነው መስሪያ ቤታችሁን አይመለከትም እንዴ?” ብዬ ብጠይቀው “እኛ እንኳን ዋናው ጉዳያችን ባህል ነው፤ ቋንቋው እምብዛም አይመለከተንም” ቢለኝ፤ ባህል የቋንቋ ልብሷን አውልቃ፣ እርቃኗን፣ ምንተእፍረቷን አጋልጣ፣ ፊቴ ቆማ ታየችኝና የሰፈራችን እብድ ይርገዱ ትዝ አለችኝ፡፡

“እድሜ ዘልዛላው ስንቱን አሳየኝ” ይሉ የነበሩ አያቴ ትዝ ሲሉኝ፣ እድሜን ዘልዛላ የሚያሰኘው መርዘሙ ይመስለኝ ነበር፡፡ ዘልዛላ ዘመን ያደለው እድሜ ገና በአስራ አምስት አመቱም ቢሆን ይንዘላዘላል፡፡ አያቱ ለሞታቸው በፀለዩበት እድሜ ያላዩትን ጉድ በአስራ አምስት አመቱ ያያል፡፡ ምን የተንዘላዘለ እድሜ ቢቸረኝ ባህልን ከቋንቋ አፋቶ የሚያለማ የባህልና ቱሪዝም መስሪያ ቤት የስራ ሀላፊ አያለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም፡፡ ምን የተንዘላዘለ እድሜ ቢኖረኝ መሀል አዲሳባ “ጬንበለላ፣ ሚሚ ቂጦ የባህል ምሽት ቤት” የሚባል መጨፈሪያ ቤት አያለሁ ብዬ አልሜ አላውቅም፡፡

የመጨፈሪያ ቤቱን ስያሜ አንስቼ፣ “ግን ይህ ነገር የእናንተን መስሪያ ቤት አይመለከትም ነው የምትለኝ?” ብዬ ያንኑ የስራ ሀላፊ ብሞግተው፣ “ሊመለከተን ይችላል፤ አየህ ነገሩን በባህላዊ ፈርጅ ካየኸው አግባብ ላይሆን ይችላል፡፡ ግን ደግሞ የሌላውን ሰላማዊ ኑሮ እስካላናጋ ድረስ አንድ ሰው ለድርጅቱ የወደደውን ስም ሊሰጥ ይችላል” አለኝ፡፡ እንዲያ ነው! ጎሽ! ‹‹የሰላማችን መናጋት መለኪያው ምንድነው?›› እራሴን ጠየኩ፡፡ ህብረተሰቡ ነውር ነው ብሎ በልጆቹ ፊት የማይጠራው ቃል /ቂጦ/ በአደባባይ ተለጥፎ ሲመለከት ሰላም አይነካም መባሉ ይደንቃል፡፡ መቼም ቋንቋ ሲነውር ህሊናን ያደማል እንጂ ጥይት ተኩሶ አያቆስል! … እና ለዚህ ነው “ያለን አስፈጻሚ አልባ ፖሊሲ ነው” ማለቴ፡፡ ሰላም ከጥይት ጩኸት ጋር ተቆራኝቶ ሲበየን፣ ሰላም ማጣት የአካል ጉዳት ብቻ ይሆናል፡፡ ያኔ “አድዮስ” የህሊና ሰላም!

# ኪነጥበብ



# ፔዳል ዴሞክራሲ 7

## የተሸጠ መንፈስ...

ገጣሚ ኤፍሬም ስዩም

ባዶ ቦታ አለ አንድ የሆነ ክፍተት የሆነ ቦታ ላይ። ችግሩ ክፍተት እንዳለ ይታወቃል እንጂ ሥፍራው የት እንደሆነ አይታወቅም። ...ይሄ ስሜት ከባለፀጋ እስከ ደሃ... ከምሁር እስከ ሰነፍ... ከአራዳ እስከ ቀሽም... በየሁሉም ልቡና የሚመላለሥ ሥሜት ነው... ቦታው የማይታወቅ ስሜት...

የዚህ ዘመን ወጣት (የኔ ትውልድ) መንፈሱ የተሸጠ ነው። ነገር ግን በሸጠው መንፈስ ምንም አልገዛበትም፣ ምንም በእጁ ላይ የለም። በሁሉም ነገር ደስተኛ አይደለም። መንፈሱን ሸጦ ምንም የያዘ ሰው ምን ሊያስብ ይችላል?። ምንም።

መንፈሳችን የት ነው? መቼ ሸጥነው? መንፈሳችንን ሳንስማማ የገዛን ሰውስ ምን ተጠቀመ? ይህ የብዙ ሰው ጥያቄ ነው። ለማንም የሚቀርብ በስውር መንፈሳችንን የገዛን ሰው የሚመልሰው ጥያቄ...

የዚህ ዘመን መንፈስ ጥቅሙ ምንድ ነው? የሚል ነው። የሁሉም ነገር ጥቅም በሚመልሰው ዋጋ ላይ የተመሰረተ ነው። ግን የመንፈስ ዋጋው ስንት ይሆን?

የሕይወታችሁን ዋጋ የሚያስከፍል ሥራ ብትሠሩ ምላሻችሁ የቅስም ስብራት ነው። ‹‹ሥንት አገኘህበት›› የሚል። ምንም የማያስገኝ ብዙ የሚቸር ተግባር አለና..

የመንፈሥ ሥጦታዎች የጥልቅ ሥሜት ጥበቦች ዋጋቸው ንዋይ አይደለም። ከገንዘብ በላይ ለሆኑ ጥበቦች ብዙ ገንዘብ ቢተመንባቸው ዕንኳ ያ ዋጋቸው አይደለም። ችግሩ ታላላቅ ጥበቦች ታላላቅ እውነቶች የዋጋቸው ማነስ ሳይሆን አብዛኛው ሕዝብ ከሚመለከተው ነገር፣ ከሚያነበው ፅሑፍና በእጁ ላይ ካለው መጽሐፍ ማወቅና መረዳትም ሆነ ሥሜትንና እውነትን መጋራት አይፈልግም። ሁሉም የሚፈልገው ‹‹ትክክል አለመሆናችሁን ማረጋገጥ ነው›› ከተሠጠው ይልቅ ያልተሠጠውን የሚጠይቅ።

እንዲህ ዐይነት አስተሳሰብ የመንፈስ በሽታ ነው። የተሸጠ መንፈስ ምልክት አንድ ሕዝብ በፅኑ ደዌ ሊመታ ሲል (ሲመታ) የጉንፋን ምልክቱ የመልካም ነገርን ጣዕም መለየት አለመቻል ነው። ለትውልድና ለሀገር የሚበጁ ሃሳቦች ሲፃፉ ‹‹ጥቅሙ ምንድነው?›› ከተባለ፤ የዛ ሀገር ባህል በሽታ ላይ ወድቋል ማለት ነው።

ለአንድ ሕመምተኛ ሠው ከሕመሙ በላይ ሕመም የሚሆነው የበሽታውን ዐይነት አለማወቅ ነው። ብዙ ሕሙማን ከወደቁ በኋላ ወደ ሕክምና ሥፍራ የሚሄዱት የሕመማቸውን ዐይነት (ስያሜውን) ማወቅ ባለመፈለጋቸው ነው። የሕመምን ዐይነት ማወቅ እንኳ አንድ ሕክምና ነው፤ ሐኪም ባይችለው ጠበል ዕድሉ ነውና።

አንድ ሀገር ሲታመም የመጀመሪያ ምልክቱ የሚታየው ባሕሉ ላይ ነው። ባሕል የተለምዶ ጉዳይ ሳይሆን ነፍስ መልእክቷን የምታስቀምጥበት ሰሌዳ ነው።

የኛ ሀገር ሕፃን እንደተቸከቸከበት የስዕል ካንቫስ ሆኗል። አሳዛኙ ነገርም ሆነ ታላላቅ ዋጋ ይዞ የሚገኘውም፤ ይሄ አላዋቂ የሰራው ስዕል መሆኑ ነው። ለዚህ ነው መልካም ነገርን እንዳናጣጥም፣ በዕውቀትም ሆነ በማስተዋል ከፍ ሊያደርጉን የሚችሉትን ነገሮች መፀየፋችን ‹‹የተሸጠ መንፈስ›› የሚያሰኘው።

ጥያቄው ግን ‹‹ዋጋ ልንሰጣቸው የሚገቡትን ነገሮች ዋጋ እንዳንሰጣቸው ዐይኖቻችን ወደ ብርሃን እንዳይመለከቱ፣ አዚም አድርጎ የማይረባንን እንድንሸምት፣ በሚያጠፉን እንድንደሰት፣ ያታለለን የመንፈስ ነጋዴ ደላላው ካድሬ ማነው?›› እንድንል የሚያደርገን...

ሀሳባችንን በጽሑፍ እንዳንገልፅ እያስፈራራ መንፈሳችንን ለማስፈራራት በመሞከር፣ ምንም የሆነ ሐሳቡን አቀብሎ ማንነታችንን ለማሸማቀቅ መሞከር ‹‹ከዚያ በኋላስ?›› ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ሳይኖረው የነፍስን ጉልበት አራት በአራት ሣጥን መሰል ቤት ውስጥ ለማሸግ መሞከር ስንፍና ነው። የማይረባውን ለመዝራት ስንዴውን መንቀል አልያም ዓረም ለመሰብሰብ የወይን ዐፀድ መሰባበር፤ አዕምሮውን የታመመ ገበሬ መንገድ ነው።

ወንጀልና ወሲብን በተመለከተ የሚፃፉ ፅሁፎች ቁጥር አንድ ተመራጮች ናቸው። ለእንደዚህ ዐይነት ሥራዎች አራጋቢው ሁሉም ነው፣ ሁሉም። ችግሩ የኢትዮጵያን ሕይወት በቺቺኒያ ሴቶች ውስጥ ለማሳየት መሞከሩ አይደለም። ችግሩ ‹‹እንዲህ ዐይነት የመንፈስ ውድቀት የተፈጠረው ያቺ ሀገር ምን ዐይነት አስተዳደር ቢኖራት ነው?›› ብላችሁ ስትጠይቁ አፋችሁ መለጎሙ ላይ ነው።

በዘመን ላይ መንፈስ ሲሸጥ መጠየቅ አይፈቀድም፣ መፃፍ አይፈለግም፤ ብትፅፍ የሚፈለገው ሁኔታውና ውጤቱ እንጂ ምክንያቱ አይደለም።

የሚፈለገው የኑሮ ውድነትን ለአንድ ሰዓት ተኩል የሚያስረሳ ሳቅ ወይም፣ ለግጥ ያለው ፊልም (ኮሜዲ) እንጂ ‹‹የኑሮ ውድነት ለምን?›› የሚል ጥያቄ አይደለም እዚህ ሀገር ላይ ሁሉም ባለማወቅ ፈገግ ብሎ መሞቱ ያሳዝናል። በፈገግታ መሰናበት።

የቧልት መንፈስ ያለው ሠው ከጀርባው ታላቅ ሀዘን ያለበት ሰው ነው። ድፍረት ከፍርሃት ማህፀን እንደምትወለድ ሁሉ፣ ቧልተኛም ከታላቅ ሀዘን ምንጭ ይፈሳል ‹‹ሣቃችሁ በግልፅ የሚታይ ሀዘናችሁ ነው›› እንዲል ካህሊል ጂብራን ይህ ማለት ኮሜዲ (ለግጥ) የዚህ ዘመን መንፈስ መገለጫ ማለት ነው? በዘመኑ ታላቅ ሀዘን አለ ማለት ነው። ‹አሌ ለክሙ›።

መንፈሳችን እየተቸበቸበ ነው። በየመንገዱ መሬት ላይ የተደረደሩትን መፃህፍት ተመልከቱ። የጫት ቤቶችን ብዛት ተመልከቱ። የመጻህፍት ቤቶችን ብዛት ተመልከቱ (ድንቄም እቴ) ¡¡¡...

ታላቁ ሀዘን የዋጋ መጠን በሌለው በተሸጠው መንፈሳችን የጨበጥነው ዕብቅ መሆኑ ነው። በመንፈስ ደላላዎች ዘንድ የሚፈለገው ይኸው ነውና!

በገንዘብ ደሃ መሆን የሀገሪቷ መገለጫ ነው። ግን ‹‹በመንፈስም ጭምር ድሆች እንሆን ዘንድ ዘሩን ማን ዘራው?›› ነው ጥያቄው። ዋጋ በማይከፈልበት ዋጋ ከፍለን እንደኸይ ዘንድ ተገደናል ተደፍረናልም...

‹‹ሴቶችን የማማለል ዘጠኝ ጥበቦች›› የሚል ፅሑፍ ዶክተር የሚል ቅጥያ ካንጠለጠለ ወገበ ነጭ ይፃፋል። አቧራ ዘርቶ ዕብቅ የሚሰበስብ ሐሳብ።

በዚህ የነፍስ ገበያ ላይ አብዛኛው ነጋዴ ይዞ የሚወጣው፤ ውጤቱ ዜሮ የሆነ ለሀገርም፣ ለወገንም ለራሱ ለፀሐፊውም ጭምር ኋላ ላይ በሽታ የሚሆነውን የበሽታውን ምልክት ነው።

‹‹እውነት እነዚህና ይህንን የመሳሰሉ ፀሐፍት በቤታቸው መደርደሪያ ላይ ራሳቸው የተረጎሟቸውና የፃፏቸው መጽሐፍት ተቀምጠዋል?›› ሐሰት። አያደርጉትም ‹‹ለምን ሌላው ላይ (ሕዝብ ላይ) ለልጆቻችሁ የማታስቡትን ታደርጋላችሁ ብላችሁ ብትጠይቁ?›› መልሳቸው...

‹‹ሕዝቡ የሚወደውና የሚፈልገው ይህንን ነው ይሏችኋል››። አራት ነጥብ ግን...

ለሕዝቡ ጣፋጭ ስኳር ብቻ ቢሆን ማር ማስለመድ (ማስለመድ ባይቻል ማቅመስ) ማንን ገደለ? ሁሉንም...

እንግዲህ የምሁራንም ሆነ የሕዝባውያን የዚህ ዘመን መገለጫ አቧራ ዘርቶ ዕብቅ መሠብሰብ ነው።

ሀሳባችንን አባ ዮሐንስ የተባለ መነኩሴ ጉባዔ ጥሎና እውቀት አሻፈረኝ ብሎ ከኮበለለ ተማሪው ጋር ባደረገው መራር እውነታ እንሠረው።

በአንድ ወቅት አባ ዮሐንስ በመንገድ ላይ እየተጓዙ ሣለ የቀድሞ ተማሪውን (ትምህርቱን አቋርጦ ጠፍቷል) ጎዳና ላይ ተቀምጦ ዋዘኛ ሆኖ በጊዜና በራሱ ሕይወት ላይ ተጋድሞ አገኘው። ሠላምታ ከተለዋወጡ በኋላ...

‹‹ልጄ አሁን ምን እየሰራህ ነው?›› አባ ዮሐንስ ጠየቁ

‹‹ምንም... አባቴ ምንም››

‹‹ምንም ካልሠራህ ታድያ ትምህርቱን ለምን አቋረጥክ?››

‹‹ቤተሰቤን የምረዳበት፣ እናቴን የምጦርበት ገንዘብ የሚያስገኝ ስራ እሞክራለሁ ብዬ ነበር... ሁሉም አልተሳካም›› ተማሪው መለሰ

መነኩሴው አባ ዮሐንስ መጎናፀፊያቸውን ወደ ትከሻቸው እየመለሱ ‹‹ልጄ ድሮ ሳውቅህ ጉባዔ ላይ ጎበዝ ተማሪ ነበርክ፣ ጭንቅላትህ ፈጣን ነበር፣ ትምህርትህስ ተቋርጧል ግን መጻሕፍትን ታነባለህ ወይ?›› አሉና ጠየቁት።

የቀድሞው ተማሪም የራስ ፀጉሩን እየፈተለ ‹አዬ አባቴ ምን በልቼ?› ብሎ መለሰላቸው።

አባ ዮሐንስም ‹‹ምን በልቼ? ታዲያ ምን በልተህ ደደብ ሆንክ?›› አሉና መንገዳቸውን ቀጠሉ። ተማሪውም ፀጉሩን እያሸ መንገድ ጠርዝ ላይ ያለው ጉብታ ላይ ተቀመጠ።

አባ ዮሐንስ፤ በመንገዳቸውና በየጉብታው ላይ ተግባር ፈተው፣ ከዕውቀት ተፋተው ወይ ከትምህርታቸው ወይ ከሀሳባቸው ሳይሆኑ የተሸጠ መንፈሳቸውን የሚፈልጉ ስንት የቀድሞ ተማሪዎቻቸውን ያገኙ ይሆን? ጎዳናው ይመስክር።

ምንም ያልገዛንበት የተሸጠው መንፈሳችን ይህንን ይመስላል ‹‹ከእግር እስከ ራስ ሁሉም የታመመበት›› የኢትዮጵያ ደማቅ ስዕል።





# አዲስ መጽሐፍ በገበያ ላይ ዋለ

አከፋፋይ አይናለም መጽሐፍት መደብር አድራሻ ብሔራዊ ቴያትር ጀርባ


## ሰመጉ ከኢሰመኮ ጋር አድርጎት የነበረው የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት አለመከበሩን አስታወቀ

ሐምሌ 29 ቀን 2003 ዓ.ም. የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ /ሰመጉ/ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን /ኢሰመኮ/ ጋር አድርጎት የነበረው የሕግ ድጋፍ አገልግሎትን የተመለከተ የመግባቢያ ሰነድ እስከአሁን ድረስ አለመከበሩን ትናንት በጽ/ቤቱ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ አስታወቀ።

ጋዜጣዊ መግለጫውን ለጥቂት የግል ጋዜጦች የሰጡት የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር አቶ እንዳልካቸው ሲሆኑ ስምምነቱን ለመፈራረምና ተግባራዊ ለማድረግ ዓለም አቀፍ የልማትና የለጋሽ አገራትና ድርጅቶች ተሳትፎ እንደነበረበት በመግለጫው ተገልጿል።

ከበጐ አድራጎት ድርጅቶች አዋጅ 627/2001 መታወጅ በኋላ ሰመጉ እና መሰል የሰብዓዊ መብት ተቋማት 90 በመቶ ገቢያቸውን ከሀገር ውስጥ ለመሰብሰብ መገደዳቸውን የጠቆመው መግለጫው፣ ኢሰመኮ ከዓለም አቀፍ ማህበረሰብ የሚገኙ እርዳታዎች ለእነዚህ ተቋማት በማስተላለፍ እንዲደግፍ የታለሙ የፕሮጀክት ስምምነቶች ሰመጉን ጨምሮ በኢሰመኮ እና በሌሎች ተቋማት በወቅቱ መደረጉ ተዘርዝሯል።

ይህ የለጋሽ አገሮችና ድርጅቶች እያዋጡ ያሰባሰቡት ፈንድ እንደ ሀገር ውስጥ ፈንድ ተደርጐ እንዲቆጠርና ይህንን ፈንድም ኢሰመኮ ተረክቦ ከሌሎች በሰብዓዊ መብት ነክ ጉዳዮች ላይ ከተሰማሩ የሀገር ውስጥ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ስምምነት እያደረገ እንዲያካፍል ስምምነትና መግባባት እንደነበረ መግለጫው ጠቁሟል።

ሆኖም ሰመጉ ሰነዱን ከፈረመ በኋላ በ2003 እና 2004ዓ.ም ዓመታዊ እቅድና በጀቱ ውስጥ አካትቶ ተግባራዊነቱን ሲጠብቅ መቆየቱን እና ከላይ ለተጠቀሰው የሕግ ድጋፍ ፋይናንስም ከሌላ ምንጭ ማፈላለጉን እንዳቆመ ተገልጿል።

ጉባዔው ባላወቀው ምክንያት በኢሰመኮ ስምምነቱ እስከአሁን ድረስ ሳይከበር ስለቀረ እና ኢሰመኮም ለዚህ ምክንያት መስጠትም ሆነ መወያየት ስላልፈለገ ጉዳዩን ይፋ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ እንዳገኘው አስረድቷል።

በመጨረሻም ዳይሬክተሩ ከጋዜጠኞች የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ምላሽ ሰጥተዋል።

## ኢራፓ በወላይታ ዞን ስብሰባ አደረገ

የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ክልል በወላይታ ዞን በዳሞት ጋሌ ወረዳ በቦዲቲ ከተማ ሰኔ 23 ቀን 2004 ዓ.ም ከህብረተሰቡ ጋር ውይይት አደረገ።

ፓርቲው በእለቱ የተከናወነውን ስብሰባ ለማደናቀፍና የስብሰባው ተሳታፊዎችን ለማስደንገጥ የቦዲቲ ከተማ ፖሊስ ሞክሮ እንደነበር ተገልጿል።

በወቅቱ በተደረገው ስብሰባ ላይ ከተሳተፊዎች የተነሱ በርካታ ጥያቄዎችን የፓርቲው ዋና ፀሐፊ እና በወላይታ ዞን የፓርቲው አመራሮች መልስ ሰጥተዋል ሲል ፓርቲው ለፍትሕ አስታውቋል።

## የጋዜጣና የመጽሔቶች የማስታወቂያ ይዘት 60 በመቶ ሆኖ ፀደቀ

‹‹በጋዜጣና መጽሔት ላይ የሚተላለፉ ማስታወቂያዎች የህትመት ሽፋን ከ70 በመቶ መብለጥ የለበትም።›› በሚል ለተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ የነበረው ረቂቅ የማስታወቂያ አዋጅ በትላንትናው ዕለት የተወካዮች ም/ቤት ስብሰባ እንደገና ‹‹ከእያንዳንዱ እትም ጠቅላላ የህትመት ሽፋን ከ60 በመቶ የሚበልጠውን መያዝ የለባቸውም›› በሚል ተሻሽሎ ፀድቋል።

## የአካባቢ ጥበቃን በማስመልከት የፎቶ ግራፍ ኤግዚቢሽን ሊካሄድ ነው

‹‹ግላመር ኢሜጅ ፎቶ ጋለሪና ስቱዲዮ›› የዘንድሮውን የአካባቢ ጥበቃ ቀን በማስመልከት ለሁለተኛ ጊዜ ያዘጋጀው በአይነቱና በይዘቱ ለየት ያለ የፎቶ ግራፍ ኤግዚቢሽን ሐምሌ 2 ቀን 2004 ዓ.ም. አምስት ኪሎ በሚገኘው በብሔራዊ ሙዚየም ከቀኑ በ10:30 ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት የሚከፈት መሆኑ የተገለፀ ሲሆን ዓውደ ርዕዩም ለቀጣይ አስራ አምስት ቀናት ክፍት ሆኖ ይቆያል።

## ‹‹የተከፈለበት›› ፊልም ሰኞ ይመረቃል

በሜሮን ጌትነት ተደርሶ በሦስትዮሽ (ሜሮን ጌትነት፣ ቶማስ በየነና ዮሐንስ ገ/አብ) የተዘጋጀው ‹‹የተከፈለበት›› የተሰኘው ፊልም ሰኞ ሐምሌ ሁለት ቀን 2004 ዓ.ም. ከምሽቱ 11:30 ላይ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ጥሪ የተደረገላቸው የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎችና የፊልም አፍቃሪዎች በተገኙበት በድምቀት ይመረቃል።

በየዘም መልቲ ሚዲያ ፕሮዳክሽን በኩል ተዘጋጅቶ የቀረበው ይኸው ፊልም በዘውጉ ከሮማንቲክ ድራማ የሚመደብ ሲሆን አንጋፋና ወጣት ተዋንያን ተሳትፈውበታል።

## ግራና ቀኝ የተሰኘ የመድረክ ቴአትር ነገ ይመረቃል

በአርቲስት ዘነበ ተስፋዬ (ዲንጎ) የተደረሰውና በአላዛር ሳሙኤልና ቅድስት ገ/ሥላሴ በጋራ ተዘጋጅቶ በ‹‹ጥሩ አየሁ ፕሮሞሽን ስራዎች›› ፕሮዲውስ የተደረገው ‹‹ግራና ቀኝ›› የተሰኘ የመድረክ ቴአትር በነገው እለት ከቀኑ 7:00 ጀምሮ ጥሪ የተደረገላቸው ባለስልጣኖች፣ አምባሳደሮች ታዋቂ ግለሰቦች፣ አርቲስቶችና ጋዜጠኞች በተገኙበት በአዲስ አበባ ባህልና ማዘጋጃ ቤት በደማቅ ስነ-ስርዓት ይመረቃል።

ከስድስት በላይ ተዋንያን የተሳተፉበት ይህ ቴአትር አንድ ሰዓት ከአርባ አምስት ደቂቃ የሚፈጅ ሲሆን ተሰርቶ ለመጠናቀቅ የሶስት ወር ጊዜ እንደወሰደ አዘጋጆቹ ለፍትሕ ገልፀዋል።

# በአዲስ አበባ መዲና የአፍሪካ ሕብረት መንግስታት የመንገድና የመሬት ስሪት ታሪክ

**ከ1955-1996ዓ.ም በአዲስ አበባ ማዕከልነት የአፍሪካ ሕዝቦች የነፃነት ትግልና ድል በተሳካ ሁኔታና መንገድ በመጠናቀቁና በምትኩም የአፍሪካ መንግስታት ሕብረት (AU) በመመስረቱ ምክንያት ከተማውም እንዲሁ ቋሚ መቀመጫ እንዲሆን በህብረቱ መንግስታት ተወስኗል።**



ከፕ/ር ላጵሶ ጌ.ድሌቦ
የታሪክ ተመራማሪና ደራሲ

መግቢያ፣

በ1996-1998ዓ.ም የሽግግር ዘመን በከንቲባ አርከበ ዕቁባይ የተመራው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመማክርት ጉባኤውና በምሁራን ትምህርትና ምክር የከተማውን ነባር የቀበሌ፣ የከፍተኛና የማዕከላዊ ምክር ቤት፣ የኢኮኖሚ ታዕታይና የፖለቲካ ላዕላይ መዋቅሮችን በአዳዲስ ተስማሚ የአገር ግንባታ መሣሪያዎችና ድርጅቶች በመተካት እንዲሁም በመዲናው ለአፍሪካ ሕብረት መንግስታት የመንገድና የመሬት ስሪት በመስጠት ከተማውን የኢትዮጵያ ሪፐብሊክና የአፍሪካ ሕብረት መንግስታት ጥምር የጋራ መዲና አደረገው።

በሌላ በኩል ደግሞ ነጻነት እና ዳኝነት በኢትዮጵያ የተሰኘውና በ2002ዓ.ም የታተመው መጽሐፍ ደራሲ አቶ ስየ አብርሃ በመዲናው የ1996ዓ.ም የአፍሪካ ሕብረት መንግስታትን የመንገድና የመሬት ስሪት ምስረታ ተግባርና ታሪክ በተመለከተ በታሪክ መረጃና ትምህርት ያልተመዘነ አስተያየት እና የታሪክ ክፍተት በይፋ ስለፈጠሩ ለፍትህ ጋዜጣ አንባቢያን ግምገማና ግንዛቤ የመንግስታቱ የመንገድና የመሬት ስሪት ተግባርና ታሪክ ሙሉ ቃል ከዚህ መግቢያ ቀጥሎ ቀርቧል።

1. የታሪክ ግድፈት

ነጻነት እና ዳኝነት በኢትዮጵያ የተሰኘውና በ2002ዓ.ም የታተመው መጽሐፍ ደራሲ አቶ ስየ አብርሃ በአዲስ አበባ መዲና የ1996ዓ.ም የአፍሪካ ህብረት መንግስታትን የመንገድና የመሬት ስሪት ምስረታ በተመለከተ በመዲናው ከንቲባ በአቶ አርከባ ዕቁባይ (1996-1998) ላይ የሚከተለውን ያልተጣራ አስተያየት ሰንዝረዋል። በመጽሐፉ ገጽ 195-196 ላይ እንደተባለው፣

"አቶ አርከባ ዕቁባይ ለአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባነት የተሾመ ጊዜ ለአፍሪካ ህብረት መንግስታት መሬት ይሸነሽን ነበር። ጥንታዊና ታሪካዊ መጠሪያቸውን እየቀየረም ለአፍሪካ አገራት በየስማቸው ጎዳና ይሰይም ነበር። ለኢትዮጵያ አርበኞች በመታሰቢያነት የተሰየሙ ጎዳናዎች ሳይቀሩ ስማቸው እንደተቀየሩ ይነገራል። የአድዋ መቶኛ አመት የድል በአል ሲከበር አድዋ አካባቢ ይህንን የሚያስታውስ ሀውልት እንዲሰራ ፕሬዝዳንት ነጋሶ ጊዳዳ መሠረት እንዳስቀመጡ ሁሉ፣ አቶ አሊ አብዶ የአዲስ አበባ ከንቲባ በነበሩበት ጊዜ አዲስ አበባ ላይም ቦታ ተመርጦ ፕሬዝዳንት ነጋሶ ለአድዋ ድል መታሰቢያ ሀውልት ግንባታ የመሠረት ድንጋይ አኑረው ነበር። አቶ አርከበ ይህንን ለሀገራችን ታሪክና ለኢትዮጵያዊያን ተጋድሎ ትልቅ ፋይዳ ያለውን የመታሰቢያ ሀውልት ወደጎን ትቶ ለአድዋ ድል መታሰቢያ የታሰበውን አካባቢ ለመንገድ ሥራ አውሎታል፣ ቅያሪ ቦታም ሳይመድብ ቀርቷል።

"የአድዋ ድል ለኢትዮጵያውያንና ለመላው ጥቁር ሕዝብ አኩሪ የሆነውን ያክል ለጣልያኖች እና ለዘረኞች በጠቅላላ አሳፋሪ በመሆኑ የአድዋ ድል መታሰቢያ ሀውልት አዲስ አበባ ላይ እንዳይሰራ የጣሊያን መንግስት ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለው ይታወቃል። ይህንን ታላቅ ገድል የሚዘክር የሀውልት ሥራ ቀርቶ ለዚሁ የተመደበው ስፍራ ለሌላ ሥራ እንዲውል መደረጉ ምናልባት ከጣሊያኖች ዲፕሎማቲክ ጫና ጋር ተያይዞ ይሆን? የሚል ጥያቄ ያስነሳል።"

2. የአዲስ አበባ መዲና ክስተትና ሚና በአፍሪካ የነጻነት ታሪክ

የአፍሪካ የአርነትና የአብዮት መዲና

በ19ኛው ምዕተ ዓመት በኢትዮጵያ አፄ ነገስታት ቴዎድሮስ፣ ዮሐንስና ምኒልክ መሪነትና አዝማችነት ለአገሪቱ ጥንታዊ፣ ማዕከላዊና በሀውርታዊ የአፄው መንግስት የፖለቲካ ተሃድሶና ምእክልና በውስጥና በውጭ ተጻራሪ ኃይሎች ላይ የተሳካ እንቅስቃሴ ተካሄደ። በእንቅስቃሴው ዘመንና ሂደት በ1879 ዓ.ም የአዲስ አበባ ያገር መዲናነት በጠንካራ የገባር ኢኮኖሚና ሥርዓት በአፄ ምኒልክ ተመሠረተ። በዘመነ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ አገር ግንባታ ተግባርና ሂደትን በሚመለከት፣ በትምህርትና በሥራ ምክንያቶች ለረጅም ጊዜ (1958-1968) ከኖርኩበት አሜሪካን አገር በእናት አገር ጥሪ ከተመለስኩ በኋላ "የአዲስ መዲና ዕድገትና ሚና በኢትዮጵያ ታሪክ" በሚል የጥናት ርዕስና ድባብ በመዲናው ውስጥ ከደጃች ውቤ ሰፈር ጀምሮ እስከ ፖሊስ ጋራዥ ድረስ እንዲሁም በታሪካዊ የፊኒፊኔ ስምጥ ሸለቆ ውስጥ ከፍተኛ 2፣ 13 እና 14 በተሰኙ አዲስ የከተማ አስተዳደር ክልሎች የናሙና ጥናት ለማካሄድ በሰኔ 1970ዓ.ም ለኢትዮጵያ አዲሱ የባህል ሚኒስቴርና ለአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ባቀረብኩት አዲስ የጥናት ቢጋር (ፕላን) መሠረት የከተማዋ የመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ክብረ በዓል በህዳር 1979ዓ.ም በአገር አቀፍ ደረጃ በድምቀት እንደተከበረ ይታወሳል። በጥናቱ ቢጋር እንደተባለው፣

"የአዲስ አበባ ከተማ መቶኛው ዓመት ክብረ በዓል ከዛሬ አሥር ዓመት በኋላ በ1979ዓ.ም በታላቅ ብሔራዊ ስሜትና ክብር እንደሚከበር ይጠበቃል። ይህ የአዲስ አበባ መዲና ያለፈው ዘጠና ዓመታት ተግባርና ታሪክ በአጠቃላይ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ድምር ያገር ተግባርና ታሪክ ነው። በዚህ አዳጊና ታሪካዊ በሆነው ያገር መዲና አንድ መቶ ዓመት ባልሞላው አጭር ዘመን ውስጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በቅደም ተከተል የመደባዊ ባርነትና የሕዝባዊ አርነት ዘመናት ፈረቃ በትግልና ድል ገድል አይቷል። አሳልፏል።

በዚህ ያገር ግንባታ ዘመንና ታሪክ በ1966ዓ.ም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት እንደእሳተ ጎሞራ ከፈነዳ ወዲህ የአዲስ አበባ መዲና በሀውርታዊ ውህድና ጀግና ሕዝብ በፊታውራሪነት ከውስጥና ከውጭ ተፃራሪ ኃይሎችና ወኪሎች ጋር ሲፋለም መዲናውን በጉልበቱና ባፈሰሰው ክቡር ደሙ የተከበረ አገራዊና ሕዝባዊ ቅዱስ ስፍራ የሰማዕታት ምድርና መዲና አድርጎ ገንብቶታል።

ከመዲናው ፈጣን የታሪክ መነሻና ሂደት አኳያ በዝርዝር ሲታይ ከ1879-1933ዓ.ም ዘመን የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስትና ሕዝብ በሕይወትና በንብረት ታላቅ ዋጋ ከፍለው የአገሪቱን ነፃነትና ብሔራዊ አንድነት ከዓለማቀፋዊ የኢምፔሪያሊዝምና የፋሺዝም ኃይሎች ሕብረ ሴራና ወረራ አዳኑ። ከ1933-1966 ዓ.ም የአዲስ አበባ መዲና በአፄው ማዕከላዊ መንግስት አመራር በዓለማቀፋዊ የኢምፔሪያሊዝምና የፋሺዝም ኃይሎች አገዛዝ ላይ ለአፍሪካ አህጉራዊ ነፃነት የፖለቲካ መሠረትና ማዕከል ተደረገ። በመሆኑም ከ1955-1996 ዓ.ም ነፃ የአፍሪካ መንግስታት የአዲስ አበባ መዲናን የአፍሪካ ቋሚ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ማዕከል አድርገው መረጡት።

በኢትዮጵያ የ1966-1983ዓም ሕዝባዊ አብዮት ክስተትና ሂደት ከ1969-1996ዓም የአዲስ አበባ መዲና በ1,200,000 የሚቆጠሩ ነዋሪዎች በ284 የቀበሌ፣ በ25 ከፍተኛና በአንድ ማዕከላዊ የኢኮኖሚ ታዕታይና የፖለቲካ ላዕላይ መዋቅሮችና እርከኖች ተደራጅተው ለኢትዮጵያ የሪፐብሊክ ሥርዓት ግንባታ የፖለቲካ መነሻ፣ መሠረትና መሣሪያ ሆኑ። በመጨረሻ ከ1996-1998 ዘመን፣ በከንቲባ አርከባ ዕቁባይ መሪነት የአዲስ አበባ መዲና በአስር ቋሚ የፖለቲካ ላዕላይ መዋቅሮችና በ49 የኢኮኖሚ ታዕታይ ድርጅቶች ማለትም በአስር ተደራጀ።

3. በአዲስ አበባ መዲና የአፍሪካ ህብረት መንግስታት የመንገድና የመሬት ስሪት ታሪካዊ ፋይዳ

የኢትዮጵያ የአፄው ማዕከላዊ መንግስት ህዳሴና የ1900-1966 የሥርዓተ ገባር ክስተትና ውድቀት

ከዛሬው የቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር 3744 ከ1996-1998ዓ.ም የሽግግር ዘመን የአዲስ አበባ መዲና አስተዳደር የመማክርት ጉባኤ አባል በመሆን ከትምህርትና ከፖለቲካ ስርዓት አኳያ ተግባራዊ ተሳትፎና የግንዛቤ አስተዋጽኦ በቃልና በጥናት አድርጌያለሁ። በዚህ ረገድና ተግባር በሚያዝያ 5 ቀን 1996ዓ.ም ከከንቲባ አርከባ ዕቁባይ ጋር ባደረኩት የግል ውይይት በአሜሪካ የዋሽንግተን ዲ.ሲ. መዲና የመንገድ፣ የአደባባይና የድልድይ ግንባታ፣ ስያሜና አገልግሎት መልካም ምሳሌ በማንሳትና በማስረዳት ተናገርኩ።

ብሎም በኢትዮጵያ ሪፐብሊክም የአዲስ አበባን መዲና መሰል መንገዶች፣ አደባባዮችና ድልድዮች ግንባታ፣ ስያሜና አገልግሎትን በተመለከተ በቋሚና ዘላቂ የአገር መሪዎች፣ የፌደራልና የክልል አገሮች እንዲሁም የአፍሪካ ህብረት መንግስታት እንዲሰየሙ ቢደረግ አገራዊና ዓለማቀፋዊ ፋይዳ ይኖረዋል በማለት የግንዛቤ ሀሳብና ምክር አቀረብኩ። ከንቲባውም ምክሬን ተቀብለው ጉዳዩን በጥናታዊ ጽሑፍ አዘጋጅቼ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዳቀርብ ጠየቁኝ።

በመሆኑም በሚያዝያ 8 ቀን 1996ዓ.ም የአዲስ አበባ መዲና መንገዶችን በአፍሪካ ሕብረት መንግስታት መሰየም የኢትዮጵያ መንግስትና ሕዝብ በአውሮፓውያኑ ኮሎኒያሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ላይ ለአፍሪካ ሕዝቦች ነፃነትና አንድነት በረጅም ዘመን ላደረገው የፖለቲካ ትግልና ድል ሕያው መታሰቢያ የሚሆን ገድል እንደሆነ በመግለፅ በኢትዮጵያ የትግልና ድል ታሪክ ላይ ከዚህ የሚከተለውን ጥናት አዘጋጅቼና ለክቡር ከንቲባው አቅርቤ በተግባር ላይ መዋሉን በደስታ አስታውቃለሁ። የጥናቱ ሙሉ ቃል፣

ከታሪክ፣ ከጊዜና ከተግባር አኳያ ሲታይ፣ ከ1524-1543ዓ.ም የአዳሉ ኢማም አህመድ ቤን ኢብራሂም አሊ.ጋዝ የአመጽ ጦርነትና ተዛማጅ የ1520-1855 ዘመን የኢትዮጵያ ታላቁ የሕዝቦች የፍለሳና የሰፈራ፣ የመስተጋብርና የመወራረስ እንቅስቃሴ ከአገር ውስጥ፣ የፖርቱጋሎችና የቱርኮች ዓለማቀፋዊ የፖለቲካ፣ የትጥቅና የባህል ግፊት ደግሞ ከውጭ በአንድነት ዘመን በኢትዮጵያ ጥንታዊ የአፄው ማዕከላዊ መንግስት ላይ ረጅም የገለልተኝነትና የውድቀት ተፅዕኖ እንዳስከተሉ የታሪክ መረጃና ትምህርት ያሳያል።

በሌላ በኩል ከ1600-1855ዓም የጦርነት ዘመንና ሥርዓት በጎንደር፣ በሸዋና በትግራይ የፖለቲካ ኃይሎችና ክልሎች በየበኩላቸው በጥንቱ አፄ ነገስታት የአገር ግንባታ ፖሊሲና ተግባር መሠረት በመላው ሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍል አህጉር የኢትዮጵያ ጥንታዊና ማዕከላዊ የአፄው መንግስትን በተሃድሶ ፖሊሲና በምዕክልና ፖለቲካ መልሶ ለመገንባት የጋራ ራዕይና ተልዕኮ አንግበው እንደተነሱ የታሪክ መረጃችና ያሳያል።

ይህ የኢትዮጵያ የአካባቢ ኃይሎች የአገር ግንባታ ፖሊሲና እንቅስቃሴ በጅምር ደረጃ እያለ በ19ኛው ምዕተ ዓመት ከ1820ዎቹ መባቻ ጀምሮ የአካባቢ ወራሪዎችና የአውሮፓ የካፒታሊዝም፣ የኮሎኒያሊዝና የኢምፔሪያሊዝም ኃይሎች በተናጠልና በሕብረት የአባይ ሸለቆ፣ የቀይ ባህር፣ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍል አህጉርና የሕንድ ውቅያኖስ እስትራቴጂያዊ አካባቢዎችን ለመያዝና ለመቆጣጠር በኢትዮጵያ ላይ ለረጅም ዘመን የሚቆየውን የወረራ ፖሊሲና ተግባር ከፈቱ። ጀመሩ።

በዚህ ዓለማቀፋዊ የአውሮፓውያኑ ወረራ ከ1600-1855ዓ.ም ድረስ በጎንደር፣ በትግራይና በሸዋ ክልሎች የአገር ግንባታ ራዕይና ተልዕኮ አንግበው የተነሱ የኢትዮጵያ ክርስቲያን የፖለቲካና የሀይማኖት ኃይሎች በአፄ ነገስታት ቴዎድሮስ፣ ዮሐንስና ምኒልክ ተከታታይ መሪነትና አዝማችነት በአንድ በኩል መላ የአገሪቱን ሕዝቦች የአካባቢ፣ የዘር፣ የቋንቋ፣ የባህልና የሀይማኖት ምርጫና ልዩነት ሳይደረግ በአንድ ጥንታዊና ማዕከላዊ የአፄው መንግስትና ሥርዓት ሥር የማደራጀትና የማማከል ፖሊሲና ተግባር፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአገሪቱን መንግስታዊ ህልውናና ብሔራዊ ነፃነት ከወራሪ ኃይሎች ሕብረ-ጥፋት አዳኑ።

4. የአውሮፓውያንና የአፍሪካውያን የኃይል ሚዛን በአድዋ ተራሮችና ሸለቆዎች ወሳኝ ጦርነት

በየካቲት 23 ቀን 1888ዓ.ም በዳግማዊ ምኒልክ መሪነትና አዝማችነት እቴጌ ጣይቱን ጨምሮ በአስራ አንድ የአገርና የጦር መሪዎች የተመራው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገስት መንግስት፣ ሕዝብና ሠራዊት በ1884ቱ የበርሊን ፀረአፍሪካ ጉባኤ ውልና ውሳኔ መሠረት በአውሮፓና በአሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግስታት ፖሊሲና ፖለቲካ የተደገፈውንና በአምስት ጀኔራሎች የተመራውን የኢጣሊያ ወራሪ ጦር በታላቁ የአድዋ ጦር ሜዳ በመደምሰስ በምንም ሥፍራና ጊዜ የተደራጀ ሕዝብ ከወራሪ ኃይሎችና ሥርዓቶች የበለጠ ኃያልና ድል አድራጊ መሆኑን ሰለባ ለሆኑና ለሚሆኑ የዓለም ሕዝቦች በተለይ ለአፍሪካ ሕዝቦች በተግባር አሳየ። ተዛማጅ የበርሊን እ.አ.አ 1884ዓ.ም፣ የውጫሌ የ1889 ውሎችንና ውሳኔዎችን በአድዋ ጦር ሜዳ በትግልና ድል ደመሰሰ።

ከየካቲት 23 ቀን 1888ዓ.ም የአድዋ ድል በኋላ የኢትዮጵያ፣ የአድዋና የምኒልክ ስሞችና ስራዎች በአፍሪካና በመላ ዓለም የወራሪና የዘረኝነት ኃይሎችና ሥርዓቶች ሰለባ ለሆኑ ጥቁር ሕዝቦች የትግልና ድል፣ የነጻነትና የክብር ስሞች፣ ምሳሌዎችና ምልክቶች ሆኑ።

ከታላቁ የአድዋ ድል በኋላም በአገሪቱ በሰሜንና በምስራቅ የባህር ጠረፎች አራት እስትራቴጂያዊ አካባቢዎችን ማለትም "ኤርትራ"፣ "የፈረንሳይ ሶማሊያ ላንድ"፣ "የእንግሊዝ ሶማሊያ ላንድ" እና "የኢጣሊያ ሶማሊያ ላንድ" አሰኝተው ከአያሌ ብሔረሰቦችና ማህበረሰቦች ከሰፋሪ ጦር ጋር በመሆን ለዘለቄታው የያዙት የፈረንሳይ፣ የእንግሊዝና የኢጣሊያ የቅኝ ገዥ መንግስታት እንደወቅቱ ሁኔታና ፖሊሲ በተናጠልና በሕብረት በኢትዮጵያ ውስጣዊ ጉዳዮች ላይ ጣልቃ በመግባት ለአገሪቱ የፖለቲካ ሰላምና የልማት ስራ ቋሚ እንቅፋቶች ሆኑ። በመጨረሻም በ1927ዓም ከዘመኑ የዓለም መንግስታት ማህበር ጋር የእንግሊዝና የፈረንሳይ መንግስታት የኢትዮጵያን ሉአላዊ አገርና መንግስት ለኢጣሊያ ፋሺስቶች ወረራና ግዛት በይፋ አሳልፈው ሰጡ።

በአውሮፓና በአሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግስታት ቁጥጥር ስር በሆነው ዓለም ላይ ከ1927-1933 ዓ.ም የኢጣሊያ ፋሺስቶች የወረራ ሰለባ ከሆኑ ኢትዮጵያውያን ጎን ተሰልፈው የአፍሪካ ሕዝቦች በአህጉሩና በመላ ዓለም በኢምፔሪያሊዝም ኃይሎች ላይ ዓለም አቀፍ የተቃውሞ እንቅስቃሴ አካሂደዋል።

በ1933ዓ.ም በእንግሊዝ የኮመንዌልዝ ጦርና በኢትዮጵያ አርበኞች ሕብረት የኢጣሊያ ፋሺስቶች በተደመሰሱ ጊዜ በእንግሊዝ ጦር ውስጥ የተሰለፉ የሱዳን፣ የናይጄሪያ፣ የጋና፣ የኬንያና የደቡብ አፍሪካ ወታደሮች ኢትዮጵያን ከፋሺዝም-ኢምፔሪያሊዝም ኃይሎች ነፃ ለማውጣት በተደረገው ፍልሚያ ታላቅ አፍሪካዊ የትግልና የድል አስተዋጽኦ አድርገዋል።


5. አዲስ አበባ የአፍሪካ የነፃነትና የአንድነት መዲና

በ1938ዓ.ም የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን (ተመድ) በአሜሪካ ሳንፍራንሲስኮ ከተማ ከመሰረቱት የዓለም መንግስታት አንዱ የኢትዮጵያ መንግስት ነው። ከ1938ዓ.ም ጀምሮ በቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ መሪነት የኢትዮጵያ መንግስት በተመድ መድረኮችና ስብሰባዎች፣ በአውሮፓ ኢምፔሪያሊስት መንግስታትና ኃይሎች ላይ የአፍሪካ ሕዝቦችንና አገሮችን የፖለቲካ ነፃነት ጥያቄ የራሱ ሕዝብና አገር ጉዳይ እንደሆነ አድርጎ ከመታገሉ የተነሳ በቅደም ተከተል በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ ለሁለቱም ማለትም ለተመድ የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን (ECA) እና ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት (OAU) መዲናነት አዲስ አበባ ዋና መቀመጫ ሆኗል።

ከ1955-1996ዓ.ም በአዲስ አበባ ማዕከልነት የአፍሪካ ሕዝቦች የነፃነት ትግልና ድል በተሳካ ሁኔታና መንገድ በመጠናቀቁና በምትኩም የአፍሪካ መንግስታት ሕብረት (AU) በመመስረቱ ምክንያት ከተማውም እንዲሁ ቋሚ መቀመጫ እንዲሆን በህብረቱ መንግስታት ተወስኗል።

በዚህ ረገድና ተግባር በሀያኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ በአፄ ኃይለ ሥላሴ "የአፍሪካ አንድነት አባት" የፖለቲካ ጥበብ፣ ግርማና ሞገስ እንዲሁም ኢትዮጵያ በአፍሪካ ሕዝቦች ዘንድ በዓለማቀፋዊ ደረጃ ከፍተኛ ተቀባይነት ባገኘው በአገሪቱ ልዩ የታሪክ ቅርስና ውርስ መልካም ተፅዕኖ ምክንያት እንደሆነ የኢትዮጵያ መንግስት፣ ህዝብና ህብረተሰብ አጠንክሮ ማወቅ የሚገባው የአገርና የሕዝብ መሠረታዊ ጉዳይ ነው።

በመሆኑም የአዲስ አበባ ታላላቅ መንገዶች፣ አደባባዮችና ድልድዮች ስያሜ፣ የሚገባቸው...



እንዳለጌታ ከበደ

# ታማሚዋ አገራችን ያልዳነችው በመድሃኒት አወሳሰድ ችግር ይሆን?

እምን፤ እንዲህ ነው የሚሰማኝ፤ ‹‹ለምንድነው ይህቺ አገር ከተጣባት ድኅነት እና ጉስቁልና ነፃ መውጣት ያቃታት?›› የሚል ጥያቄ ወደህሊናዬ ሲመጣ፤ በመድሃኒት አወሳሰድ ችግር ይሆን እላለሁ፤ ቢሆን ነው እንጂ ድህነትን እያፈረችበት፤ በብልፅግና ጉዳና ለመራመድ ግን ‹ወገቤን› ማለት የምታበዛው?

ሰሞኑን እንደዚህ ስላሉ ጉዳዮች ሳስብ የአንዲት እናት የቀድሞ ልማድ ትዝ አለኝ፤ ይህቺ የልጆች እናት ቀለም የዘለቃት አይደለችም፡፡ ብዙ ያልተለመዱ ድርጊቶችን በመከወን በእናቴ፣ በጐረቤቶቿ እና በዘመድ አዝማዶቿ ዘንድ ትታወቃለች፡፡ የታመመን ተመላልሶ በመጠየቅ የሚያክላት የለም፡፡ በእሷ ልክ ታማሚዎችን በጥያቄ የሚያስጨንቅ የለም፡፡ የሚሏትን ሁሉ በጥንቃቄ አዳምጣ በልቦናዋ የመመዝገብ ችሎታ አላት፡፡ ያለአንዳች ቸልተኝነት ታማሚን ተመላልሳ የምትጠይቀው፤ ማለትም ‹ሲጀምር እንዴት አረገህ? ሃኪምስ ምን አለህ? ምን አይነት መድሃኒት አዘዘልህ?› እና ሌሎችም አሰልቺ የሆኑ ይህን የመሳሰሉ ጥያቄዎችን የምትጠይቀው፤ ለታማሚው ተቆርቁራ አይደለም፤ የሷ ጉዳይ ሌላ ነው፤ ከእያንዳንዱ የአልጋ ቁራኛ አንድ ነገር መመጽወት ትፈልጋለች፤ እሱም መድሃኒት ነው፡፡

ይህቺን ነገር ሳብራራት፡ ወደ ታማሚው ቤት ገብታ ስትወጣ ባዶ እጇን አይደለም፡፡ ሕመምተኛውን ለምና፤ ተለማምጣ ወይም አንዳች ዘዴ ዘይዳ፤ ሃኪም ካዘዘለት ክኒኖች ሶስት አራት ፍሬዎችን ትቀበላለች፤ ‹እኔንም አንተ እንደሚያደርግህ ያደርገኛል› ብላ፡ ብዙዎቹ - ልክ እንደሷ መሠረታቸው ገጠር ነውና - አያሳፍሯትም፡፡ በእርግጥ የተቀበለችውን መድሃኒት ወዲያው አትወስደውም፤ ‹አንተን እንደሚያደርግህ ያደርገኛል› የምትለውም እውነቷን አይደለም፤ መድሃኒቱ ለአሁን ባይጠቅመኝ ለአንድ ቀን ይጠቅመኛል ብላ ነው እንጂ፡ ክኒኑን በወረቀት ጠቅልላ፤ ቤቷ ወስዳ አንድ ተለቅ ያለ ብልቃጥ አላት፤ እዚያ ውስጥ ትጨምረዋለች፡፡

እንዲህ እንዲህ እያደረገች - ከዚህም ከዚያም እየለማመነች - ያጠራቀመቻቸው ብዙ ዓይነት መድሃኒቶች አሏት፡፡

ከቤተሰብ መካከል ለምሣሌ ልጇ በሽታ ጥሎት አልጋ ላይ ከወቀደ፤ የህክምና ባለሙያ የሚጠይቀውን ዓይነት ጥያቄ ትጠይቀዋለች - ከዚያ በኋላ ያንን ብዙ የመድሃኒት ዓይነቶች የተጠረቃቀመበትን ብልቃጥ አውጥታ - ‹አዎ ይኼ ነው መድሃኒቱ፤ እንቶኔ ሲታመም ይህንን ውጦ ነው የተፈወሰው፤ ስለዚህ ሀኪም ቤት ሄጄ ወጪ ከማወጣ ለምን ይህን አላስውጠውም?› ብላ ትወስናለች፤ ታደርገዋለችም፡፡

በቃ እንዲህ ናት፤ ይኼ ነገር እውነት ነው፤ የፈጠርኩት ወይም ተፈጥሮ የቆየኝ አይደለም፡፡ ለብዙ ጊዜ ሲገርመኝ ቆየና ሰሞኑን ደግሞ ከእናቴ ጋር ስሚን አንስተን ስንሳሳቅ ቆየንና - ይህን እና ይህን የመሳሰሉ ድርጊቶቿን ዙሪያችን ላሉ ሰዎች ስናካፍል ቆየንና - አንድ ነገር ተገለጠልኝ፡

ይህቺ እናት፤ ኢትዮጵያ፣ የኢትዮጵያ መሪዎች እና ፖሊሲ ቀራፂዎቿ መስላ ታየችኝ፡፡ ይህቺ አገር አንድ ችግር ሲገጥማትና አንድ ሕመም ‹ሰውነቷን› ሲቆጣጠረው ሕመሟ ፖለቲካዊም ይሁን ኢኮኖሚያዊ ወይም ማኅበራዊ፤ ለሕመምዋ መድሃኒት የምትፈልገው ውጭ አገር በመሄድ ነው፤ ተመሣሣይ ርዕዮተ ዓለም አለን ብላ ወደምታምንባቸው አገሮች በመዝለቅ፡፡ የሌሎችን ሕመም እንደራስ በመቁጠር ሳይሆን ሕመማቸውን ከራሳችን ሕመም ጋር በማመሳሰል እና ‹ቁርጥ እንደ እኛ ነበር የሚያደርጋቸው› በሚል ሰበብ ‹መድሃኒታቸውን› እንጐመጃለን፤ እንቀላውጣለን፡፡

ለችግሮቻችን መፍትሔ ይሆኑናል ብለን ያመንባቸው እና እንከኖቻችንን ለማከም የምንውጣቸው ክኒኖች በአብዛኛው በልመና ያገኘናቸው ናቸው፤ ተረድተን፤ ደጅ ጠንተን፤ ‹‹ስለምንተማርያም›› ብለን የተመፀወትናቸው፡፡ የሚያሳፍረው ደግሞ እነዚህ መድሃኒቶች በህክምና ባለሙያዎች የታዘዙልን አይደሉም፤ በድፍረት ነው የምንወስዳቸው፤ እኛው ላይ ሞክረን ነው ለውጥ አላመጣ ሲሉን ንቀን የምንተዋቸው፡

እነሱን ፈውሶ ጤናማ ያደረገው መድሃኒት ለእኛ ላይሰራ ይችላል፤ እንደ አኗኗራችን፤ እንደ ነባር የጤና ሁኔታችንና እንደ ሰውነታችን አቅም ነውና፤ መድሃኒት በሙያተኛ የሚታዘዝልን፡፡ ሌላው ይቅር፤ ስንት ጊዜ ነው፤ የትምህርት ስርዓታችን የተለዋወጠው? ስንት ጊዜ ነው፤ አምና የለወጥነውን የመማር የማስተማር ሂደት ትተን፤ ‹‹የለም፤ አምና ከኮረጅነው የእነ እገሌ አገር የትምህርት አካሄድ ይልቅ የእንቶኔ መንገድ ነው አገራችንን ከሰለጠኑት አገራት ተርታ የሚያሰልፋት›› የሚል ቃል ከመሪዎቻችን አንደበት ያደመጥነው? ይህ ድርጊት- ያለምርመራ እና ያለ ባለሙያ ምክር መድሃኒት ከመውሰድ በምን ይለያል? እስከመቼ ድረስ ነው፤ ቀኑ ያለፈበት መድሃኒት እንድንውጥ የምንገደደው? ለምንድነው ለችግሮቻችን መፍትሔ የማፍለቅ አቅም ያላቸውን የአገር ውስጥ ሞያተኞችን ድምፅ የማንሰማው?

እንዳየነውና ስንኖር እንደታዘብነው፤ ከውጭ ያላመጣናቸው ሀገር በቀል እውቀቶች ናቸው፤ ብዙውን ጊዜ ሕዝቡን ቀጥ አድርገው እያኖሩ ያሉት፡ እነዚህ ማኅበራዊ ተቋማት በሕዝቡ ውስጥ ስር ለሰደዱ በሽታዎች መድሃኒት ሆነዋል፤ የኢኮኖሚ ችግር ሲኖር ብቻ ሣይሆን የመንፈስ አለመረጋጋት፣ የመፅናት እና የመፅናናት ችግር ሲያጋጥም፤ እንደማኅበር፣ ሰንበቴ፣ ዕድር እና እቁብ የመሳሰሉት ማህበራዊና ሃይማኖታዊ ተቋማት ናቸው፤ የታማሚውን ጉድለት የሚሞሉት፡፡ እነዚህ ለጥቂት፤ ሕመሞቻችን የምንወስዳቸው ክኒኖች ናቸው፡፡ ለሌሎች ሕመሞቻችን የሚሆኑ ብዙ መድሃኒቶች አሉ፤ ብንፈልግ አናጣቸውም በየባህሉ፣ በየብሔሩ፡፡

አዎን፤ ወደራስ የመመልከት እና ‹ያገሩ ሰርዶ ባገሩ በሬ› የሚለውን ብሂል የመከተል ችግር አለብን፡፡ ውሸት ነው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ወፍ እንዳገሯ አትጮህም፡፡ ውሸት ነው፤ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ እንደ ጐረቤቱ እንጂ እንደራሱ እየኖረ አይደለም፡፡ የመጣንበትን መንገድ አንወደውም፤ የመጣንበትን መንገድ መለስ ብለን ብናይ እንደ ሎጥ ሚስት ደርቀን ተገትረን የምንቆይ ይመስለናል፡፡ እንዲህ ባይሆን ኖሮማ፤ ለበሽታዎቻችን ምን አይነት መድሃኒት መውሰድ እንዳለብን የሚያውቁ ጉምቱ ሽማግሌዎችንና ምሁራንን እንሰማ አልነበር? እኛ ግን እነዚህን ‹አያውቁም፤ ቢያውቁም ዕውቀታቸውን አናውቅላቸውም› ብለን ንቀን የተውናቸው ይመስላል፡፡

የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፍልስፍና መምህር የሆኑት ዶ/ር በቀለ ጉተማ፤ ስለ እነዚህና ስለ አፍሪካውያን ፈላስፎች ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል፡ "…ትምህርት ቤት ገብተው የተማሩ አይደሉም፤ ግን አዋቂዎች ናቸው፡፡ ማወቅ ማለት የግድ ፊደል መቁጠር ማለት ስላልሆነና እነዚህ በኑሯቸው፣ በባህላቸው፣ ባላቸው ስርዓት መሠረት የራሳቸው አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች በመሆናቸው፡ እነዚህ ሰዎች እኛ ይኼን እናውቃለን ብለው ለሰዎች ለማስተማር አይሄዱም፤ ወይም አንተ ምን ታስባለህ ብለው ሄደው እንደ ሶቅራጥስ አይጠይቁም፡፡ ግን ባሉበት ሕብረተሰብ አዋቂዎች እንደሆኑ ይታወቃል፡" (መዝገበኞች - ግንቦት 2004ዓ.ም)

እምነት የለንም፤ የሰለጠነ የሚመስለን ከውጭ አገር የመጣ ሞያተኛ ነው፡፡ ከበሽታችን የምንድን የሚመስለን ፤ ተመርምረን ሰውነታችንን አስፈትሸን መድሃኒት ሲታዘዝልን ሣይሆን፤ የውጭውን ሰው መድሃኒት- ስንቀላውጥ ነው፡፡ ከውጭ የለመንነው - የድህነታችንና የድንቁርናችንን ሰንኮፍ ነቅሎ ይጥላል ብለን የምናምንበት ይህ መድሃኒት፣ አንድ ጊዜ ወይም ሁለቴ ከወሰድነው በኋላ ይዞን ሊሄድ ይችላል፤ ቀደም ሲል ይዞን ከነበረ በሽታ ጋር መታረቅ አቅቶት፡፡ በሽታችንን እጥፍ ድርብ አድርጐ ከአገልግሎት ውጪ ሊያደርገንም ይችላል - ቀን ያለፈበት ክኒን ሆኖ፡፡

እነዚህ ለችግሮቻችን ፍቱን ናቸው ተብለው - በመንግሥት መልካም ፍቃድ ወደ አገር ውስጥ ስለገቡ ክኒኖች - መንግሥት በራሱ ሚዲያዎች ይደሰኩርልናል፤ ጋዜጠኞችም በገባቸው ልክ ይተነትኑልናል፡፡ ድህነትና ድርቁርናን ድል ስናደርግ የምንዘምረውን መዝሙር ከወዲሁ ያስጠኑናል፡፡ ስለ አዲሱ የመፍትሔ ሃሳብ ልቃወም ብሎ ለሚነሳሳው ደግሞ አዲስ ስድብ ቀደም ብሎ ተዘጋጅቶ ይቆየዋል፡ ታክመን ድነናል የሚሉ ምስክሮችም ይዘጋጃሉ፤ ለአዲሱ መድሃኒት ውዳሴ ሲጐርፍለት ይቆይና፤ ብዙም ሳንቆይ ‹በአፈጻጸም ችግር ነው› ተብሎ፤ ይኼ የመፍትሔ ሃሳብ ተትቶ፤ አሁንም የጤንነታችን ሁኔታ በባለሞያ በቅጡ ሳይመረመር ወደ ሌላ አገር ይኬዳል፤ ሁለት ክኒን ልትሰጠኝ ትችላለህ ለማለት፤ በሽታህ ከበሽታዬ ጋር አንድ አይነት ነውና ለማለት፡፡

… ብዙ ናቸው ችግሮቹ፤ ለዚህም ነው ይህቺን አገር ከዚያች የገጠር ሴት ጋር ማመሳሰሌ፤ ለዚህም ነው ይህቺ አገር ድና ቀና ብላ ከጤነኞች እኩል መራመድ ያቃታት በመድሃኒት አወሳሰድ ችግር ይሆን ወይ ብዬ መጠየቄ፡፡

በነገራችን ላይ ይህቺ ከታመመ ሰው መድኃኒት እየለመነች፤ የለመነችውን እያጠራቀመች፤ ያጠራቀመችውን ደግሞ ቤተሰብ በታመመ ቁጥር እያስዋጠች … ትኖር የነበረችዋ ሴት፤ አሁን ይህንን ልመናዋን ትታዋለች፤ ልጆቿ ደረሰው የተማሩ ሆኑላትና፤ ያንን የመድሃኒት ብልቃጥ ሽንት ቤት ውስጥ እንድትጨምረው አድርገዋል- ከብዙ ውትወታና ተግሳፅ በኋላ፡፡

ኢትዮጵያስ? የኢትዮጵያ መሪዎችስ? ፖሊሲ ቀራጺ ልጆቿስ?

> እነዚህ ለችግሮቻችን ፍቱን ናቸው ተብለው - በመንግሥት መልካም ፍቃድ ወደ አገር ውስጥ ስለገቡ ክኒኖች - መንግሥት በራሱ ሚዲያዎች ይደሰኩርልናል፤ ጋዜጠኞችም በገባቸው ልክ ይተነትኑልናል፡፡ ድህነትና ድርቁርናን ድል ስናደርግ የምንዘምረውን መዝሙር ከወዲሁ ያስጠኑናል፡

# ክፍተቱና ለውጡ...

ከነቀነቀለት በኋላ ገፍቶ የጣለው ደርግ በለውጥ ወደ ኋላ መሄድ እንደሚቻል አሳይቶናል፡፡ ደርግ ዘውዳዊውን አገዛዝ ማስወገዱ ባይከፋም ራሱን በቦታው መሰየሙ ግን ‹‹ታላቅ ጥፋት›› ነበር፡፡

የደርግ መንግስት ‹‹የወታደሮች ስብስብ›› እንጂ ምንም አይነት የጠለቀ የፖለቲካ፣ የአስተዳደርና የዲፕሎማሲ እውቀት እንዳልነበረው ቀጥለው የተከሰቱት ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ዝቅጠቶች በቂ ማሳያዎች ናቸው፡፡

እናማ ወጣቱ በተስፋ የታገለለት የዜጐች ውድ ህይወት የተከፈለበት ትግል ውጤቱ በጉልበተኞች እጅ ወደቀና ‹‹የአሁኑ ይባስ›› የሚያስብል ሆነ፡፡ የጊዜውም ወጣት ሁኔታውን በመመልከት ለሌላ ትግል ራሱን ማዘጋጀት ቀጠለ፡፡

ኧረ ጥራኝ ጫካው
ኧረ ጥራኝ ዱሩ እያለ፡፡
ዛሬ

የትጥቅ ትግልም ሆነ ሰላማዊ የፖለቲካ ተቃውሞ በሚያራምዱ ቡድኖች ውስጥ በነቢብ የሌለ በገቢር ግን ተዛንፎ የማያውቅ አንድ ሕግ ያለ ይመስላል፡፡ ‹‹ሕዝብ ወደ ዓላማችን መሸጋገሪያ ድልድይ ነው፤ ከድላችን በኋላም ወደ ቀደመው የባርነት ግዛቱ ይመለሳል›› የሚል፡፡

ስለዚህም ነው ተራራው በመንቀጥቀጡ፣ ኮሎኔሉ በመፈርጠጡ ያተረፍነው የሀገር መቆረጥ፣ የፖለቲካ ከሃይማኖት መቃየጥ፣ በየዘርፉ ባሉበት መርገጥ፣ አንድ ወጣት መሪ ከዙፋኑ ሳይነሳ ወደ አዛውንትነት መለወጥ… የመሠለ ኪሳራ የሆነው

ስለዛሬማ ምን አዲስ ነገር እነግርሃለሁ? ወንድሞችህ ስለነፃነት በተከራከሩ እንደተከረቸመባቸው? ቤተሰቦችህን የኑሮ ጫና እንዳጐበጣቸው? ወጣት እኩዮችህ የተሻለ ሕይወት ፍለጋ ሲሰደዱ በጠባብ ኮንቴነር እንደ ዕቃ ታጅለው ሕይወታቸው ስለማለፉ…? ይሄ ለቀባሪው አይነገርም፡፡

ባይሆን እኔ የምነግርህ ዛሬ መከራ የሆኑብህ ገገሮዎችህ ትላንት እንዳንተው በአገዛዝ ቀንበር ስር ነበሩ እናማ ውጤቱ ምንም ይሁን ምን በአላማ ፅናት ተሞልተው ወጣትነታቸውን ከፍለው አሁን ላሉበት መብቃታቸውን ነው፡፡

እናማ አባዬ የዛሬውም ሆነ የነገው ዕጣ ፈንታ በኔና አንተ እንቅስቃሴ ይወሰናል አሰልቺውን የጉልበተኝነት አስተሳሰብ አዙሪት ለመቀየር ሀላፊነት መውሠድ ይኖርብናል፡፡ በአመፅ፣ በትግል፣ በደም ላይ ተጉዞ ወደ ዴሞክራሲ መድረስ አይቻልም፡፡

እንደምታየውም ዛሬ ከለውጡ ሃያ አንድ አመታት በኋላ የትጥቅ ትግሉ የተመሰረተባቸው መደቦች በሙላ አረም ውጧቸዋል፡፡ ለህዝቡ የተዘራው በቡድኖች ታጭዷል፡፡ ያሸታሉ ተብለው በተስፋ የተጠበቁት ፍትሕና መልካም አስተዳደር፣ ልማትና እድገት የተምች ሲሳይ ሆነዋል፡፡

# ተስፋዬ ገብረአብ...

ለመፍጠር የፈለጋቸውን አጤ ምኒሊክ በዘዴ ያስተዋውቀናል፡፡

‹‹የመነን 4ኛ ባል›› የተሰኘ ፅሁፉ ደግሞ ያነጣጠረው አጼ ኃይለሥላሴ ላይ ነው፡፡ መነን በፊት ሁለት አግብተው ፈትተዋል ይለናል፡፡ ልጆችም አሏቸው፡፡ በኋላ ሦስተኛ ትዳራቸው ላይ ሳሉ ነው ልጅ ኢያሱ አፋትቶ ለራስ ተፈሪ ሲድራቸው የምንመለከተው ‹‹አምላክ በዚሁ በቃሽ ይበለኝ›› በማለት አራተኛ ትዳራቸውን የተቀበሉት እቴጌ መነን ዘመኑና ዘመነኞቹ ያደረሱባቸው ‹‹ጥቃት›› አጥንታችንን ሰርስሮ ይገባል፡፡ ይሄ እንግዲህ ተስፋዬ ገብረአብ ቆንፅሎ እንዳቀረበው ሁሉ ነገሩን ከሁኔታዎች ነጥለን ስንመለከተው ነው ሀፍረት እንዲሰማን የምንሆነው፡፡ ከዚያ ውጭ ግን ነገሩ ሌላ ነው፡፡ የዚያ ዘመን ፖለቲካዊ ሀይል የሚመነጨው ከዘር ብቻ ነበር፡፡ በመሆኑም አካባቢዎችና ግዛቶች ከማዕከላዊ መንግሥት ጋር ተሳስረው የሚቆዩት በፍትሃዊ የበጀት ክፍፍል ሳይሆን በሚዛናዊ የትዳር ስርጭት ነበር፡፡ ሁሉም አካባቢና ግዛት የጋብቻ ዝምድናንና መዋለድን ለዙፋኑ የነገ ተስፋ በዋስትናነት ከያዙ ብቻ የሰላሙ ተባባሪዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ በንጉሠ ነገሥቱና በመኳንንቱ አካባቢ የነበሩ ሴቶች እንደ ዋነኛ የፖለቲካ መሣሪያ መታየታቸው ግድ ነበር ይሄ በእኛ ብቻ ሳይሆን በአውሮፓውያን ታሪክ ውስጥ ቦታ ያለው ክስተት ነበር፡፡ የሔነሪ ስምንተኛን ታሪክ ማንበብ በቂ ነው፡፡

የተስፋዬ ገብረአብ በዚህ ዘመን አስተሳሰብ ለማስዳኘት ከታሪክ ጋር የመካሰስ አዝማሚያ ጅልነት ሳይሆን፣ መሰሪነት እንዳለበት እንድንጠረጥር የሚያደርገን ይሄ ነው፡፡ ተስፋዬ ያለጥርጥር ከታሪክ ነቁጥ ኢትዮጵያዊ የስብዕና ነውጥ ለመፍጠር በመሞከር ላይ ነው፡፡ በተስፋዬ ገብረአብ መስገር ሁልጊዜም የሚፈልገው ቦታ የሚደርሰው ጆርባውን የተከራየው አካል እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ተስፋዬ የራሱ መዳረሻ የለውም፡፡ ተስፋዬን እዚህ ታሪክ የመቅመል ሥራ ውስጥ የከተተው ጆርባን አከራይቶ የመኖር ፈረሳዊ ጣጣ ነው፡፡ ጋላቢው መንፈስ በግልፅ እኔ ነኝ ባይልም ከተስፋዬ አሰጋገር አስጋሪውን መለየት የሚያዳግት አይደለም፡፡ ግን… ግን ተስፋዬን ያለጋላቢ የማይሰግር ‹‹የጋማ-ከብት›› አድርጐ አጉልኛ የገራው ማን ይሆን? እሱ እንደሚለው ባንወልደውም አሳድገነዋልና ጆርባን አከራይቶ የመኖር ፖለቲካዊ ስብዕናው የእኛም መሰደቢያ ገመና ሳይሆን ይቀራል? ‹‹አሳዳጊ…›› በሚል የገመና ተጋሪዎቹ መሆናችን እርግጥ ነው፡፡

## አውደ ታሪክ

# ዘራፍ ለዘራፍ ገጥሞ ሲዛረፍ፤ ጎበዝ ለጎበዝ ነፍስ ሲጋፈፍ

### ከአርበኞች ፉከራ የተቀነጨበ



ከታዴዎስ ታንቱ

ቢሳን ሐረዋጫ የደም ጎርፍ ያጥለቀልቃታል! የምሥራቅ አናብስት ተዘጋጅተዋል! ኮሎኔል ካናባሊ ወራሪዎቹን አስጠግቷል! ጦርነቱ ሊፈነዳ ተቃርቧል! የኢትዮጵያ አርበኛ ማንንም አይፈራም! የኮሎኔል ካናባሊ ኃይል በአሠራር እየገባ ምድብ ቦታውን ተረክቧል! የኢትዮጵያ አርበኞች ደግሞ በር በሮችን ይዘዋል! በዋናው በር መድፍ ተጠምዷል! በተቀሩት በሮች የመትረየስ ምድብ አለ፡፡ በጠባብ ስፋት የፈሪ መሬት ይስተዋላል! ድብልቅልቁ ይውጣ! ያበጠው ይፈንዳ! ድም.ም.ም.ም ድም.ም.ም.ም የኢትዮጵያ አርበኛ በመድፍ ተኩስ ጦርነቱን መርቋል! ከወራሪው ኃይል የአፀፋ ምላሽ ተሰምቷል! ቢሳን ሐረዋጫ የደም መሬት! ሁሉም ዓይነት የጦር መሣሪያ ያንባርቅባታል! ይሰማችኋል? ይሰማችኋል? አንድ! አንድ! አንድ! ቢሳን ሐረዋጫ ላይ ጦርነቱ ተፋፍሟል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል እንደ ቅጠል ረግፏል! የኢትዮጵያ ጀግኖችም ተሠውተዋል! ነፃነት ወይም ሞት! ጀግናው የኢትዮጵያ አርበኛ ሺመልስ ሀብቴ በታላቅ ጀግንነት ግምባር ቀደም ሆኗል! ጭንቅላቱን ከመትረየሱ ሥር ቀብሯል! ሺመልስ ሀብቴ የጀግኖች አውራ! አይበገሬው የኢትዮጵያ ልጅ! ድም! ድም! ድም! ድም! ድም! ይህ ከቢሳን ሐረዋጫ ጦር ሜዳ ቀጥታ የመትረየስ ድምፅ ነው! ጥቅምት 16 ቀን 1929 ዓ.ም!

ጦርነቱ ቀጥሏል፡፡ ሣር ቤቶች በእሳት ይነድዳሉ፡፡ ቢሳን ሐረዋጫ በጪስ ጉም ተሸፍናለች፡፡ በደም ጎርፍ ተጥለቅልቃለች፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል እጅግ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ተጠቅሟል፡፡ የኢትዮጵያ አርበኛ ጥቂት መድፎችና መትረየሶች ታጥቋል፡፡ የነፍስ ወከፍ የጦር መሣሪያዎቹ ደግሞ በጣም አርጅተዋል፡፡ በጀግንነት እንወድቃለን! የአድዋ ጀግኖች ልጆች መሆናችንን በተግባር እናረጋግጣለን! ይህ የኢትዮጵያ አርበኞች ድምፅ ነው! ጦርነቱ ሳይበርድ ውሎ መሽቷል፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ወደ ምሽጉ ተሰብስቧል፡፡ የኢትዮጵያ አርበኛ ደግሞ ጧት የያዛቸውን የመከላከያ በሮች አጠናክሮአል፡፡ ከበሮቹ አንዷት ጋት ወደ ኋላ አላፈገፈገም፡፡ አሁን መሽቷል፡፡ ምድር በጨለማ ብርድ ልብስ ተጀቡናለች፡፡ አርበኛው ከነጋ እህል አልቀመሰም፡፡ የጀግኖች አስክሬን ከባሕር ዛፍ በመጥረቢያ ተቆርጠው በልጥ በተበጁ ቃሬዛዎች ከአንድ ሣር ቤት ውስጥ ገብቷል፡፡ ቁስለኞች ደግሞ ለየት ያለ ቦታ ይዘዋል፡፡ አገልግል ተከፍቶ ከስንቅ ተቆንጥሮ ለቁስለኞች ምግብ ቀርቧል፡፡ ከሌሎቹ ተለይተው ለመመገብ ግን አልፈቀዱም፡፡ ስለዚህ ሁሉም የግድ አንድ ላይ መመገብ ነበረባቸው፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ግን አስክሬኖቹንና ቁስለኞቹን በጊዜ በካሚዮን ወደ ሐረር አስወስዷል፡፡ በቂ ሕክምና እንዲያገኙ ለማድረግ ከሐረር የቀረበ ከተማ በዘመኑ አልነበረምና፡፡

ጎሕ ቀደደ፡፡ የተወሰኑ አርበኞች የተሠዉ ጀግኖችን አስክሬን እንዲቀብሩ ተመድበዋል፡፡ ጥይት ይታደላል፡፡ የመከላከያ በሮችን በመጠበቅ ላይ ለነበሩ ጀግኖችም ተልኮላቸዋል፡፡ ቦምቦች ከተወሰኑ አርበኞች እጅ ውጭ አይገኙም፡፡ ጀግናው ሺመልስ ሀብቴ የአመራር አባላትን በውጊያ ስልት አፈፃፀም ላይ አነጋግሯል፡፡ አሁን የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ወደ አርበኞች የመከላከያ በር ተጠግቷል፡፡ በጣም ተጠግቷል፡፡ ድም! ድም! ድም! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተኩስ ከፍቷል፡፡ የኢትዮጵያ አርበኞች በአፀፋ ተኩስ ቢሳን ሐረዋጫን አናወጡት፡፡ ጀግና ይወድቃል፡፡ ግን ጠብመንጃው አይማረክም፡፡ አስክሬኑም አይጎተትም፡፡ ቆራጡ የኢትዮጵያ አርበኛ ከመቅፀበት ይወረወራል፡፡ አስክሬኑን በክብር ያገላላል፡፡ ጠብመንጃውንም ያነሳል፡፡ ጦርነቱ ቀጥሏል፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ በሰው ኃይልና በጦር መሣሪያ የበላይነትን በመያዙ በጀግኖቹ የኢትዮጵያ አርበኞች ላይ የከፋ ጉዳት ይስተዋላል፡፡ ለሀገራችን ደማችን ይፈስሳል! ፋሽስት አይገዛንም! አረንጓዴ፣ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማችን ነው! ይህ የአርበኞች ድምፅ ነው! ከቢሳን ሐረዋጫ የጦር ሜዳ ጥቅምት 17 ቀን 1929 ዓ.ም

የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ባሁኑ ሰዓት በቢሳን ሐረዋጫ ዙሪያ እየተሽሎከሎከ በአርካሽ ስብከት የነዋሪዎችን ልብ ለመግዛት ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ ይታያል፡፡ ለዓላማው ለማዳ ባንዳዎችን በገፍ አሰማርቷል፡፡ ፍርኖ ዱቄት፣ ስኳርና ሻይ ቅጠል ያድላል፡፡ ገናናው የኢጣሊያ መንግሥት ለኢትዮጵያ ሕዝብ መልካም ነገር ብቻ እንደሚያስብ ለማስገንዘብ ይጥራል፡፡ በተጓዳኝም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንነው በኢየሩሳሌም ገዳም የገቡ በማስመሰል ወሬ ይዘራል፡፡ ጦርነቱ አሻቅቧል፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በኢትዮጵያ ምድር ላይ ሆኖ ዕርቅ አይታሰብም፡፡ ኮሎኔል ካናባሊ የአርበኛውን የሺመልስ ሀብቴን ጀግንነት አሳምሮ ያውቃል፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ነዋሪዎችን ከአርበኞች ለመነጠል ቆርጦ የተነሣ ይመስላል፡፡ እሾህን በእሾህ በሚል መርህ ይሠራል፡፡ ከትናንትናው በከፋ መልኩ የኢትዮጵያ አርበኞች መሥዋዕት ሆነዋል፡፡

ጦርነቱ በአሰቃቂ ይዘቱ የጀግኖቹን ሕይወት እየተመገበ በተልዕኮው ቀጥሏል፡፡ በሒደቱ አሳዛኝ ወሬ ከታማኝ ምንጭ በአርበኞች ጆሮ ዘልቋል፡፡ በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የተሰበኩ የቢሳን ሐረዋጫ ዙሪያ ነዋሪዎች በጀግኖቹ የኢትዮጵያ አርበኞች ላይ ክንዳቸውን አስተባብረው ተነሥተዋል፡፡ አርበኞች በአደራ ያስቀመጧቸውን የጋማ ከብቶች ፍየሎችና ጥራ ጥሬ ወስደው ለፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል አስረክበዋል፡፡ አደራ መብላት በኢትዮጵያ ባሕል ነውር ነበር፡፡ ከሐዲዎች ግን ሕሊናቸውን በዕለታዊ ጥቅም ሸጠዋል፡፡ ብኩርናቸውን ለፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሰጥተዋል፡፡ ቁስለኞችንም ካረፉበት ቤት አስወጥተዋቸዋል፡፡ ጀግናው ሺመልስ ሀብቴ ጭንቅላቱን ከመትረየሱ ሥር እንደቀበረ ይህን አሳዛኝ ወሬ ሰምቷል፡፡ ዙሪያውን ተከብቧል፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ በሰው ኃይል እያሻቀበ መጥቷል፡፡ አንድ ፋሽስት ሲገደል አምሥት ይተካል፡፡ አርበኞች በሰው ኃይል በጣም ወርደዋል፡፡

ጀግናው ሺመልስ ሀብቴ አሁንም በከፍተኛ ወኔ ይስተዋላል፡፡ ከበባውን ለመስበር ቆርጧል፡፡ ከአርበኞች የተማረከ የለም፡፡ ጦርነቱ ቀጥሏል፡፡ አሁን መሽቷል፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተኩስ አቁሟል፡፡ በአርበኞች በኩልም ተመሳሳይ አቋም ተወስዷል፡፡ የባሩድ ሽታ ቀንሷል፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የኢትዮጵያ አርበኞች በጣም እንደ ተጎዱ አውቋል፡፡ በሐሳቡ በነጋታው ጦርነቱን እንደማይቀጥሉ ገምቷል፡፡ ግን ግምቱ አልሠራም፡፡ ልክ አሥራ ሁለት ሰዓት ሲሆን የኢትዮጵያ ጀግና የመትረየስ ድምፅ አሰማ፡፡ ጦርነቱ ወዲያው ተፋፋመ፡፡ ለአፍታም ሳያቋርጥ ቀጥሎ ዋለ፡፡ ሆኖም ወራሪው ኃይል የአርበኞችን የመከላከያ በር ሰብሮ ለመግባት አልቻለም፡፡ እርግጥ ነው፡፡ አርበኞችም ወደ ፊት አልገፉም፡፡ ጥቅምት 18 ቀን 1929 ዓ.ም.

በጀግናው የኢትዮጵያ ውድ ልጅ በሺመልስ ሀብቴ የተመራው ቆራጡ አርበኛ እንደ አለፉት ቀናት ሁሉ ጥቅምት 19 ቀን 1929 ዓ.ም. ሲዋጋ ውሏል፡፡ የአራት ቀናት የጀግንነት ውሎ ወደ ታሪክ ወርዷል፡፡ ሐሰት አላወራም፡፡ ካድሬ አይደለሁም፡፡ ወይም ደግሞ በባለሥልጣን ምንዳ የአገዛዙን መለከት የምነፋ የፕሮፓጋንዳ ሰብዓዊ ዕቃ አይደለሁም፡፡ ለምን እዋሻለሁ? በፍፁም አልዋሽም! ሐቅ ጎርጓሪ እውነት ተናጋሪ የሕሊና ጋዜጠኛ ነኝ! በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በምሥል የተቀረፀውን የእህል ቡቃያ በወሬ አስደግፌ የምቀባጥር ውስጠ ሙት ልማታዊ ተቀጣሪ አይደለሁም! ታሪክ አወራለሁ! ዕውነት እናገራለሁ! ኢትዮጵያ ሰው ነበራት! ነበራት! ነበራት!

አሁን ጀግናው የኢትዮጵያ አርበኛ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልንና የቢሳን ሐረዋጫ ዙሪያ ነዋሪ ከሐዲዎችን ጥምር ከበባ በመበጠስ ከቀለበቱ ወጥቷል፡፡ በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ እጅ የተማረከ አንድም አርበኛ አልነበረም፡፡ የተሠዉ ጀግኖች አስክሬን ተቀብሯል፡፡ አውሬ ቆፍሮ እንዳይበላው እሾህ ከአፈር ቀድሟል፡፡ ምድብተኛ ቀባሪዎች ፈጣን ተግባራዊ እንቅስቃሴ አከናውነዋል፡፡

ለሉዓላዊነታችንና ለአንድነታችን በተከታታይ ለአራት ቀናት የተዋጋው ጀግናው የኢትዮጵያ አርበኛ ከብዙ ድካም በኋላ አሁን አሩሲ ፈረቀሳ ገብቷል፡፡ ጀግናው ሺመልስ ሀብቴ አርበኞችን አስከትሎ በሰው ኃይልና በጦር መሣሪያ የላቀ ብልጫ ከነበረው ወራሪ ኃይል ጋር ለቀናት የመዋጋቱ ወሬ ከሐረርጌ አንሥቶ እስከ ሲዳሞ ተሰምቷል፡፡ የወሬ ምንጩ ወገን ብቻ አልነበረም፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልም በአውራ ሽፍታነት መዝግቦታል፡፡ ሺመልስ ሀብቴ ስሙ ገንኗል፡፡ የግድ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ግን በስሙ የሚጠራው ሰው አልነበረም፡፡ ይልቁንም አባ ትንታግ ጎልቶ ወጥቷል፡፡ ጾሙን ውሎና አድሮ ተዋግቷል፡፡ አሁን ግን ውስን እርዳታ ከሌሎች አርበኞች መጥቷል፡፡ አባ ትንታግ በፈረቀሳ ውስጥ ለሃያ ቀናት ቆይቷል፡፡ ቁስለኛ ጀግኖች በመጠኑ አገግመዋል፡፡ በተሰዉት ምትክም በውስን መልኩ ሰዎች ተገኝተዋል፡፡

ቆራጡ ሺመልስ ሀብቴ አሁን ከፈረቀሳ ተነስቶ ወደ ባሌ አቅንቷል፡፡ ቀጥታ መስመር አልነበረም፡፡ በመንገድ መሪ ሐሳብ የማቋረጥ ጉዞ ተመርጧል፡፡ ባንዳ በሆዱ አስቦ በሕሊናው ይፀዳዳል፡፡ ኢ-ተጠየ ቃዊ አገላለፅ ይመስላል፡፡ ከሕሊና ሆዱን ለሚያስቀድም ግን ይሠራል፡፡ ባንዳና ጅብ ልብ የላቸውም፡፡ አልባሶ በተባለ ቦታ ላይ አባትንታግን ሊወጋው መጣ፡፡ አንድም ጣሊያን አልነበረም፡፡ ባንዳ ብቻ ነበር፡፡ ነገር ግን ፈርቶ አንድ ጥይት እንኳን ሳይተኩስ ተመልሷል፡፡ ታዝዞ የመጣው ከጢቾ እንደ ነበር ታውቋል፡፡

የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ግን የጀግናውን የሺመልስ ሀብቴንና የተከታዮቹን እንቅስቃሴ ከመከታተል ለአፍታም አልታቀበም፡፡ በጉዞ ላይ በነበሩበት ቦምብ ሊጥሉ አይሮፕላኖች መጡ፡፡ ዝቅ አሉ፡፡ ይህችን ይወድዳል የኢትዮጵያ አርበኛ! አንበሳው ሺመልስ ወዲያው ወደ ላይ ተኩሰባቸው፡፡ አንደኛው አይሮፕላን ተመትቶ ዱብ አለ፡፡ ሁለተኛው ግን በሙሉ ኃይሉ በማሻቀብ አምልጧል፡፡

በቆፍጣናው የኢትዮጵያ ልጅ በሺመልስ ሀብቴ የተመራው ጀግናው አርበኛ መንገዱን ከባንዳ እያፀዳ ባሁኑ ሰዓት ዶዶላ ገብቷል፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ያለ የሌለ ኃይሉን ሰብስቦ በድንገት ጦርነት ከፈተ፡፡ ጀግናው አርበኛ አፀፋውን መልሷል፡፡ ጦርነቱ ተፋፋመ፡፡ የኢትዮጵያ አርበኛ ከወራሪው ኃይል የጦር መሣሪያና ራዲዮ በብዛት ማርኳል፡፡ በዚሁ አላበቃም፡፡ ወራሪውን ኃይል እያሳደደ ጉዞውን ቀጥሏል፡፡ ጀግናው ሺመልስ ሀብቴ ቆርጧል፡፡ ለእናት ሀገሩና ለክብሩ ይሠዋል፡፡ በውርደት ከመኖር በጀግንነት ማለፍን መርጧል፡፡ አርበኞችን አስከትሏል፡፡ ግፋ ወደ ፊት! ይህ የጀግናው የሺመልስ ሀብቴ ድምፅ ነው! ጥር 23 ቀን 1929 ዓ.ም!

የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ ጀግናው ሺመልስ ሀብቴ የጋራ ሙለታ አበጋዝ እንደ ነበረ ተመልክቷል፡፡ በዚሁ በጋራ ሙለታ ውስጥ ሆኖ ግን የጦርነት ዝግጅት ያደርግ ገባ፡፡ ለሀገሩና ለሐይማኖቱ ታማኝ የሆነ ሁሉ እንዲከተለው መልዕክት አሰራጨ፡፡ ሕይወቱንና ንብረቱ የወደደ ደግሞ በምርጫው ይፀናል፡፡ ሺመልስ ሀብቴ ማንንም አላስገደደም፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል አሁን ሐረር ገብቷል፡፡ አረመኔው ጄኔራል ግራዚያኒ በኢትዮጵያ ውስጥ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ያልገባበት አውራጃ እንዳልነበረ በመግለፅ ሺመልስ ሀብቴ እጁን ባስቸኳይ እንዲሰጥ ሰው ላከበት፡፡ ጀግናው ሺመልስ ግን ይህ ሐሳብ መቅረቡ በራሱ ትልቅ ውርደት መሆኑ ተሰማው፡፡ አባትንታግ በጣም ተናደደ፡፡ ለተላላኪ ሽማግሌዎች ግን እጁን የሚሰጥ ማን እንደሆነ ወደፊት እንደሚታይ በመግለፅ ለጊዜው በይቅርታ ለቀቃቸው፡፡

ከጥቂት ቀናት በኋላ ቁጥር ስፍር የሌለው የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ወደ ጋራ ሙለታ መጣ፡፡ ሺመልስ ሀብቴ ተዘጋጅቶ ጠበቃቸው፡፡ ከጋራ ሙለታ በሃያ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ዳዌ በተባለ ቦታ ጦርነት ተከፈተ፡፡ ጀግናው ሺመልስ ሀብቴ ጣሊያኖችንና የሊቢያ ቅጥረኛ ባንዳዎችን እንደ ሣር አጨዳቸው፡፡ እንደ ዛፍ ቆረጣቸው፡፡ በዚህ ጦርነት የፋሽስት ኮሎኔል ተገድሎ፣ ተገፍፎ ተቆራርጦ ተጥሏል፡፡ በሕይወት የነበረው የፋሽስት ወራሪ ኃይል ግን ሸሽቶ ሐረር ምሽጉ ውስጥ ገባ፡፡

ከዚህ መሪር ጦርነት በኋላ ደግሞ ኮሎኔል ካናባሊ ደደር ላይ ሆኖ ለሺመልስ ሀብቴ ሽማግሌዎችን ላከበት፡፡ ሽማግሌዎቹ ባለፈው ጥፋቱ ምንም እንደማይደረግና ኢትዮጵያን በማሠልጠን እንደ ጣሊያን ገናና ለማድረግ የመጣው ገናናው የኢጣሊያ መንግሥት ሹመት ሊሠጠው እንደሚፈልግ ለሺመልስ ሀብቴ ነገሩት፡፡ የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ! ተላላኪ ሽማግሌዎች ስንቴ በይቅርታ ይታለፋሉ? ጀግናው ሺመልስ ሀብቴ ከግንድ ጋር በማሠር በጥይት ቆላቸው፡፡ ከዚያን ጊዜ ወዲህ ለሺመልስ ሀብቴ ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሽማግሌ አልተላከለትም፡፡

ውድ የኢትዮጵያ ልጅ ጀግናው ሺመልስ ሀብቴ ባሁኑ ሰዓት በባሌ ውስጥ ሒቦና በተባለው ሥፍራ በተፋፋመ ጦርነት ግምባር ቀደም ተዋጊ ነው፡፡ ጥር 25 ቀን 1929 ዓ.ም.፡፡ ጦርነቱ ከጠዋቱ አራት ሰዓት አንስቶ ተጋግሏል፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በኮሎኔል ቢሊሣሪ እንደሚመራ ታውቋል፡፡ የኢትዮጵያ አርበኛ ደግሞ በቆራጡ ሺመልስ ሀብቴ አዋጊነትና ተዋጊነት ተሰልፏል፡፡ እጅግ አሰቃቂ ጦርነት ነበር፡፡ የሰው አካል በእሳት ሲነድድ ይስተዋላል፡፡ እግሮችና እጆች በከባድ መሣሪያና በቦምቦች ተቆራርጠው በየቦታው ወድቀዋል፡፡ ጦርነቱ ቀጥሏል፡፡ ይህ ከሒቦና ጦር ሜዳ ቀጥታ ድምፅ ነው! ጥር 25 ቀን 1929 ዓ.ም! ጦርነቱ ቀጥሏል! አሳዛኝ ክስተት ግን ተፈጥሯል! በጣም ያሳዝናል! ጀግናው የኢትዮጵያ ልጅ ሺመልስ ሀብቴ በታላቅ ጀግንነት እየተዋጋ በክብር ወድቋል! በጀግንነት ተሠውቷል! ባሌ ውስጥ ሒቦና በተባለ ሥፍራ ጥር 25 ቀን 1929 ዓ.ም. ግምባሩን ሳያጥፍ በቆራጥነት በታሪክ ከጀግኖች ጋር ተቀላቅሏል!! ኢትዮጵያ እናታችን ኩሪ! ለዘለዓለም ኑሪ!

የጀግናው ሺመልስ ሀብቴ ዕፅም፣ ፋሽስት ኢጣሊያ ከኢትዮጵያ ከተባረረ በኋላ ከተጣለበት ተነሥቶ አዲስ አበባ መጥቶ በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቅጥር ግቢ ውስጥ በክብር ማረፉ ተመልክቷል፡፡ ነገር ግን ዝርዝር ሥነ ሥርዓቱን በተመለከተ መረጃ አጥተናል፡፡ አዲስ አበባ ውስጥ በስሙ አንድ ትምህርት ቤት አለ፡፡ ባሌ ውስጥ ሒቦና ላይ አንድ መታሰቢያ የግድ ያስፈልገዋል! ጀግናው ሺመልስ ከፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ በፊት የፊታውራሪነት ማዕረግ እንደነበረው ታውቋል! ልጆች አሉት ይሆን? እናቱ መንታ ትውለድ! ዘሩ ይለምልም!

ዘራፍ ለዘራፍ ገጥሞ ሲዛረፍ፤
ጎበዝ ለጎበዝ ነፍስ ሲጋፈፍ፡፡

## የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ብይን በዓለም አቀፍ ተቋማት ተተቸ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት በእነ አንዷለም አራጌ መዝገብ በሽብርተኝት በተከሰሱት 24 ሰዎች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ማሳለፉን ተከትሎ የአሜሪካ መንግሥት ስቴት ዲፓርትመንት ተቃውሞ ማሰማቱ ተገለፀ፡፡ በመግለጫው እንደተመለከተው እስክንድር ነጋን ጨምሮ በሌሎች ጋዜጠኞች ላይ ፍርድ ቤቱ ያሳለፈው ብይን እንደሚያሳስበው በመጠቆም ውሳኔው በኢትዮጵያ የፀረ-ሽብር ህግ ይዘት እንዲሁም አገሪቱ ሕገ-መንግስታዊ ዋስትና በሰጠቻቸው በፕሬስ እና ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብቶች አተገባበር ላይ ጥያቄ የሚያስነሳ እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡

የስቴት ዲፓርትመንት ቃል አቀባይ የሆኑት ቪክቶሪያ ኑላንድ በጉዳዩ ላይ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፤ የጋዜጠኞች መታሰር ሚዲያዎች እንዳያብቡና ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት እንዳይዳብር ያለው ተፅዕና ከባድ መሆኑን በማመልከት ከኢትዮጵያ ጋር የሰብዓዊ መብት አያያዝን አስመልክቶ በነበረን ውይይት ሀሳብን የመግለፅ እና የፕሬስ ነፃነትን ማረጋገጥ ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የመሠረት ድንጋይ እንደሆነ አቋማችንን ግልፅ አድርገንላቸዋል ብለዋል፡፡ ‹‹ነፃ ሚዲያው በጥቃት ስር ባለባቸው አካባቢዎች ሁሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችም በጭቆና ስር ናቸው›› በማለት ሂላሪ ክሊንተን መናገራቸውን ያወሱት የስቴት ዲፓርትመንቱ ቃል አቀባይ ‹‹ለዚህም ነው ዩናይትድ ስቴትስ በየትኛውም የዓለማችን ክፍሎች የታሰሩ ጋዜጠኞች እንዲፈቱ ጥሪ የምታቀርበው›› ብለዋል፡፡

ዓለም አቀፎቹ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ተቋማት አምንስቲ ኢንተርናሽናል እና ሂዩማን ራይትስ ዎች በበኩላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቱ በተከሳሾች ላይ ያሳለፈውን ብይን በማውገዝ መንግሥት ክሱን ውድቅ በማድረግ እስረኞቹን በአስቸኳይ እንዲፈታ ጠይቀዋል፡፡ አምንስቲ የብይኑን ዕለት ‹‹ይህ ለኢትዮጵያ ፍትሕ የጨለማ ቀን ነው›› ሲል ገልፆታል፡፡ አለማቀፍ የጋዜጠኞች መብት ተሟጋቹ ሲፒጄ በበኩሉ በእስክንድር ነጋ እና ስደት ላይ ባሉ አምስት ጋዜጠኞች ላይ የተመሰረተው የሽብርተኝነት ክስ በፍርድ ቤት ተቀባይነት ማግኘቱን በመኮነን ‹‹የኢትዮጵያ መንግሥት በፀረ-ሽብርተኝነት ሕግ ሰበብ ነፃ ሀሳብን ለማፈኛነት እየተጠቀመበት ነው›› ብሏል፡፡ ለጋሽ ሀገሮች ብይኑን እንዲያወግዙ እንዲሁም ኢትዮጵያ የፀረ-ሽብር ሕጓን ታሻሽል ዘንድ ጫና እንዲያደርጉ ሲፒጄ ጠይቋል፡፡

በተያያዘ ዜና የፔን አሜሪካ ሴንተር ፕሬዚዳንት ፒተር ጎድዊን በመግለጫቸው ለጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ባስተላለፉት መልዕክት ‹‹ከእስር ተለቀህ በነፃነት እስከምትራመድ ድረስ ትግላችንን አጠናክረን እንቀጥላለን›› ብለዋል፡፡ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ከወራት በፊት የፔን ባርባራ ጎልድ ስሚዝ የነፃነት ተሸላሚ መሆኑ ይታወሳል፡፡ ቢቢሲ፣ ሮይተርስ፣ አጃንስ ፍራንስ ፕሬስ፣ አሶሺየትድ ፕሬስ፣ ዘጋርዲያንና ሌሎች ዓለም ዓቀፍ ሚዲያዎች በተከሳሾች ላይ የተመሰረተውን የሽብርተኝነት ክስ ሲመለከት የነበረውን ፍርድ ቤት በሁሉም ላይ የጥፋተኝነት ብይን ማስተላለፉን ሰፊ ሽፋን ሰጥተው ዘግበውታል፡፡

# ምርጫ 2002ን በምርጫ 97…

ሁለት ስለምርጫ 2002 የሚያወሳ ሲሆን፤ የመቋጫውን ወግ ጨምሮ ስድስት ምዕራፎች አሉት፡፡ በዚህም ክፍል ግንባሩ የለጋስነት ባህሪው ይበልጥ ተጎናጽፎ መቀጠሉ ይታያል፡፡ ከምርጫ 97 ትምህርት በመቅሰሙ ወጣቶችንና ሴቶችን የተመለከቱ ፓኬጆች መዘጋጀታቸው፣ መንግሥት የቅንጅት ታሳሪዎችን በመፍታት፣ የምርጫ ስነምግባር ድርድርን ማነሳሳቱ፣ የምረጡኝ ዘመቻና የሚድያውን ክርክር ‹‹ሰላማዊ›› እንዲሆን ማድረጉ ሁሉ ለለጋስነቱ ዋቤ ሆነው ቀርበዋል፡፡ በመገናኛ ብዙኃንና በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ዙሪያ ስለተወሰዱ እርምጃዎችና የወጡ ሕጎች ተብራርቷል፡፡ እርግጥም ይህ ዘመን የሉማሜ ወረዳ አርሶ አደሮች እንዳደረጉት አጀንዳው የልማት ብቻ እንዲሆን ሳት ብሎት ወደአልባሌ ጉዳይ (ነጻነት?) የሚገባ አለመኖሩ ተወድሷል፡፡ ይህ ክፍል በምርጫ 97 የተከሰቱ ሁነቶች እንዳይደገሙ በሚል ለተወሰዱ እርምጃዎች ማብራሪያነት በግልጽ የተንጸባረቀበት ነው፡፡ የምርጫውን ውጤት ካለፈው የምርጫ ሂደትና ውጤት አንጻር በማስተያየት የትክክለኛ ፖሊሲ ትሩፋት ተደርጎ እንዲወሰድ የተወተወተበት ነው፡፡ በአንጻሩ የተቃዋሚዎች ድክመት በስፋት ተዘርዝሮበታል፡፡ ውጤቱም ‹‹ያማረና›› ሂደቱም ሰላማዊ፣ ፍትሃዊ፣ ዴሞክራሲዊና ታኣማኒ (ሰፍዴታ) መሆኑ የተገለጸበት ክፍል ነው፡፡ እንደዚህ መሆኑን ለመመስከር የሚያወላዳ ባይሆንም፤ የ1987ቱንና የ1992ቱን ምርጫዎች ገምግመው “The Pretension of Democracy in Ethiopia” በሚል ርዕስ ስር እንዳሳተሙት እንደነትሮንቮልና ፓዝዋንግ እንዲሁም እነዚሁኑ ምርጫዎች ቃኝተው “Electoral Politics, Decentralized Governance and Constitutionalism in Ethiopia” (2007) በሚል ርዕስ ስር እንዳሳተሙት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ትምህርት ክፍል መምህራን ለ1997ቱና ለ2002ቱም እስኪሠራ እንጠብቅ ይሆን?

### ፖለቲካዊ ጥቃትና ፍራቻን መንዛት

መጽሐፉ በተቃዋሚዎች ላይ እንደተሰነዘረ ፖለቲካዊ ጥቃትና የሽብር ንዛት አድርገን ልንወስደው እንችላለን፡፡ የተቃዋሚዎችን ድክመት መጠቃቀስ የተለመደ ከመሆኑ አኳያ የአቶ በረከትን መጽሐፍ ልዩ አያደርገውም፡፡ ብዙዎች ‹‹የፖለቲካ ትንተና›› ሲጀምሩ እጅ ማሟሻ የሚያደርጉትም እንዲህ ዓይነቱን አካሄድ ነው፡፡ በአቶ በረከት የተስተዋለው ግን ከዚህም ተለየ ነው፡፡ በዶ/ር ብርሃኑ፣ በኢንጂነር ኃይሉ፣ በፕ/ር በየነ፣ በዶ/ር መረራ፣ በአቶ ቡልቻ ደመቅሳ ወይም በኢንጂነር ግዛቸው ላይ ስነበራቸው አመለካከት የሚያነሷቸው ጉዳዮች በክስተቱ ዙሪያ ስማቸው መነሳት ስለነበረበት ብቻ ነው ለማለት የሚቸግሩ ድግግሞሾችን ማስተዋል ይቻላል፡፡ የተነሱት ጉዳዮች ምን ያህል የተቃዋሚው ወገን እንኳን ሕዝብ ሊመራ ለራሱ ወጥነት የሚጎለውና አስጠያፊ ባህሪይ እንደነበረው የሚያመለክት ነው፡፡ ይህንኑ አስተያየት ያለፍተሻ የሚቀበልም ሊያነሳ የሚችለው ጥያቄ ግን፣ አቶ በረከት ለዚህ ጉዳይ የሰጡት ትኩረት ከመጠን ያለፈበትን ምክንያት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ከርሳቸው የማይጠበቅ ምስጢር እስከማውጣት ደርሰዋል የሚያስብል ነገር አድርገዋል፡፡ ኢንጂነር ግዛቸው ‹እነዚህን ጉረኞች ተዉአቸው› የሚል ጽሑፍ በፕ/ር ኤፍሬም ይስሐቅ ኪስ ውስጥ ከተቱ ብለው መጻፋቸው ሽማግሌዎቹን እንደ ሃላፊነታቸው የማያስከብር ነው፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ በሚያዝያ 30ው ሰልፍ ላለመገኘታቸው ምክንያት የሆናቸውን ሲጽፉም፣ ኢንጂነር ኃይሉ በምርጫ ፊርማው ጊዜ አሉኝ በሚል ያቀረቡትና ለመጀመሪያ ጊዜ አወቅሁኝ ያሉበት ሁኔታ ከግብረገብ አኳያ ለትችት የሚጋብዝ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ፖለቲካዊ ሽኩቻውን በመጽሐፍ ለመቀጠል ተቃዋሚውን ወገን እንደመሰባበሪያ ‹‹ተጨማሪ›› አጋጣሚ ተደርጎ ተወስዶም ይሆናል፡፡

አቶ በረከት ስምኦን በግላቸው ይሁን በሚወክሉት ቡድን ገፍተው ዕስር ይደርስብናል ብለው ፈሩ የሚሏቸውን የተቃዋሚ መሪዎችን የሚስሉበት ሁኔታ እንደአገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣን አነጋጋሪ የሚባል ይሆንብናል፡፡ ለምሳሌ ስለእነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ ዶ/ር መረራ ጉዲናና ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ የቀረበው ትረካና ጥቆማ ኃላፊነት መውሰድ የማይችሉ ስለመሆናቸው ለአንባቢው መልዕክት ለማስተላለፍ ያለመውን ያህል፤ የኢህአዴግ መንግሥትም በጡንቻው የሚያስፈራራ ደብቁኝ የሚያስብል፣ ሰዎች በተቀመጡበት ወንበር ስምጥ የሚያስደርግ፣ ጣት የሚቆርጥ ወዘተ እንደሆነ የሚያስረግጥ መሆኑ ይታያል፡፡ ስለዲሞክራሲያዊ ምርጫ ለማውሳት በተዘጋጀ መጽሐፍ ‹‹መግደልና መሞት ትፈልጋለህ›› የሚሉ አነጋገሮች የጸሐፊውና የሚወክለው ቡድን ጦረኛ ስብዕና ውጤት ይሆን? ሲያስብል፤ የዲሞክራሲ ትርክቱንን እዚያው በዚያው መና የሚያስቀር ይሆናል፡፡ በእንዲህ ዓይነት ያልተገባ አቀራረብ የአቶ በረከት መጽሐፍ ስለአምባገነን መንግሥት ባህሪ ማስተማሪያ ጥሩ ማጣቀሻ እንዳይሆን እንደምሰጋ ስናገር እስካሁን የዘረዘርናቸው ከመጽሐፉ አንድምታዎች ከብዙ በጥቂቱ መሆናቸውን ለመግለጽ እገደዳለሁ፡፡

# በግንቦት 7 ጉዳይ በሽብርተኝነት ወንጀል የተከሰሱት ግለሰቦች የተከሳሽነት ቃላቸውን ሰጡ

‹‹ከግንቦት 7 ጋር በመተባበር በአመራር ሰጪነት፣ ፈፃሚነትና አስፈፃሚነት በመሳተፍ በአዲስ አበባ፣ በአማራ ክልል እና በሌሎች ቦታዎች ህቡዕ ቡድን በመፍጠርና የሽብር ጥቃት ለማድረስ ተንቀሳቅሰዋል›› ሲል የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ክስ የመሰረተባቸው አራት ግለሰቦች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት ‹‹ተከላከሉ›› የሚል ብይን መስጠቱን ተከትሎ ባሳለፍነው ሰኞ ዕለት በችሎቱ የተከሳሽነት ቃላቸውን የሰጡ ሲሆን Sስት የጋራ ተከላካይ ምስክሮችንም አስምተዋል::

በዕለቱ የተከሳሽነት ቃላቸውን የሰጡት 1ኛ ተከሳሽ ታደለ መሰለ፣ 2ኛ ተከሳሽ መለስ ሰጤ፣ 3ኛ ተከሳሽ አበበ መልኬ እና 4ኛ ሻምበል አለሙ አያሌው ናቸው::

በ1ኛ ክስ መሠረት ሁሉም ተከሳሾች የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1)(ሀ)(ለ)፣ 38(1)(2) እና የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 3 እና 4 ስር የተመለከተውን ተላልፈው ተገኝተዋል::

ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ካልተያዙት የውጭና የሀገር ውስጥ አባሪዎች ጋር ተካፋይ በመሆን ግንቦት 7 የተባለውን የአሸባሪ ቡድን አባላት ሲያፈላልጉ ከቆዩ በኋላ በጥቅምት ወር 2002 ዓ.ም. ወደ ኤርትራ መሄዳቸውን ክሱ ጠቅሷል::

ከዚያም የዚሁ አሸባሪ ቡድን አካል የሆነውንና ራሱን የአማራ ዴሞክራሲያዊ ሀይል ንቅናቄ (አዴሀን) ብሎ የሚጠራው የሽብርና የአመፅ ቡድንን በህቡዕ አደራጅተውና ከግንቦት 7 አባላት ጋር በህቡዕ ግንኙነት ጀምረው ነበር::

በተለይም ከአንዳርጋቸው ፅጌና ሌ/ኮሎኔል አለበል አማረ ጋር ኤርትራ ላይ ግንኙነት በማድረግ፣ የጋራ የወንጀል አድማ ስምምነት በመድረስ፣ ህቡዕ ጉባዔ በማካሄድ፣ የሽብር ስትራቴጂና እቅድ ላይ በመወያየት፣ በማፀደቅ፣ ለዚሁ አላማ የማዕከላዊና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በመምረጥ በተዘጋጀው የሽብር እቅድና ስትራቴጂ ላይ በመወያየት፣ የሽብር ጥቃት የሚሰነዘርባቸው የመንግስትና የልማት ተቋማት ዝርዝር ላይ በመስማማት የስራ ክፍፍል አድርገዋል::

እንዲሁም ግንቦት 7 የተባለው አሸባሪ ቡድን የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያደርግ፣ የአሁኖቹ ተጠርጣሪዎች የሽብርና አመፅ ተግባሩን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ለማስቻል የተለያዩ ወታደራዊና ለሽብር ተግባር የሚረዷቸው ስልጠናዎች በመውሰድ የስራ ክፍፍል በማድርግ የወንጀል ድርጊቱን አላማ ውጤትና ፍሬ ሙሉ በሙሉ በመቀበል ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታ ሲንቀሳቀሱ እንደነበረ ክሱ ዘርዝሯል::

በሁለተኛ ክስ ደግሞ ተከሳሾቹ በሽብርተኛ ድርጅት ውስጥ በአሸባሪነት፣ በውሳኔ ሰጪነት፣ የሽብርተኝነት ድርጊቶች እንዲፈፀሙ ሰዎችን በመመልመል፣ በአባልነትና በተለያዩ ዘዴዎች በመሳተፋቸው በሽብርተኝነት ድርጅት ውስጥ በመሳተፍ ወንጀል ተከስሰው ነበር:: ተከሳሾች 3ኛ ክስ የቀረበባቸው የሽብር ወንጀል ለመፈፀምና ለማስፈፀም በህቡዕ ከኤርትራ መንግስትና ከግንቦት 7 የተላከላቸውን ገንዘብ ህገ-ወጥ አመጣጡን ሰውረው የተጠቀሙ፣ በስራ ላይ ያዋሉ፣ ያዘዋወሩና ያስተላለፉ በመሆናቸው ነው::

ዐቃቤ ሕግም በተከሳሾች ላይ 11 የሰው፣ ስድስት የሰነድና ሁለት የኤግዚቢት መረጃዎችን አቅርቦ እንደነበረ የክስ መዝገቡ ያስረዳል:: ፍ/ቤቱም የዐቃቤ ሕግን መረጃዎች መርምሮ ተከሳሾች እንዲከላከሉ በሰጠው ብይን መሠረት ከላይ በተጠቀሰው ዕለት ተከሳሾች በየተራ የተከሳሽነት ቃላቸውን ከሰጡ በኋላ የጋራ ሦስት ተከላካይ ምስክሮቻቸውን አድምጧል::

1ኛ ተከሳሽ ታደለ መሰለ በአማራ ክልል አዊ ዞን ዳንግላ ወረዳ ዳንግላ ቴክኒክ ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም መምህር እንደነበረ ከተናገረ በኋላ ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም. ጠዋት 1:00 ሰዓት ገደማ ሁለት የደህንነት፣ ሦስት የፌዴራል ፖሊስና አንድ ሹፌር ሆነው ላንድክሩዘር መኪና ውስጥ አስገብተውት ‹‹አንተ አሸባሪ ነህ፣ በቤትህ የተለያዩ መሳሪያዎች አሉህ›› እንዳሉት ጠቅሶ ከቤቱ የተገኘው የኮምፒውተር ሶፍትዌር ሲዲና የማስተማሪያ ቁሳቁሶች መሆኑን ለችሎቱ አስረድቷል:: አያይዞም ‹‹በዚህ አይነት በሃገሪቷ ውስጥ ያሉት 300,000 መምህራን አ`ባሪዎች ናቸው ማለት ነው?!›› በማለት ሲናገር ዳኞች ‹‹ትንታኔ አያስፈልግህም›› በማለት ተከሳሹን ገስፀውታል:: ዐቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድማገኝም ተከሳሹ በተናገረው ነገር ላይ ተቃውሞ አሰምተው ነበር::

ተከሳሹ ንግግሩን በመቀጠል ከባህርዳርና ከፍኖተ ሰላም ከተያዙ ሌሎች አምስት ሰዎች ጋር ተይዞ በአንድ መኪና ወደ አዲስ አበባ እንደመጣ፣ ከተያዙት ጋርም የተዋወቀው መኪና ውስጥ መሆኑን፣ በፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ታስሮ በነበረበት ወቅት ለፖሊስ የሰጠው ቃል በድብደባ ከመሙዳትና ከመሞት ይልቅ አንድ ቀን ሀገሩን ለማገልገል ባለው ተስፋ መሰረት እንደሆነ ተናግሯል:: በማስገደድ የተገኘ መረጃም በማስረጃነት ሊቆጠርበት እንደማይገባ፣ በምርመራ ወቅት ለመርማሪዎች ኢ-ሜይሉንና የሚስጥር ቁልፉን /ፓስዋርድ/ ከነገራቸው በኋላ ‹‹አሁን አታስፈልገንም›› ተብሎ ከሳምንት በኋላ በዶክመንቶች ላይ ፊርም መባሉን እና መርማሪዎች በኢ-ሜይሉ ላይ የተለያዩ የሀሰት ማስረጃዎችን ላለማዘጋጀታቸው ምንም ማረጋገጫ እንደሌለው ለፍ/ቤቱ አስረድቷል::

አያይዞም መርማሪዎችና ዐቃቤ ሕጎች በሀሰት ባቀነባበሩት ክስ በግፍ ታስሮ እንደሚገኝ፣ ዐቃቤ ሕግ ያቀረባቸው 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች እስክንድር መላኩና አየነው እጅጉ የሀሰት ምስክር ሆነው መቅረባቸውን፣ የሰጡትም የምስክርነት ቃል እርስ በእርሱ እንደሚጣረስ፣ በቀረበበት ክስ ላይ በቂ ማስረጃ አለመቅረቡን በመጥቀስ ፍ/ቤቱ ያቀረበውን የተከሳሽነት ቃል በመከላከያነት እንዲመለከትለት ጠይቋል::

ሁለተኛ ተከሳሽ መለስ ሰጤ የተከሳሽነት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ዳኞች ‹‹ለ1ኛ ተከሳሽ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ላንተም ይሰራል›› በማለት ለተከሳሹ አስረድተውት ነበር:: ተከሳሹም ስለ ሕገ-መንግስቱ፣ ኢትዮጵያ ስለፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ሰነዶችና ድንጋጌዎች፣ ስለሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ... ወዘተ በዝርዝርና በተደጋጋሚ በመግለፅ በፖሊስ የተያዘበት መንገድ ከህግ ውጪ መሆኑን ሲናገር ዳኞች አቋረጡትና ‹‹ሕጎቹን በዝርዝር እናነባቸዋለን:: ወደ ክሱ ፍሬ ሀሳብ ገብተህ የተከሳሽነት ቃልህን ስጥ:: ሕጎችን ደጋግመህ በመናገር የሌሎችንም ጊዜ አታባክን:: ክሱን ይከላከልልኛል በምትለው ፍሬ ነገር ላይ አተኩር›› በማለት ተግሳፅ እና ምክር ሰጡት::

በባህርዳር ከተማ በአማራ ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ኢንተርፕራይዝ መ/ቤት ውስጥ ሲሰራ እንደነበረ የገለፀው ተከሳሹ፣ ተወዳድሮ ሁለተኛ ድግሪውን እየተማረ እያለ ‹‹አሸባሪ›› ተብሎ መያዙን፣ በህጋዊ ፓርቲ ውስጥ ሲንቀሳቀስ እንደነበረ፣ ግንቦት 12 ቀን 2003 ዓ.ም. ምሽት 12:00 ላይ ስምንት ሰዎች ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ ይዘውት መደብደቡን፣ ‹‹የጦር መሳሪያና ቦንብ አለህ፣ አሳየን›› መባሉን፣ ነገር ግን ከቤቱ የስራ ዶክመንቶችና የፓርቲ ስብሰባ ሲመራ የተነሳው ፎቶ ግራፍ መገኘቱን ለፍ/ቤቱ አስረድቷል::

እንዲሁም በፌዴራል ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ እስር ቤት ድብደባ እንደተፈፀመበት፣ በድብደባው ደም እንደፈሰሰው፣ ራሱን ለማዳን ከፈለገ በሀሰት እንዲመሰክር መርማሪዎች በብዙ ነገር ሊያግባቡት እንደሞከሩ፣ ይሄም እነሱንም ሆነ እሱን እንደሚጠቅመው እንደነገሩት፣ በሀሰት ሰዎች ላይ መመስከር ስላልቻለም በእሱ ላይ በሀሰት እንደተመሰከረበት፣ በፖሊሶች ተገድዶ በሰነዶች ላይ እንደፈረመ፣ 1ኛ እና 2ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ሀሰተኛ መሆናቸውን፣ እርስ በእርሱ የሚጣረስ ሀሰተኛ ምስክርነት መስጠታቸውን እና በግንቦት 11 ቀን 2003 ዓ.ም. ተያዘ የተባለው ሀሰት መሆኑንና እሱ የተያዘው በነጋታው መሆኑን በመጥቀስ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃን ፍ/ቤቱ ውድቅ እንዲያደርግለት ጠይቋል::

3ኛ ተከሳሽ አበበ መልኬም በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል መተከል ዞን ፓዌ ወረዳ ነዋሪ ሲሆን ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት መሆኑን ገልጿል:: በ1991 ዓ.ም. የሀገሪቱ መከላከያ ሠራዊት አባል ሆኖ ማገልገሉንና በ1999 ዓ.ም. ከሠራዊቱ ተቀንሶ በመተከል ዞን ሚሊሻ ሆኖ በጥበቃና በፀጥታ ስራ ላይ መሰማራቱን አስረድቷል::

ዐቃቤ ሕግ ያቀረበበት የሰውና የሰነድ ማስረጃ ያለአግባብ በመቅረቡ ክሱን እንደሚቃወም በመጥቀስ የዐቃቤ ሕግ 1ኛና 2ኛ ምስክሮች ቃል ሀሰትና እርስ በእርሱ የሚጣረስ መሆኑን፣ ዐቃቤ ሕግ በጥቅምት ወር 2002 ዓ.ም. ኤርትራ መሄዱን ቢገልፅም ቀኑንና ጊዜውን መግለፅ አለመቻሉን፣ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ባለቤቱና ልጆቹ ባሉበት ቤቱ መበርበሩን፣ መንግስት ካስታጠቀው አንድ ክላሽ ጠመንጃና ሰባት ጥይቶች በስተቀር ምንም ነገር አለመገኘቱን፣ ዐቃቤ ሕግ መገናኛ ራዲዮ እንዳለው ቢገለጽም ሳሲኒ የተባለ ድርጅት ለስራ ሲጠቀምበት የነበረና በየቦታው ወድቆ ሕፃናት የሚጫወቱበት የዛገ፣ የተበላና የማይሰራ ራዲዮ መሆኑን አስረድቷል::

አያይዞም ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም. ከነበረበት ቦታ በጥርጣሬ ተይዞ ማዕከላዊ ሲገባ እጅግ ከፍተኛ ድብደባና ስቃይ እንደደረሰበት፣ ተገድዶ ለፖሊስ ቃል መስጠቱን፣ ይሄንን ለአራዳ ፍ/ቤት ማስረዳቱን፣ በሌሎች ላይ ከመሰከረ እንደሚወጣ፣ ካልመሰከረ ግን ‹‹ቆይ! እሰራልሃለሁ›› እንደተባለ፣ ከመኖሪያው አከባቢው ጋር በተገናኘ የተምታታ ነገር መገለፁን፣ ከተከሳሾች ጋር ለወንጀሉ በጋራ አብሮ መንቀሳቀሱ በክስ ቢገለፅም ተከሳሾችን ከተያዘ በኋላ እንዳወቃቸው ተናግሯል::

4ኛ ተከሳሽ አለሙ አያሌው (ሻምበል) በበኩሉም ‹‹ተሸባሪ እንጂ አሸባሪ አይደለሁም:: ግንቦት 9 ቀን 2003 ዓ.ም. ከባህር ዳር ታፍኜ ነው የመጣሁት:: ተያዝኩ የተባለው ግን በ11/09/2003 ዓ.ም. ነው:: አሸባሪ አይደለሁም:: ለዚህ የተገኘብኝ ማስረጃ የለም:: ያወደምኩት ንብረት የለም:: አይደለም ይሄን፣ የቲማቲም ጦርነት እንኳን እንዲደረግ አልፈልግም:: ሕገ-መንግስቱ የደማሁለትና የቆሰልኩለት ነው:: የቀረበብኝ ክስ የምማርበት ሳይሆን እኔን የሚያጠፋ ነው:: የሰለጠንኩትና ያደራጀሁት ነገር የለም:: የማሰለጥን እንጂ የምሰለጥን አይደለሁም::አማራ በመሆኔ ነው የታሰርኩት ጨርሻለሁ›› በማለት የተከሳሽነት ቃሉን ለፍ/ቤቱ ሰጥቷል::

ለተከሳሾች የጋራ ተከላካይ ምስክር ሆነው የቀረቡት አቶ ቢራራ አለሙ በግንቦት 2003 ዓ.ም. በማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ ጨለማ ክፍል ውስጥ በተከሳሾች ላይ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሆኖ ከቀረበው እስክንድር መላኩ ጋር ታስሮ እንደነበር ተናግሯል::

‹‹እስክንድር ቀኑን በማላውቀው ቀን ምሽት 1:00 ሰዓት ላይ ለምርመራ ተጠርቶ ሲመለስ በኮሎኔል መላኩ ተፈራ ላይ ስለመሰከረ ግለሰቡ አንስቶ ነበር:: ...‹እነ ታደለ መለስ ላይ ከመሰከርኩ ከእስር እንደምወጣ ተነግሮኛል› ብሏል:: ለእኔም ያንን ካደረገ እንደሚወጣ እና እሱም መስክሮ እንደሚወጣ ነግሮኛል›› በማለት ምስክሩ ለፍ/ቤቱ አስረድቷል::

የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድማገኝም በመስቀለኛ ጥያቄ ‹‹ማዕከላዊ ለምን ነበር የገቡት? ጨለማ ክፍሉ እንዴት ነው? በወቅቱ ካንተ ጋር እነማን ነበሩ? ‹እስክንድርን ፖሊስ ከመሰከርክ ትወጣለህ› ሲለው ሰምተሀል ወይ?›› የሚሉ ጥያቄዎችን አንስተው ነበር:: ምስክሩም የአርበኞች ግንባር አባል ተብሎ 10 ዓመት እንደተፈረደበት፣ ጨለማ ቤት የሚባለው መብራት ሲበራ ብርሃን እንደሚያሳይ፣ እስክንድርም ከመሰከረ እንደሚወጣ ሲናገር እንደሰማ እና በወቅቱ አብረውት ታስረው የነበሩትን ሰዎች በመጥቀስ ተናግሯል::

ፈይሳ ሰኚ የተባለው ሁለተኛ የጋራ ተከላካይ ምስክርም በወንጀል ምርመራ ከእስክንድር መላኩ ጋር አብሮ ታስሮ እንደነበረ፣ ከተከሳሾች ጋር ዳንግላ ላይ ተገናኝተው ወደ ወንጀል ምርመራ አብሮ እንደመጣ እና በእነሱ ላይ መስክሮ መውጣት በአማራጭነት በመርማሪዎች እንደተነገረው የምስክርነት ቃሉን ሰጥቷል::

ዐቃቤ ሕግ ‹‹ማዕከላዊ ለምን ገባህ? ምስክሩ በተከሳሾች ላይ በወቅቱ ስለመመስከሩ የምታውቀው ነገር አለ? እስክንድር ያንን ሲናገር የት ነበርክ?...›› በማለት መስቀለኛ ጥያቄ አቅርቦ ነበር::

ምስክሩም በኦነግ አባልነት በሽብርተኝነት ወንጀል ተጠርጥሮ መያዙን፣ በወቅቱ እስክንድር ስለመመስከሩ የሚያውቀው ነገር አለመኖሩንና ከእስክንድር ጋር ጨለማ ክፍል አብረው ታስረው እንደነበረ ተናግሯል::

ቴዎድሮስ አያሌው የተባለው ሦስተኛ ምስክርም አየነው እጅጉ (ሁለተኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር) ጋር ጨለማ ክፍል አብሮ ታስሮ እንደነበረ፣ ግንቦት 24/2003 ዓ.ም. አንድ ወፍራም ሰው ሰፊ አዳራሽ ውስጥ ‹‹በእነዚህ ሰዎች ላይ ትመሰክራለህ፣ ይሄ ለእኛም ለአንተም ጥሩ ነው›› ብለውኛል በማለት እንደነገረው እና እሱም (አየነው እጅጉ) ‹‹በእነ ጄኔራል ተፈራ ማሞ ላይ መስክረው እንደወጡት (ሰዎች) እኔም መስክሬ እወጣለሁ›› በማለት ሲናገር መስማቱን መስክሯል::

ዐቃቤ ሕግ ለሌሎቹ ምስክሮች አቅርቦት የነበረውን ተመሳሳይነት ያለው መስቀለኛ ጥያቄ ለምስክሩ አንስቶ ነበር:: ምስክሩም በአርበኞች ግንባር ምክንያት መያዙን፣ በወቅቱ ከእሱ ጋር እነማን እንደነበሩ እና በማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ ጨለማ ቤት መብራት ሲኖር ብርሃን ስለመኖሩ ምላሽ ሰጥቷል::

በመጨረሻም ፍ/ቤቱ የጋራ ተከላካይ ምስክሮች ቃል ተሰምቶ መጠናቀቁን ከገለፀ በኋላ የ2ኛ ተከሳሽ አንድ፣ የ3ኛ ተከሳሽ ሁለት እና የ4ኛ ተከሳሽ አንድ መከላከያ ምስክሮች እንዲሰሙና የ3ኛ ተከሳሽ የመከላከያ የፅሁፍ መረጃን ለመመልከት ለሐምሌ 20 ቀን 2004 ዓ.ም. ከሰዓት 8:30 ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቶ የዕለቱ ችሎት አብቅቷል::

# የጫት ግብር በፓርላማ ጭቅጭቅ አስነሳ

ለሀገር ውስጥ ፍጆታ በሚውል ጫት ላይ የሚጣለውን ታክስ ለማሻሻል፣ አፈጻጸሙም በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥ እና የተመጣጠነ እንዲሆን ለማድረግ እና ቀደም ሲል በስራ ላይ የነበረው የጫት ግብር በኤክሳይዝ ታክስ እንዲተካ ትናንት በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ተዘጋጅቶ የቀረበው ረቂቅ አዋጅ አባላቱን አጨቃጨቀ::

የፓርላማ ተወካዮቹን በከፍተኛ ደረጃ ያጨቃጨቀው የጫት ኤክሳይዝ ታክስ ረቂቅ አዋጁ ላይ ‹‹የጫት ንግድ የሚያካሂዱ ሰዎች ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆችን በመሸጥና በመግዛት ውስጥ ካሳተፉ ግለሰቦቹን የሚቀጣ አንቀጽ መካተት አለበት›› የሚለው ሀሳብ ከተከበሩ አቶ ግርማ ሠይፉ ለምክር ቤቱ በመቅረቡ ነበር::

የቀረበው ረቂቅ አዋጅ፤ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጫት በብዛት በሚመረትባቸው እና አመቺ በሚሆኑ ውስን ቦታዎች ላይ ብቻ ጣቢያዎችን በማቋቋም እንዲሰበስብ፣ በተጨማሪም በባለስልጣኑ የተሰበሰበው ታክስ ባለቤት ለሆነው ክልል መተላለፍ ስላለበት የግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን የሰበሰበውን ታክስ በየወሩ ለክልሉ እንዲያስተላልፍ ያዛል::

በምክር ቤቱ አባላት ተመርምሮ ለህግና ፍትሕ ቋሚ ኮሚቴ እንዲመራ በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ‹‹የሀገር ውስጥ ፍጆታን ለመቀነስ አዋጁ ቆንጣጭ መሆን አለበት›› የሚል ሀሳብ ከምክር ቤቱ አባላት ተሰንዝሮ ነበር::

አቶ ግርማ በረቂቁ ላይ እንዲካተት ያቀረቡትን ጥያቄ የተቃወሙት የተከበሩ አቶ ሀሡን አብዲ በጫት ዝውውር ውስጥ ከ18 ዓመት በታች ወጣቶችን የሚያሳትፉ ሰዎች ይቀጡ የሚለውን እቃወማለሁ:: መጠጥ ጠጥቶ ስራ እንደሚሰራ ሁሉ ጫት ቅሞ ስራውን የማይሰራ የለም:: ደግሞም የጫት ንግድ ከፍተኛ ገቢ ነው የሚያስገባው:: ስለዚህ የተከበሩ አቶ ግርማ ይህንን አስተሳሰባቸውን ማስተካከል አለባቸው::›› ሲሉ የምክር ቤቱ አባላትን ፈገግ አስብለዋል::

# በእነ ብርጋዴር ተፈራ ማሞ የክስ መዝገብ የይቅርታ ጥያቄ ያቀረቡ ታራሚዎች ታወቁ

‹‹ሕገ-መንግሥቱን እና ሕገ-መንግሥታዊ ስርዓቱን በኃይልና በትጥቅ አመፅ ለመጣል...›› በሚል በ2001 ዓ.ም. በእነ ብ/ጄኔራል ተፈራ ማሞ የክስ መዝገብ በዐቃቤ ሕግ ክስ ቀርቦባቸው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት በሞትና በእድሜ ልክ ፅኑ እስራት የተፈረደባቸው 23 ግለሰቦች ግንቦት 27 ቀን 2004 ዓ.ም. ለፍትሕ ሚኒስትር የይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት ይቅርታ ያቀረቡ ታራሚዎች ስም ዝርዝር ታወቀ::

ጉዳዩን አስመልክቶ ፍትህ ጋዜጣ ባለፍው ሳምንት ባቀረበችው ዘገባ ላይ ይቅርታ የጠየቁትን ግለሰቦች ስም ዝርዝር ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ማግኘት ሳይቻል ቀርቶ ነበር:: ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ስም ዝርዝሩን ከማረሚያ ቤት ማግኘት እንደምንችል ጥቆማ መስጠቱ ይታወሳል::

ነገር ግን ከሌሎች ምንጮቻችን ባገኘነው መረጃ መሰረት የይቅርታ ጥያቄውን ያቀረቡትን ታራሚዎች ለማወቅ ችለናል::

እነዚህም የሞት ቅጣት ፍርደኛ የሆኑት መላኩ ተፈራ፣ የዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ፍርደኞቹ የሸዋስ ምትኩ፣ ጉበና በላይ፣ የሸዋስ መንገሻ፣ እማዋይሽ አለሙ፣ ተመስገን ባይለየኝ፣ መስከረ ካሣ፣ አበራ አሰፋ፣ ሰለሞን አሻግሬ፣ ደምሰው አንተነህ (ሌ/ኮሎኔል)፣ አሳምነው ፅጌ፣ ብ/ጄኔራል ተፈራ ማሞ፣ መኮንን ወርቁ (ሻለቃ)፣ አለሙ ጌትነት (ሌ/ኮሎኔል)፣ ጌታቸው ብርሌ (ሌ/ኮሎኔል)፣ ፋንታሁን ሙሃባ (ኮሎኔል)፣ ምስጋናው ተሰማ፣ መንግሥቱ ተሰማ፣ መንግሥቱ አበበ፣ ጎbይራድ ፀጋው፣ አመራር ባያብል፣ ይበልጣል ብርሃኑ፣ ውድነህ ተመስገንና ጌቱ ወርቁ ናቸው::

# እነ ኮሎኔል አለበል አማረ በጠቅላይ ፍ/ቤት ዛሬ የቅጣት ውሳኔ ያገኛሉ

- ኮሎኔሉ በእድሜ ልክ ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ዐቃቤ ሕግ ጠይቋል
- ውሳኔ ከሚያገኙት ግለሰቦች መካከል አንዱ የአንዷለም አራጌ ወንድም ነው

በእነ አንዷለም አራጌ የክስ መዝገብ በሽብርተኝነት ወንጀል ተጠርጥረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት ጉዳያቸው ሲታይ ቆይቶ ፍርድ ቤቱ በነፃ ያሰናበታቸውና ዐቃቤ ሕግ ይግባኝ የጠየቀባቸው አራት ተከሳሾች ጠቅላይ ፍ/ቤት ጥፋተኛ ባላቸው መሠረት በዛሬው ዕለት የቅጣት ውሳኔ ያገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል::

የቅጣት ውሳኔ የሚያገኙት ግለሰቦች ኤፍሬም ማዴቦ፣ ኤልያስ ጥሪት (ሞላ)፣ ደሳለኝ አራጌ እና ኮሎኔል አለበል አማረ ናቸው:: ከኤፍሬም ማዴቦ ውጪ ሦስቱ ተከሳሾች ኤርትራ ውስጥ አሉ ተብሎ የሚገመት ሲሆን ዐቃቤ ሕግ ‹‹የስር ፍ/ቤት በተጠቀሱት ተከሳሾች ላይ የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ አልፎ በነፃ እንዲሰናበቱ አድርጓል›› በሚል ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ማመልከቱ ታውቋል::

ኤፍሬም ማዴቦ በግንቦት 7 ስር በሚታተም የውስጥ መጽሔት ላይ ለአዲስ አመት በቀረበው መግለጫ ላይ ግለሰቡ የግንቦት 7 የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ተብሎ በመጽሔቱ አዘጋጆች ዝርዝር ላይ መጻፉን የዐቃቤ ሕግ አቤቱታ ያስረዳል:: እንዲሁም አንዷለም አራጌ ከኤልያስ ጥሪት (ሞላ) እና ከኮሎኔል አለበል አማረ ጋር ያደረገው የኢ-ሜይል ግንኙነት የስር ፍ/ቤት በደንብ ሳይመለከተው መታለፉ ሌላኛው የዐቃቤ ሕግ አቤቱታ ነበር::

ዐቃቤ ሕግ በስነ ስርዓት ሕጉ 192 መሠረት ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃዎችን በማቅረብ የቀረቡት ማስረጃዎች ምን እንደሆኑና በስር ፍ/ቤት ያልቀረቡበትን ምክንያት በመግለፅ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ማመልከቻ እንዳቀረቡ ለማወቅ ተችሏል:: ከቀረቡት ማስረጃዎች መካከል በኮሎኔል አለበል ተመልምለው ከባህር ዳርና ከጉንደር ወደ ኤርትራ ሄደው የነበሩ ሁለት ምስክሮች ሚያዝያ 2/2004 ዓ.ም በፍ/ቤቱ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል::

እንዲሁም እነዚህ ሁለት ምስክሮች ኤርትራ በሄዱበት ወቅት ከኮሎኔል አለበል፣ ኮሎኔል ፍፁም እና አንዳርጋቸው ፅጌ ጋር የተወያዩበትን አጀንዳ ከምስክሮቹ ዲያሪ ላይ ተገኝቶ በማስረጃነት የቀረበ ሲሆን ይሄም በሌላ መዝገብ ላይ ተያይዞ እንደነበረ ለማወቅ ተችሏል::

ፍ/ቤቱም ዐቃቤ ሕግ ያቀረባቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች መርምሮ ባሳለፍነው ሰኞ ዕለት በአራቱ ተከሳሾች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቶ ነበር::

ዐቃቤ ሕግ የቅጣት አስተያየቱን በጽሑፍ ያቀረበ ሲሆን ከወንጀሉ ክብደት አኳያ ጥፋተኝነታቸው በቅርቡ በእነ አንዷለም አራጌ ላይ ከተሰጠው ውሳኔ ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን ጠቅሶ፣ ኮሎኔል አለበል ከዚህ ቀደምም በሌላ ወንጀል ቅጣት ተጥሎባቸው ስለነበር ከጥፋታቸው ተደጋጋሚነት አኳያ ቅጣታቸው ከብዶ በእድሜ ልክ ፅኑ እስራት እንዲቀጡ አመልክቷል:: ሌሎቹ ተከሳሾች ግን ተደጋጋሚ የወንጀል ሪከርድ ስለሌለባቸው ጥፋተኛ በተባሉት የሕግ አንቀጽ ሥር ከባድ በሚባለው ደረጃ የፅኑ እስራት ቅጣት እንዲወስን ዐቃቤ ሕግ አመልክቷል::

# የፕ/ር መርጋ በቃናን ዳግም መመረጥ መድረክ ተቃወመ

### የፓርላማው ውሎ ከተጠናቀቀ በ|ሳ ኢህአዴግ ብቻውን ተሰብስቦ ነበር

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድን በቦርድ አባልነት እንዲያገለግሉ በጠ/ሚኒስትር ጽ/ቤት በኩል የተመረጡት ዘጠኝ የቦርድ አባላት ሹመት በትላንትናው ዕለት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ፀደቀ::

የቦርዱ አባል ሆነው ከተመረጡት ዘጠኝ ግለሰቦች መካከል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ተገኔ ጌታነህ የሚገኙበት ሲሆን ቦርዱን በሰብሳቢነት እንዲያገለግሉ ፕ/ር መርጋ በቃና በድጋሚ ተመርጠዋል:: በዕለቱ የዶ/ር አዲሱ ገ/እግዚአብሔር፣ የዶ/ር መሕሙድ አብዱላሂ፣ የአቶ ፍቅረማርያም በረደድ፣ የወ/ሮ ሙሉ አባተ፣ የአቶ ዝናሬ ማሞ፣ የአቶ እንይ ሀይሌን እና የአቶ አላመረው ከበደን ሹመት ምክር ቤቱ ሲያፀድቅ በጉዳዩ ላይ ጠንካራ ክርክር ገጥሞት ነበር::

‹‹በእኛ እምነት እነዚህ የምርጫ ቦርድ አባላት በሠሩት ስራ ስንገመግማቸው የስራ ድርሻቸውን የተወጡ ስላልሆኑ እኛ አንቀበልም::›› በማለት ሹመቱን መቃወም የጀመሩት የመድረክ ተወካይ የተከበሩ አቶ ግርማ ሠይፉ ‹‹እነዚህ የምርጫ ቦርድ አባላት አንድ ለአምስት የምርጫ አካሄድን ልክ ነው ያሉ ናቸው:: ምክር ቤቱ ውስጥ ያሉትም በዚህ መስፈርት የተመረጡ ስለሆኑ ልክ ነው ይላሉ::›› ሲሉ ተቃውሟቸውን አሰምተዋል::


አቶ ግርማ ያቀረቡትን ተቃውሞ ተከትሎ ምላሽ የሰጡት የኢህአዴግ ተመራጭ የተከበሩ አቶ አስመላሽ ‹‹የምርጫ ቦርድ አባላት ታማኝነት ያላቸው ናቸው:: ያሉትም አንድ ፓርቲ የሚፈልገውን አካሄድ ይከተል ነው እንጂ፤ ኢህአዴግ እንደዚህ ይደራጅ አንድነትም እንደዚህ ይደራጅ አላሉም::›› ሲሉ ገልፀዋል:: አያይዘውም ‹‹በሀገሪቱ የሚደረገውን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የሚያደናቅፍ ሕገ-ወጥ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው:: ይህ ለማንም አይጠቅምም!›› በማለት በማስጠንቀቂያ መልክ ተናግረዋል::

የቀረቡትን የቦርድ አባላት ሹመት ተከትለው አስተያየታቸውን ለምክር ቤቱ ያሰሙት የተከበሩ ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ ‹‹ገዢው ፓርቲ ያስቀመጠውን ተቃዋሚዎች አይቀበሉም:: ተቃዋሚዎች ያስቀመጡትን ገዥው ፓርቲ አይቀበልም:: እኔ እንደ አንድ የግል ተወዳዳሪ የተወዳደርኩት ከከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣን ጋር ነበር፤ ምርጫ ቦርድ በእኩል ዳኝቶና የሚመሰገን ስራ ሰርቶ ነው ያለፈው›› ሲሉ የቦርዱን አባላት አሞካሽተዋል:: እንዲሁም ‹‹የተከበሩ አቶ ግርማ ሠይፉ በምክር ቤቱ ያሉ አባላት በአንድ ለአምስት አደረጃጀት የተመረጡ ናቸው ብለዋል:: ነገር ግን እኔ አንድ ለአስር አደረጃጀት ተመርጬ ነው የመጣሁት›› ብለዋል::

አያይዘውም ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ ‹‹የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድን በቦርድ አባልነት ለማሾም የቀረበው የሹመት ደብዳቤ ለምን አልታደለም?›› የሚል ጥያቄ ምክር ቤቱ ያቀረቡ ሲሆን ይህንን ጥያቄ ተከትሎ መልስ ባለመሰጠቱ አንዳንድ የምክር ቤት አባላት ጠ/ሚንስትሩ በደብዳቤው ላይ ስላልፈረሙ ይሆናል የሚል ጥርጣሬ እንዳላቸው በተለይ ለፍትህ ተናግረዋል::

በመጨረሻም በጠ/ሚኒስትር ጽ/ቤት በኩል የቀረቡት የምርጫ ቦርድ አባላት ለአምስት አመታት እንዲያገለግሉ ምክር ቤቱ ተቀብሎ ወስኗል::

በተያያዘ ዜናም የዕለቱ የም/ቤቱ ስብሰባ ከተጠናቀቀ በኋላ የኢህአዴግ አባላትና አጋር ፓርቲዎች ‹‹ቆዩ›› ተብለው የተቃዋሚ ብቸኛ የመድረክ ተወካይ አቶ ግርማ ሰይፉ እና የግል ተወካዩ ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ እንዲወጡ ከተደረገ በኋላ ኢህአዴግ ብቻውን መሰብሰቡ ታውቋል:: ‹‹ይሄ ጉዳይ ከፓርላማ ደንብ አኳያ ያስኬዳል ወይ?›› በማለት ለአቶ ግርማ ሰይፉ ላቀረብንላቸው ጥያቄ ‹‹እንግዲህ አንድ የሆነ የሚሰሩት የግል ጉዳይ እንዳላቸው እገምታለሁ:: ነገር ግን ተገቢ ነው ብዬ አላምንም:: ምክንያቱም ም/ቤቱ ሀገራዊ ጉዳይ ውይይት የሚደረግበት እንጂ የአንድ ፓርቲ የመሰብሰቢያ አዳራሽ አይደለም›› በማለት ምላሽ ሰጥተዋል::



# ‹‹አቤቱ ጸሎቴን ስማኝ፣ጩኸቴም ወደ አንተ ይድረስ››

## መዝሙረ ዳዊት ም.91(92)ቁ.1

ከጥቂት የሰቆቃ ዜና እረፍት በኋላ ዳግም የወገኖቻችንን የስቃይ እና ሞት ባልተለመደ አኳኋን ካልተለመደ ስፍራ ሰማን፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ወገኖቻችንን እዚሁ እትብታቸው በተቀበረበት፣ ቤተሰቦቻቸው፣ ጓደኞቻቸው፣ዘመድ አዝማድ ከሚኖሩበት ፣የልጅነት ትውስታቸው አሻራ ካረፈበት፣ የአመት በዓል ግርግሩ ከሚደምቅበት፣ ቅዳሴና አዛኑ በተመሳሳይ ከሚሰማበት……አገር ይልቅ የባዕዳንን ምድር እየመረጡ በስደት ሕይወት መከራቸውን መጋት ቀጥለዋል፡፡ በቀድሞ ጊዜ፣ በዚያ ትውልድ፣ በደጉ ዘመን ኢትዮጵያዊ መባል ኩራትና ክብር እንዳልነበር ሁሉ አሁን የማንም መሳቂያና መሳለቂያ ለመሆን በቃን፡፡ በንጉሰ ነገስቱ ጊዜ አንድም ኢትዮጵያዊ እንኳን እንጀራ ፍለጋ ይቅርና ለትምህርትም ቢሆን ወደ ውጭ አገራት ተልኮ የቀረ አልያም በሌሎች አገራት ጥገኝነት የጠየቀ እንዳልነበር ታሪክ ምስክር ነው፡፡ በደርግ ዘመን በፖለቲካ አለመረጋጋትና በህይወት የመኖር ዋስትና ማጣት ምክንያት የተጀመረው የሕዝብ ስደት ማዕበል አሁን ይበልጥ ተባብሶ ቀጥሏል፡፡

ከዚህ ቀደም እንደምንሰማው የዜጎቻችን የሞት መልዕክት ሁሉ በዚህ ሳምንትም ሌላ አስደንጋጭ ዜና ሰማን፡፡ የተሻለ ኑሮ ይኖራል በሚል ተስፋ ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመሄድ በጉዞ ላይ ከነበሩ ኢትዮጵያውያን መካከል 43 ያህሉ መሞታቸውን ከታንዛኒያ መንግሥት ተሰማ፡፡ ለኢትዮጵያ መንግሥት እንዲህ አይነት ዜናዎች አዲስ ባለመሆናቸው የተነሳ ብዙም የሚያስደነግጥና የሌሎችን እርብርቦሽ እና ድጋፍ የሚያስጠይቅ ሆኖ አላገኘውም፡፡

ከዚህ ቀደምም በጅቡቲ አቋርጠው ወደ ስደት ለመሄድ የሞከሩ ኢትዮጵያውያን በአንድ ኮንቴይነር ውስጥ ታጭቀው በመጓዝ ላይ እያሉ ከተሳፋሪዎቹ መካከል ብዙዎቹ መሞታቸውን ሰምተናል፡፡ የዜጐቻችንን ስደት ተከትሎ የሚሰማው የሞት ወሬ እያስተናገድንም ቢሆን አሁንም ከዚህ ስህተት ብዙዎቹ ለመማር ፍቃደኞች አልሆኑም፡፡ መቼም ማንም ሰው በሕይወት ከመቆየት ይልቅ ሞትን የመረጠበት ፣ከመኖር ይልቅ አለመኖርን የናፈቀበት፣ በአገር ከመሰንበት ይልቅ ስደትን ብቸኛ አማራጭ ያደረገበት……በታሪክ እንደአሁኑ የከፋ ወቅት አላጋጠመንም፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በረሃብና በሥራ እጦት እየተንገላቱ ከማለቅ፣ በወጣትነት እድሜ የቤተሰብ ሸክም ከመሆን ቢያንስ ቢያንስ በባዕዳን አገር ስራ ፍለጋ በሚል ሕይወታቸውን ለመገበር መንቀሳቀስ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ሆኖባቸው እንጂ ማን ከአገሩ፣ ከርስቱ፣ ከቀዬው ይሰደድ ነበር፡፡

በብሔር ግጭት፣ በረሃብ፣ በጦርነት፣ በፖለቲካ ነፃነት እጦት፣ በቂም በቀል፣ በሃይማኖት ግጭት፣ በመሬት ይዞታ እና በመሳሰሉት ሰበቦች ስንት ፍዳችንን አየን፡፡ አሁንም በከፋ ሁኔታ እያየን ነው፡፡ ቀጣዩ ትውልድ የሚይዘውን የሚጨብጠውን አጥቷል፡፡ ሕፃናት ያለ እድሜያቸው ከወላጆቻቸው ተነጥለው በጐዳና ላይ ወደቁ፡፡ አብዛኛው ህብረተሰብ በከፋ ድህነት ሲማቅቅ ሌሎች ጥቂት ግለሰቦች (ባለስልጣናት እና ከባለስልጣናት ጋር የተወዳጁ ባለሃብቶች) ከደሃው ጉሮሮ እየነጠቁ በክብር ላይ ክብር፣ በሀብት ላይ ሀብትን አከማቹ፡፡ ይሄ የሀገርን ምንነት እና በሀገር ውስጥ ለመቆየት የሚያግዝ የማንነት መንፈስ የሚያሳጣ ትልቅ የአድሏዊነትና የልዩነት መስመር ነው፡፡ አገር አለኝ የምንለው እንደማንኛውም ዜጋ በጋራ ሃብታችን ላይ እኩል የመጠቀም መብት የተከበረልን ጊዜ ነው፡፡ እንደማንኛውም ዜጋ እኩል የመወዳደር እድል ሲኖረን ነው፡፡ አለበለዚያማ በአገሬ መድልኦ እና መገለል ከደረሰብኝ፤ የሌላም አገር ሥርዓት ከዚህ የከፋ ምን ሊያመጣብኝ ይችላል በማለት ስደትን ምርጫቸው እንዲያደርጉ ተገደዋል፡፡

ከገዢው ፓርቲ ፖለቲካ ፍልስፍና የተለየ ርዕዮተ አለም በማራመዳቸው ምክንያት ለስደት የተጋለጡ ውድ የኢትዮጵያ ልጆችም ሞልተዋል፡፡ ፍትሕ ለገዢዎቹ ወገን ብቻ ካደላ፣ በሕግ ፊት ሁላችንም ያለምንም ልዩነት እኩል የመዳኘት መብታችን ሳይከበርልን ሲቀር፣ ከራሳችን አብራክ የወጡ መሪዎቻችን ባዕዳን ሲሆኑብን…… በሀገር የመኖር፣ አገር አለኝ የማለት መተማመኛችን ምንም ሲሆንብን የቀረን አማራጭ ስደት ብቻ ይሆናል፡፡ እዚሁ ችግሮችን ተጋፍጦ ከመኖር በሌሎች አገራት ሌላ የመኖር እድልን ሞክሮ የመጣውን መቀበል የመጨረሻው መፍትሄ ይሆናል፡፡በሀገሩ ከሚኖር ከአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ይልቅ የውጭ አገር ዜጐች በነፃነት የመኖር፣ ንብረት የማፍራት መብታቸው ሲጠበቅላቸው ያየ ሰው የኔስ ሀገር ከወዴት ነው? ሲል ይጠይቃል፡፡

የትምህርት ሥርዓቱ መውደቅ ከሚያስከትላቸው ስነ-አዕምሮአዊ ቀውሶች መካከል ግማሹን ባልተፈለገ ሱስ ሲጠምደው የተቀረውን ለስደት ይዳርገዋል፡፡ ተምሮ በነፃነት ማሰብና መስራት ያለመቻል ውጤት ዜጐቻችንን ከቀዬቻው እያራቀብን ይገኛል፡፡ የደሃ ገንዘብ ተሰብስቦ እንዲማሩ ዕድል የተሰጣቸው ብዙ ምሁራን የመስራት ነፃነታቸው በፖለቲካ ፍቃድ ላይ በመመስረቱ ምክንያት ሳይወዱ በግድ የሌላ አገር ዜጐች አገልጋይ ለመሆን ተገደዋል፡፡ የአገራችን ምሁራን ከራሳቸው አልፈው የሌሎች አገራትን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ያበረከቱት አስተዋፅኦ ቀላል የሚባል እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ሴት እህቶቻችን የቤተሰብ ሸክም ከመሆን በሌሎች አገራት ገረድ ሆነው መስራትን ይሻሉ፡፡ ከእነርሱ አስቀድመው ወደ አረቡ የአለም ክፍል ተጉዘው ከፍተኛ ችግር የደረሰባቸውን እህቶቻቸውን እያዩ እንኳን ወደኋላ አላሉም፡፡ ሞትን፣አስገድዶ መደፈርን፣ ከፎቅ ላይ መወርወርን፣ በፈላ ውሃ መቀቀልን፣ በአደባባይ አንገታቸው ታንቆ በሀገራቸው ኢምባሲ ፊት ለፊት መጐተታቸውን፣ ሰውነታቸው በስለት መወጋቱን እያዩ እንኳን ድርጊቱ ወደተፈጸመባቸው ሀገራት ለመሄድ አያመነቱም፡፡ በረሀብ ከመማቀቅ፣የቤተሰብ ሸክም ከመሆን ሞት ምን ያህል ቀላል እንደሆነ ከእነዚህ እህቶቻችን መማር እንችላለን፡፡ በኢምግሬሽን መስሪያ ቤት ተገኝቶ ወደ ውጭ አገራት ለመሄድ የተሰለፉትን ሴት እህቶቻችን ያየን እንደሆነ የስደት ምክንያቱ ምን ያህል መራር እንደሆነ እንድንገነዘብ ይረዳናል፡፡

በረሃብ የብዙ ህፃናት ህይወትን አጥተናል፡፡ በብሔር ግጭት ኢትዮጵያውያን እርስ በርሳችን ተላልቀናል፡፡ በጦርነት ሰበብ ትርፍ የሌለው የህይወት ዋጋን ከፍለናል፡፡ በፍትሕ እጦት ለዚህች አገር ትልቅ አስተዋፅኦ ማበርከት የሚችሉ ምሁራንን ለሌሎች ባዕድ ሀገራት አሳልፈን ሰጥተናል፡፡ የተሻለ ኑሮን ፍለጋ በመኪና ኮንቴነሮች ውስጥ ኢ-ሰብአዊ በሆነ መንገድ የብዙ ዜጐቻችን ህይወት እንደ ቅጠል ረግፏል፡፡ ከዚህም የባሰ ብዙ ብዙ መከራዎችን አሳልፈናል፡፡እያሳለፍንም ነው፡፡

ያለፉትን ሃያ አመታት ለእነዚህ ሁሉ ችግሮች መፍትሄ ይሆናሉ የተባሉ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ረቅቀው በተግባር ቢውሉም አንዳቸውም ለችግሮቻችን የመፍትሄ አካል መሆን ተስኗቸዋል፡፡ ይባስ ብሎ በታሪካችን ሰምተንና አይተን የማናውቃቸውን የእልቂት ዜናዎች ይህ ትውልድ መመልከት ጀምሯል፡፡ በችግሮቹ አሁንም ቢሆን በቅንነት መንፈስ መፍትሄ ከመፈለግ ይልቅ እንደ ተራ ክስተትና አጋጣሚ ሰምተንና አይተን ከማለፍ ውጭ አንዳችም የመፍትሄ እርምጃዎችን ለመውሰድ የተነጋገረ፣ ለተግባራዊነቱም የደፈረ ዜጋ የለም፡፡ በሰዎች ዘንድ መፍትሄ ለማግኘት ያሰብናቸው አማራጮች ሁሉ መፍትሄን አላስገኙልንም፡፡

**<u>በረሃብ የብዙ ህፃናት ህይወትን አጥተናል። በብሔር ግጭት ኢትዮጵያውያን እርስ በርሳችን ተላልቀናል። በጦርነት ሰበብ ትርፍ የሌለው የህይወት ዋጋን ከፍለናል። በፍትሕ እጦት ለዚህች አገር ትልቅ አስተዋፅኦ ማበርከት የሚችሉ ምሁራንን ለሌሎች ባዕድ ሀገራት አሳልፈን ሰጥተናል።</u>**

መፍትሄው ያለው እግዚአብሄር ጋር ብቻ ነው፡፡ በዳዊት መዝሙር 91(92) ላይ ባዘነና ልመናውን በእግዚአብሔር ፊት ባፈሰሰ ጊዜ የሚፀልይ የችግረኛ ፀሎት እንዲህ ይላል፡-

‹‹አቤቱ ጸሎቴን ስማኝ፣
ጩኸቴም ወደ አንተ ይድረስ፡፡
በመከራዬ ቀን ፊትህን ከኔ አትመልስ፤
ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል፣
በጠራሁህ ቀን ፈጥነህ ስማኝ፡፡
ዘመኔ እንደ ጢስ አልቃለችና
አጥንቶቼም እንደ መቃጠያ ተቃጥለዋልና፡፡
እህል መብላት ተረስቶኛልና
ተቀሰፍሁም ልቤም እንደ ሣር ደረቀ፡፡
ጠላቶቹ ሁልጊዜ ይሰድቡኛል
የሚያሳድዱኝም ተማማሉብኝ፡፡
አመድን እንደ እህል ቅሜያለሁና…››

እግዚአብሄር መፍትሄውን ያበጅልን፡፡ የመከራና የስደት ጊዜያትን በቃችሁ ይበለን፡ ፡እዚሁ ሀገራችን ላይ ሰርተን የምንኖርበትን መልካም ጊዜ ያምጣልን፡፡

አሜን ያምጣልን


ዕንቁ
የቤተሰብዎ መፅሔት

የፊታችን ቅዳሜ
ሰኔ 30/2004 ዓ.ም

ኖርዌይና ኑሮዬ
(የጉዞ ማስታወሻ)
ፒያሣ መሐሙድ ጋር ጠብቂኝ
ደራሲ መሐመድ ሰልማን

ከቴዲ አፍሮ ጋር
ያደረገችውን ቃለ-ምልልስ
የመጨረሻ ክፍል ሠፊ ሽፋን
በመስጠት ይዛልዎ ትመጣለች




- ቅዳሜ- አልበምህን ለቀቅክ፤
- ዕሁድ- ቀለበት አሠርክ፤
- ብዙም ሳይቆይ ማኔጀርህን አባረርክ፡፡ ከፕሮዲዩሰርህ አዲካ ጋር ውዝግብ ጀመርክ፡፡ ይሄ ነገር የጤና ነው? … ሁኔታዎች ጥድፍድፍ አላሉም?

. “አድጌ ሚስት ሣገባ የሠርጌ ዕለት ቢዘፍንልኝ ብዬ የምመኘው አንድ ድምፃዊ አለ፡፡ እሱም…”

. “ቤተሠብ ምጣኔዎች እንዳይሠሙብኝ እንጂ ቤቴን ልጅ በልጅ ላደርገው እመኛለሁ”

የቅዳሜ ቀጠሮዎ ከዕንቁ ጋር ይሁን

# ፍትህ

# ቃጫል ?

# ՂԺ ԻՈՒԻ